# ለአገልግሎት መነሳት

**የሩሂ ተቋም**
**2ኛ መጽሐፍ**

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| **ለተባባሪዎች** | **3** |
| **የማስተማር ደስታ** | **6** |

## ለተባባሪዎች

የሩሂ ተቋም ክፍሎች በአጠቃላይ ሶስት ዋና ዋና አላማዎች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ እዚህም በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ እይታዎችን ማስኘት ስለእምነቱ እውቀትን ማስጨበጥ እና የተለያዩ የግልጋሎት ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስፈልጉ ችሎታዎች ማዳበርን መርዳት ናቸው፡፡ በእርግጥ አንድ ክፍል በአንዱ ወይም በሌላው ዓላማ ሊያተኩር ይችላል፡፡ ለምሳሌ የአንደኛ መጽሐፍ ክፍሎች ተማሪዎች በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ እይታዎችን እንዲያገኙ የሚረዱ ሲሆን የሁለተኛው መጽሐፍ ክፍሎች በአብዛኛው ያተኮሩት የተለያዩ የግልጋሎት ተግባራትን ለመፈፀም በሚያስፈልጉ ችሎታዎች ላይ ነው፡፡

ምንም እንኳን የሩሂ ተቋም ክፍሎች የሚያተኩሩባቸው ዓላማዎች የተለያዩ ቢሆኑም ሁሉም የተመሰረቱበት ጽንሰ ሃሳብ "በግልጋሎት መንገድ መጓዝ" ነው፡፡ በተቋሙ ኘሮግራም የሚሳተፉ በግላዊ የመንፈስ እድገትና ሌሎችን በማገልገል ጎዳና ይሰማራሉ፡፡ የተቋሙ የተለያዩ ትምህርቶች ከተገቢ ጽንሰ ሐሳቦች ጋር በማስተዋወቅ በመንፈሳዊ ባህሪያቸውና አመለካከቶቻቸው ማዳበር ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግና እራሳቸውን ችለው በግልጋሎት ጎዳና እንዲጓዙ የሚያስፈልጓቸውን ችሎታዎች በማስታጠቅ ይረዷቸዋል፡፡ ጉዞው በጣም ቀላል ግልጋሎቶችን በማበርከት መጀመር የሚገባዉ ቢሆንም የተሳታፊዎቹ አቅም እየጨመረ በሄደ ቁጥር የበለጠ ውስብስብ የሆኑ አገልግሎቶችን ወደማበርከት ያድጋል፡፡

ተማሪዎቹ እውቀትን የሚገበዩበት አካሄድ ያገኙትን እውቀት ለሌሎች ለማካፈል እንዲያመች ተደርጎ መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም በግለሰብ ሕይወት ውስጥ የግል እድገት እና ሌሎችን ማገልገል የተዋሐዱ ጣምራ ነገሮች እንጂ አንዳንድ ጊዜ እንደሚታሰበው የሚነጣጠሉና ተቀናቃኝ እንዳይደሉ ለመገንዘብ ያስችላል የሚል ተስፋ ስላለ ነው፡፡ በሌሎች የሩሂ ተቋም ትምህርቶች እንደሚደረገው በክፍሉ ውስጥ ብዙ ተማሪዎች ካሉ አስጠኚው በትንንሽ ቡድኖች ሊከፋፍላቸው ይገባል፡፡

የሩሂ ተቋም የዚህ የሁለተኛው መጽሐፍ ክፍል ሁለት የሆነውን "የጥልቀት ትምህርት ጭብጦች" የሚለውን ትምህርት መስጠት ከጀመረ በኋላ አንዳንድ ተሳታፊዎች ቤተሰቦችን በመጎብኘት የጥልቀት ትምህርት ጭብጦችን ማካፈል ሲቀጥሉ ሌሎች ግን ብዙም ሳይቆዩ መቀዝቀዛቸውን አስተዋለ፡፡ የዚህን ምክንያት ለማግኘት ብዙ የምክክር ስብሰባዎች ተካሄዱ፡፡ ዋናው ልዩነት የመጣው አማኞች እምነቱን በማስተማር ስለሚገኘው የደስታ ምንጭ ካላቸው አንፃራዊ ግንዛቤ ልዩነት መሆኑ ተደረሰበት፡፡ በአጭር ጊዜ ውጤት የሚረኩ ወይም በፈፀሙት ተግባር መታወቅን ወይም ምስጋናን የሚሹ አብዛኛውን ጊዜ በጥረታቸው ጸንተው አይቆዩም፡፡ ያለማቋረጥ ቤተሰቦችን የሚጎበኙት አማኞች ደስታን የሚያገኙት ከማስተማሩ ተግባር ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ "የማስተማር ደስታ" በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ የመጀመሪያ ክፍል የዚህን መሰረታዊ ልዩነት ምንነት ለማብራራት ይሞክራል፡፡ በክፍሉ የታቀፉ ሐሳቦች በሚከተለው ቅደም ተከተል ቀርበዋል፡-

1. እምነቱን በምናስተምርበት ጊዜ በባሃኦላህ የተገለጸውን የአምላክ ቃል ለሌሎች የማካፈልን ልዩ ፀጋ እንቋደሳለን፡፡
2. የባሃኦላህ ግልጸት መለኮታዊ መመሪያ በጥልቀቱ ውስጥ እንቁዎች እንዳሉበት ውቅያኖስ ሊመሰል ይችላል፡፡ ወደዚህ ውቅያኖስ ዳርቻ ቀርበን ጥቅሞቹን ለማግኘት የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡
3. የባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ በሚያስደንቅ ሁኔታ ለእኛ ቅርብ ነው፡፡ ከፈለግን በአይን ጥቅሻ ፍጥነት የዚህ ውቅያኖስ ዳርቻ ላይ ልንደርስ እንችላለን፡፡
4. ባሃኦላህን የማወቅን በረከት ከተቀበልን በኋላ በግልጸቱ ውስጥ የሚገኙትን የመለኮታዊ መርሖ እንቁዎች ለሌሎች ማካፈል እንፈልጋለን፡፡ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ የእራሱን ቃል ኃይል እንጠቀማለን፣ የሰዎችን ልቦች ለመለወጥ የሚችሉ እነርሱ ናቸውና፡፡
5. በእለት ሕይወታችን ከምንጠመድባቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የአምላክን ቃል ከሌሎች ጋር የምንካፈልባቸው ጊዜያት ልዩ ናቸው፡፡

6. እምነቱን በምናስተምርበት ጊዜ ልቦቻችንን የሚሞላው ደስታ የሚመነጨው ከማስተማር ተግባር ብቻ ነው። ይህም በባሃኦላህ የተገለፀውን የአምላክ ቃል ከሌሎች ጋር መካፈል ነው። መታወቅና መመስገን በመሰሉ ነገሮች መጠመድ ይህንን ደስታ ያጠፋብናል። ደስታ የተሞላው ማስተማር ለማካሄድ መላቀቅ አስፈላጊ ነው።
7. ጥረት ለማድረግና ማስዋዕትነትን ለመክፈል ፈቃደኞች መሆን አለብን። ይህንን በምናደርግበት ጊዜ መንፈሳዊ ደስታን እያተረፍንና መንፈሰዊ እድገትን እያገኘን መሆናችንን ማስታወስ ይገባናል። መስዋዕትነት ከፍተኛውን ለማግኘት ከዝቅተኛው መገለል ነው። ማስዋዕትነት ጉዳትን የሚያስከትል ቢመስልም እውነታው ሲታይ ግን የደስታ ምንጭ ሆኖ ይገኛል።

የመጀመሪያው የአገልግሎት ተግባር "የጥልቀት ትምህርት ጭብጦች" በሚል ርዕስ በዚህ መጽሐፍ ወስጥ ቀርቧል። ይህም ትምህርት ተማሪዎች አዲስ አማኞች ቤት ድረስ ሄደው በመጎብኘት ዘለአለማዊ የአምላክ ኪዳን የባሃኦላህ ሕይወት የባሃኢ ማኅበረሰብ ፍቅርና አንድነት የባሃኢ ስብሰባዎችና የአስራ ዘጠነኛ ቀን በዓል መዋጮ የማድረግ አስፈላጊነትና እምነቱን ማስተማር በተሰኙ ጭብጦች ላይ ውይይት የማድረግን ብቃት እንዲያዳብሩ ይረዳል። ከእያንዳንዱ ጭብጥ ቀጥሎ የተለያዩ ጥያቄዎችና መልመጃዎች ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ተማሪዎች በጭብጦቹ ላይ ያላቸውን እውቀት ለማጎልበት የታቀዱ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ተማሪዎች ጭብጦቹን ለሚጎበኟቸው ቤተሰቦች የማስተላለፍን ችሎታ እንዲያዳብሩ ለመርዳት የተቀየሱ ናቸው። ከዚህ የቀሩት መልመጃዎች ደግሞ ይህንን የአገልግሎት ተግባር ሊያስጌጡ የሚገቡ መንፈሳዊ ባህሪያትንና አመለካከቶችን ይመለከታሉ።

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በዚህ ክፍል የተካተቱትን ጭብጦች ለመጀመሪያ ጊዜ በጥልቀት የማጥናትን እድል ያገኛሉ። ተማሪዎቹ እውቀትን የሚገበዩት ለሌሎች ለማካፈል እንዲያመች ተደርጎ መሆኑን ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ይህም በግለሰብ ሕይወት ውስጥ የግል እድገት እና ሌሎችን ማገልገል የተዋሐዱ ጣምራ ነገሮች እንጂ አንዳንድ ጊዜ እንደሚታሰበው የሚነጣጠሉና ተቀናቃኝ እንዳይደሉ ለመገንዘብ ያስችላል። የሚል ተስፋ ስላለ ነው። በሌሎች የሩሂ ተቋም ትምህርቶች እንደሚደረገው በክፍሉ ውስጥ ብዙ ተማሪዎች ካሉ አስጠኚው በትንንሽ ቡድኖች ሊከፋፍላቸው ይገባል።

ከዚህ በፊት በነበሩት ክፍሎች አጫጭር ጥቅሶች ይሰጡና በመቀጠልም እነዚህን ጥቅሶች በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችና መልመጃዎች ይከተላሉ። በዚህ ክፍል ግን የጥልቀት ጭብጦቹ የተሰጡት በየመሃሉ ጥቅሶችን ባቀፉ ረዘም ባሉ ምንባቦች ነው። በአንድ ጭብጥ ላይ የተሰጠን ምንባብ ካነበቡ በኋላ አንዳንድ ተማሪዎች ጥቂት ነጥቦችን ብቻ ያስታውሱ ይሆናል። ስለዚህ እንደገና ተመልሰው ምንባቡን በሙሉ አንቀጽ በአንቀጽ እያነበቡ ጥያቄ እየተጠያየቁና የተካተቱትን ሐሳቦች በራሳቸው ቃላት እየገለጹ ማጥናት አለባቸው። ይህንን ካደረጉ በኋላ ጥቅሶቹን ይበልጥ በጥልቀት ለመረዳት እንዲችሉና ጥቅሶቹን ሌሎችን በማገልገል መንፈስ እንዴት ማካፈል እንደሚችሉ እንዲያስቡ ወደሚረዷቸው ቀጣይ መልመጃዎች ይሸጋገራሉ።

ተፈላጊዎቹን ችሎታዎችና ብቃቶች ለማዳበር በዚህ ክፍል የተካተቱ ጭብጦችን ማጥናትና ተዛማጅ መልመጃዎችን መስራት ብቻ በእርግጥ በቂ አይደለም። በተቻለ መጠን የተቀሰሙትን ችሎታዎች በተግባር ሊያውሉ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች ሊፈጠሩላቸው ይገባል። በግልም ሆነ በበድን ልምድ ካለው አማኝ ጋር በመሆን በቅርብ የሚገኙ ቤተሰቦችን ለዚሁ ዓላማ መጎብኘ ት አስፈላጊ ነው። ይህ ፍጹም የማይቻል ከሆነ ደግሞ አንዱ ጎብኚ አስተማሪ ሌሎቹ ደግሞ አዲስ እምነቱን የተቀበለ ቤተሰብ አባላት ሆኖ በመከፋፈል ጭውውቶችን በማቅረብ መለማመድ ይቻላል።

# የማስተማር ደስታ

**ዓላማ**

የማስተማር ደስታ የሚገኘው የአምላክን ቃል ከሰዎች ጋር ከመካፈል ተግባር ብቻ እንጂ በቅርብ ከሚገኝ ውጤት ጋር ያልተያያዘ እንደሆነ ለመረዳት።

## ምዕራፍ 1

እምነቱ ከእኛ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ስንመረምርና እነኚህንም እንዴት ለማሟላት እንደምንችል ስናሰላስል በአገልግሎት መንገድ በደስታና በመደነቅ እንደሚጓዝ ሰው አድርገን እራሳችንን ማሰቡ ይረዳናል። በዚህም መንገድ ስንጓዝ ከማይለካው የአምላክ በረከት ድርሻችንን እናገኛለን። ጥረቶቻችንም በማያቋርጥ መለኮታዊ ማረጋገጫዎች ይባረካሉ። በመጀመሪያ የምናበረክታቸው የአገልገሎት ተግባሮች ቀላልና ሳንቸገር የምንፈጽማቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እውቀታችን ባደገና አቅማችን በጨመረ ቁጥር ግን ፈታኝ በሆኑ የአገልግሎት መስኮች መሳተፍም እንጀምራለን። በአገልግሎት መንገድ መጓዝ በእርግጥ ብዙ ፈተናዎችንና ችግሮችን ያመጣል። ነገር ግን ከአምላክ ለተሰጠን የአገልግሎት እድል አመስጋኞች መሆን እንዳለብን ካስታወስን በአምላክና በፍጡሮች ፊት ራሳችንን ሁሉ የመጨረሻ ውጤት ለእምነቱ ትልቅም ይሁን ትንሽ ድልን ያጎናጽፋል።

በአገልግሎት መንገድ ስንጓዝ ከምናከናውናቸው እንቅስቃሴዎች መካከል አብዛኞቹ በማስተማር መስክ የሚደረጉ ናቸው። አዲስ ነፍሶችን ወደ እምነቱ እንመራለን፣ ሕጻናትን እናስተምራለን፣ ለባሃኢ ወንድሞቻችን የጥልቀት ትምህርት እንሰጣለን የአካባቢ ባሃኢ ማህበረሰቦችን በማጠናከሩ ሥራ ላይ እንሳተፋለን። በእነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች በባሃኦላህ የተገለጸውን የአምላክ ቃል ለሌሎች የማካፈልን ልዩ ፀጋ እንቋደሳለን። ይህም ቡራኬ ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ ደስታ ይሞላል።

### *መልመጃዎች*

1. እምነቱን ማስተማር ማለት አዲስ አማኞችን ማስገኘት ማለት ብቻ ነውን?____________
________________________________________
________________________________

2. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የግልጋሎት ማስኮች ውስጥ የማስተማር ተግባር ተብለው ሊቆጠሩ በሚችሉት ላይ ምልክት ያድርጉ።

____________ የባሃኦላህ መምጣትን የምስራች ለጓደኛ ማድረስ።
____________ አዲስ አማኝ በእምነቱ ጥልቀት እንዲያገኝ መርዳት።
____________ በቤትዎ የእሳት ዳር ትምህርት ማካሄድ።
____________ እምነቱን በማስፋፋትና ማጠናከር ዘመቻ ላይ መሳተፍ።
____________ ለጥቂት ሕፃናት የባሃኢ ትምህርት ክፍል ጊዜ መክፈት።
____________ አንድ ማህበረሰብ የአስራ ዘጠነኛ ቀን በዓል እንዲያከብር መርዳት።
____________ በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ተቋም ስለእምነቱ ንግግር ማድረግ።

3. ስናስተምር የምንቋደሰው ልዩ ፀጋ ምንድን ነው? ______________________
________________________________________
____________________________________

4. እምነቱን የሚያስተምሩ ሰዎች የሚያገኙት ጥልቅ መንፈሳዊ ደስታ ምንጩ ምንድን ነው? ____________________________________
________________________________________
________________________________

5. ባሃኢዎች የአምላክን እምነት እንዲያስተምሩ የሚያነሳሱዋቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ በቡድንዎ ተወያዩ።

6. የሚከተለውን ጥቅስ ቀቃልዎ ይያዙ፡-

“በአምላክ መንገድ ተጓዥ ሆይ! ከእርሱ የጸጋ ውቅያኖስ ድርሻህን ውሰድ በጥልቀቱም ውስጥ ተሸሽገው ከሚገኙት ነገሮች ራስህን አትንፈግ። ከዚያ ክብርና ሃብት ከተካፈሉትም ሁን። ከዚህ ውቅያኖስ አንድ የጤዛ ጠብታ በሰማያትና በመድር በሚገኙት ሁሉ ላይ ቢረጭ በፍጹም ኃያሉ በሁሉን አዋቂው በፍጹም ጠቢቡ አምላክ በረከት ሊያበለጽጋቸው ይችላል። ከሰው ሰራሽ ውስንነት ሁሉ እንዲነጹና የኃያሉ አምላክ መቀመጫ ወደሆነው ወደዚህ ወደተቀደሰውና አንጸባራቂ ወደሆነው ነጥብ እንዲቀርቡ በመላቀቅ እጆች ከሕይወት ሰጭ ውሃዎቹ ቀድተህ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ላይ አርከፍክፍ።”[1]

## ምዕራፍ 2

በሃኦላህ የተገለጸውን የአምላክ ቃል ከሌሎች ጋር መካፈል የከፍተኛ ደስታ ምንጭ እንደሆነ አውቀናል። ስለዚህም ስለበሃኦላህ ግልጸት ታላቅነት በየግላችን ማሰላሰልና በዚያም ውስጥ የሚገኙትን በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ እንቁዎች ለማግኘት መጣር ይኖርብናል። እስቲ ከበሃኦላህ ጽሁፎች የተገኘውን የሚከተለውን ጥቅስ በማጥናት እንጀምር።

“አገልጋዮቼ ሆይ! ቅዱሱና በመለኮታዊ ኃይል የታዘዘው ግልጸቴ፣ በጥልቀቱ ውስጥ ሊቆጠሩ የማይቻሉ ታላቅ ዋጋና የላቀ አንጸባራቂነት ያላቸው ዕንቁዎች በተደበቁበት ውቅያኖስ ሊመሰል ይችላል። ከፍለጋው ጉጉትና ከአደረጋቸው ጥረቶች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ በማይሻረውና በድብቁ የአምላክ መልእክቶች ውስጥ አስቀድሞ ከታዘዙት ጥቅሞች ይካፈል ዘንድ፣ ወደዚህ ውቅያኖስ ዳርቻዎች ለመድረስ ራሱን ማነሳሳትና ጥረት ማድረግ የእያንዳንዱ ተመራማሪ ተግባር ነው።”[2]

### *መልመጃዎች*

1. የባሃኦላህ ግልጸት በምን ሊመሰል ይችላል? ______________________________
______________________________________________
______________________________________________

2. በበሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ውስጥ ሊቆጠሩ የ____________________ እና ________ ______________________________ እንቁዎች ተደብቀው ይገኛሉ።

3. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ያሟሉ፡-

ሀ. ወደ በሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ______________________________ ለ____ ____________________ ራሳችንን ______________________ እና____ ____________________ ማድረግ____________________ የእያንደንዳችን ________________________ ነው።

ለ. ከፍለጋችን ______________________________ እና ከአደረግናቸው ____________________ ጋር ______________ ____________ በሆነ ሁኔታ፣ በማይሻረውና በድብቁ የአምላክ ጽላቶች ውስጥ አስቀድሞ ከታዘዙት ______________________ ______________________ ________ ዘንድ፣ ወደ በሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ______________________ __ ለመድረስ ____________ ማድረግ አለብን።

4. ራስን "ማነሳሳት" ማለት ምን ማለት ነው? ____________________

5. ወደ አንድ ነገር "ለመድረስ ጥረት ማድረግ" ማለት ምን ማለት ነው? ____________________

6. እያንዳንዱ ተመራማሪ ወዴት ለመድረስ ጥረት ማድረግ አለበት? ____________________

7. አንድ ነገር ከሌላው ነገር ጋር ተመጣጣኝ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? ____________________

የምናደርገውን ጥረት ያክል ከግልጸቱ ውቅያኖስ እንደምንጠቀም በሃኦላህ ይነግረናል።

ሀ. ይህንን ጥቅም ለማግኘት ልናደርጋቸው ከምንችላቸው ጥረቶች መካከል ጥቂት ምሳሌዎችን ይጥቀሱ ____________________

ለ. ልናገኛቸው ከምንችላቸው ጥቅሞች መካከል ጥቂት ምሳሌዎችን ይጥቀሱ። ____________________

## ምዕራፍ 3

የበሃኦላህ ግልጸት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እንቁዎች እንደሚገኙበት ውቅያኖስ ነው። ይህ ግልጸት ከሚሰጠን ጥቅም ለመጋራትና ሌሎችንም ወደዚህ ወቅያኖስ ለመምራት ሁላችንም የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለብን። የሆነው ሆኖ ይህ ውቅያኖስ ከእኛ ምን ያህል ይርቅ ይሆን? በሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

"አገልጋዮቼ ሆይ! አንዱና እውነተኛው አምላክ ምስክሬ ነው! ይህ እጅግ በጣም ታላቅ ይህ ለጥልቀቱ መጨረሻ የሌለውና የሚተምመው ውቅያኖስ ቅርብ በሚያስገርም ሁኔታ ቅርባችሁ ነው። ተመልከቱ ከሕይወት ደም ስራችሁ ይበልጥ ቅርባችሁ ነው! ብትፈልጉት እንደ ዓይን ጥቅሻ በሆነ ፍጥነት ልትደርሱበትና ከዚህ ከማይጠፋው ልግስና ከዚህ ከአምላክ ከተሰጠው ጸጋ፣ ከዚህ ከማይበላሽ ስጦታ፣ ከዚህ ከእጅግ በጣም ፍቱንና ሊነገር ከሚቻል በላይ ከሆነው ክቡር ችሮታ ለመካፈል ትችላላችሁ።"[3]

### *መልመጃዎች*

1. በሚከተለው አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎች ይሙሉ።

ሀ. የበሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ እጅግ በጣም ታላቅ ውቅያኖስ ቅርባችን ________________ ________________ ይበልጥ ቅርባችን ነው።

ለ. የባሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ ከሕይወት ደም ስራችን ________________ ________________ ነው።

ሐ. ብንፈልገው ልክ እንደ ________________ ፍጥነት ________________ እና ከእርሱ ግልጸት ወቅያኖስ ________________ እንችላለን።

መ. እኛ ________________ ልክ እንደ ዓይን ጥቅሻ በሆነ ፍጥነት ለመድረስና ከእርሱ ግልጸት ውቅያኖስ ለ________________እንችላለን።

2. "ይህ እጅግ ታላቅ ይህ ለጥልቀቱ መጨረሻ የሌለውና የሚተምመው ውቅያኖስ" የሚለው ሐረግ ምንን ነው የሚጠቅሰው? ________________________________________________

3. ይህ ውቅያኖስ ምን ያህል ቅርባችን ነው? ________________________________________________

4. በምን ያህል ፍጥነት ወደዚህ ውቅያኖስ እንደርሳለን? ________________________________________________

## ምዕራፍ 4

የባሃኦላህ ታላቅነት ካወቅንና ሊገመት የማይቻል ዋጋ ያላቸው እንቁዎች ለተሸከመው የእርሱ ግልጸት ውቅያኖስ ቅርብ መሆናችንን ከተነገዘብን በኋላ ነፍሳችንን በእምነት መንፈስ በመሙላት እነኚህን የመለኮታዊ መመሪያ እንቁዎች ለሌሎች ማካፈል ይኖርብናል። እነዚህ እንቁዎች ያለማቋረጥ የሚታፈሱት በጥናት፥ በጸሎትና በሱባኤ (ማሰላሰል) ነው። ይህንን ስናደርግ የእርሱን ቃላት ኃይል እንጠቀማለን።

በመሆኑም ስለአምላክ ቃል ኃይልና በሰው ልብ ላይ ስለሚኖረው ተጽእኖ በጥልቀት ማሰላሰል አስፈላጊ ነው።
የሚከተለው የባሃኦላህ ጥቅስ የዚህን ታላቅ ኃይል ምንነት እንድንገነዘብ ይረዳናል

"የአምላክ ቃል ሥሮቹ በሰዎች ልቦች ውስጥ በተተከለ ችግኝ ሊመሰል ይችላል። ሥሮቹ ጠንክረው ይይዙ ቅርንጫፎቹም እስከ ሰማይና ከዚያም አልፈው ይዘረጉ ዘንድ በጥበብ ሕያው ውሃ በተባረኩና በተቀደሱ ቃላት አማካይነት ዕድገቱን መንከባከብ አለባችሁ።"[4]

*መልመጃዎች*

1. **የአምላክ ቃል በምን ሊመሰል ይችላል? ______________________________**

2. **የአምላክ ቃል ዛፍ የሚተከለው በምን ላይ ነው? ______________________________**

3. **የዚህን ዛፍ እድገት ልናፋጥን የምንችለው እንዴት ነው? ______________________________**

4. **የአምላክ ቃል በልቦቻችን ላይ ጸንቶ ሲያርፍ ልናሳያቸው ከምንችላቸው ባህሪያት መካከል ጥቂቶቹን ይጥቀሱ ______________________________**

5. **"ቅርንጫፎቹም እስከ ሰማይና ከዚያም አልፈው ይዘረጉ ዘንድ" የሚለው ሐረግ ምን ያመለክታል? ______________________________**

6. **የአምላክን ቃል ለሌሎች ማካፈል ለምን እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በጥቂት አረፍተ ነገሮች ያስረዱ______________________________**

## ምዕራፍ 5

***እስቲ በእለት ኑሯችን የምንጠመድባቸውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እናስብ፣ እንመገባለን፣ ለእለት ጉርሳችን እንሰራለን፣ በእስፖርትና በተለያዩ መዝናኛዎች እንሳተፋለን፣ አዲስ እውቀት ለመገብየትና አእምሯችንን ለማበልጸግ እናጠናለን:: የኑሮ ደረጃችንን ለማሳደግ እንድንችል ሙያዎቻችንን እናሻሽላለን:: ለአእምሯችን እድገትና ለኑሯችን ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ተግባራት የጊዜያችንን አብዛኛውን ክፍል ይወስዱብናል:: ስንጸልይ የጥልቀት ትምህርት ስናካሂድ ስናስተምር ወ.ዘ.ተ ደግሞ በመንፈሳዊ ተግባራት እናሳልፋለን ማለት ነው:: ይሁንና በቁሳዊ ሕይወታችን ጉዳዮች የምናሳልፈው ጊዜና ከመንፈሳዊ ሕይወታችን ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የምናሳልፈውን ጊዜ አወዳድረን እናውቃለን? የእምነታችንን ጽሑፎች በግልም ሆነ በጋራ በማጥናት ሕጻናትን በማስተማር የአምላከ ቃል ዛፍ ስሮች በልቦቻችን ውስጥ እንዲሰርጹ በማድረግ ነፍሶችን ወደ በሃኦላህ ግልጸት ውቅያኖስ በማምጣትና በውስጡም የተደበቁትን እንቁዎች እንዲያገኙ በመርዳት የምናሳልፋቸው ጊዜያት ከመጠን በላይ ውድ አይደለምን? ይህንን መንግሥተ ሰማያዊ ፀጋ ከመቋደስ የበለጠ ደስታ ሊኖር ይችላልን? አብዶል በሃ ጉልበቱን ሁሉ በማስተማር ላይ ለማዋልና የአባቱን እምነት ወደ ሁሉም የዓለም ማእዘናት ለማድረስ በጣም ይመኝ እንደነበር ሁልጊዜ ማስታወስ ይኖርብናል::***

“አቤቱ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ሆኜም ብሆን፤ የምጓዘውም በእግሬ ቢሆን እንኳ፤ ወደ እነዚህ አካባቢዎች ለመጓዝ ብችልና በከተሞች፥ በመንደሮች፥ በተራሮች፥ በበረሃዎች እና በውቅያኖሶች 'ያ ባሃኦላህ አብሃ' የሚለውን ጥሪ በማሰማት ምነው መለኮታዊ ትምህርቶችን ለማስፋፋት ብችል ኖሮ! ግን በጣም ያሳዝናል፤ ይህን ለማድረግ አልችልም። ምንኛ በጥቅል አዝንበታለሁ! እናንተ እንድትፈጽሙት እግዚአብሔር ፈቃዱ ይሁን።”[5]

***መልመጃዎች***

**1.** ***ወደድንም ጠላንም በሕይወታችን ውስጥ ማከናወን ከሚገቡን ገነሮች መካከል ጥቂቶቹን ይዘረዝሩ፡-*** ________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________

**2.** ***በወዴታ ማከናወን የሚፈልጓቸውን ነገሮች ከሚሰጥዎ ደስታ አኳያ በመመዘን ደረጃ በመስጠት ይዘርዝሩ፡-*** ________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_______________________________________________

**3.** ***መቼም ማከናወን የሚፈልጓቸው ነገሮች ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጠቃሚ ናቸው ከእነዚህ ተግባሮች የሚያገኟቸው ደስታዎች የሚመነጩት ድርጊቱን ከማከናወኑ ነው ወይስ ድርጊቱ ከሚያመጣው ወጤት?*** ________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______

## ***ምዕራፍ 6***

***በሕይወታችን ከምናከናውናቸው ተግባራት ሁሉ የአምላክን ቃል ከሌሎች ጋር በመካፈል የምናሳልፋቸው ጊዜያት በልዩ ፀጋ የተሞሉ እንደሆኑ ተስማምተናል። ይሁንና ስናስተምር የሚሰማን ደስታ ከማስተሩ ተግባር ማለትም በአምላክ ቃል ላይ ከመወያየት ወይም ከማሰላሰል ብቻ የሚመነጭ እንደሆነ ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን። ይህንን ስንዘነጋ ሌሎች አፍራሽ ሐሳቦች በልባችን ያለውን የደስታ ብርሃን እንዲቀንሱብን ብሎም እንዲያጠፉብን እንፈቅዳለን ሌሎች ስለእምነቱ ትምህርቶች ለሚኖራቸው ምላሽ ከፍተኛ ቦታ ከሰጠነው በሌሎች ሰዎች ሂስ በጣም የምንነካ ከሆነና ለተግባራችን ምስጋናን ከጠበቅን የማስተማር ደስታን አናገኝም። እንድናስተምር የሚያነሳሳን የአምላክ ፍቅር ሊሆን ይገባል እንጂ ለውጤት መጓጓት፥ ጥቅም ለመግኘት፥ ታዋቂነትን ለማትረፍ ወይም ለመመስገን መሆን የለበትም። በማስተማር ደስታን ለማግኘት ከእነዚህ ሁሉ መላቀቅ ወሳኝ ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ማጥናት በዚህ መሠረታዊ ነጥብ ላይ ለማሰላሰል ይረዳናል።***

***“ባለሁለት ዓይን ሰው ሆይ! አንዱን ዓይን ጨፍነህ ሌላውን ግለጥ። አንደኛውን ለዓለምና በወስጧም ላሉት ሁሉ ጨፍነህ፤ ሌላውን ለተወዳጁ የተቀደሰ ውበት ግለጥ።”[6]***

"ወዳጆች ሆይ! ዘለዓለማዊውን ውበት፣ መጥፋት ባለበት ውበት አትለውጡ፣ ፍቅራችሁንም በዚህ ጠፊ የትቢያ ዓለም ላይ አታኑሩ::"[7]

"የልሳን ልጅ ሆይ! ፊትህን ወደኔ መልስ፣ ከእኔም በስተቀር ሁሉንም ተው ሉዓላዊነቴ ዘለዓለማዊ ግዛቴም አይጠፋምና:: አዎን ከእኔ በስተቀር ሌላ ብትሻ እስከ ዘለዓለምም ፍጥረተ ዓለማትን ብታዳርስ እንኳ ፍለጋህ ሁሉ ከንቱ ይሆናል::"[8]

"የተወዳጀሁህ እንግዳ ሆይ! የልብህ ሻማ በኃይሌ እጅ በርቷል በእኔነትና በመድራዊ ስሜት ተፃራሪ ነፍሶች አታጥፋው:: የሕመምህ ሁሉ ፈውስ እኔን ማስታወስ ነው:: አትርሳው:: ፍቅሬን ሀብትህ አድርጋት ልክ እንደ ዓይንህ ብረሃንና እንደ ሕይወትህ አጥብቀህ ተንከባከባት::"[9]

"መላቀቅ እንደ ፀሐይ ነው፣ በሚያበራበት በማንኛውም ልብ ውስጥ ስግብግብነትና የራስ ወዳድነትን እሳት ያጠፋል:: እርሱ ዓይኑ በመገንዘብ ብርሃን የበራ በእርግጥ ከዓለምና ከከንቱዎችዋ ራሱን ያላቅቃል... ዓለምና የእርሷ ክፋት አያሳዝናችሁ:: እርሱ ሀብት በከንቱ ክብር የማይሞላው፣ ድህነትም የማያሳዝነው ደስተኛ ነው::"[10]

***መልመጃዎች***

**1.** ከዚህ ዓለም መላቀቅ ማለት እንደባህታዊ መኖር ማለት ነውን? ____________________

**2.** ሀብታም ሰው ከዚህ ዓለም የተላቀቀ ነውን?____________________

**3.** እያንዳንዱን የሕይወቱን ደቂቃ ለስራው የሰጠ ሰው ከዚህ ዓለም ነገሮች የተላቀቀ ሊሆን ይችላልን? ____________________

**4.** ለእለት ጉርሱ የሚበቃውን ያክል ብቻ ሰርቶ ቀሪ ጊዜውን ያለምንም ስራ የሚያሳልፍ ሰው ከዚህ ዓለም የተላቀቀ ነውን? ____________________

**5.** ከቁሳዊ ነገሮች ሌላ መላቀቅ የሚገቡን ብዙ ነገሮች አሉ

*ሀ.* ለእምነቱ ስለሰጠው አገልግሎት ማንም እውቅና ካልተሰጠው የሚከፋ ሰው ከምን መላቀቅ አለበት?____________________

ለ. እምነቱን ሲያስተምር ሰዎች ባይቀበሉት ሞራሉ የሚነካ ከምን መላቀቅ አለበት? __________

*ሐ. ጓደኛው በመኪና ካልወሰደው በቀር ወደ ገጠር ለማስተር የማይሄድ ከምን መላቀቅ አለበት?* ____________________

____________________

*መ. የሚያሾፉበት ከመሰለው ባሃኢ መሆኑን ለሰዎች የማይናገር ከምን መላቀቅ አለበት?* ____________________

____________________

*ሠ. ለመዝናኛና ለሽርሽር ብዙ ገንዘብ የሚያወጣ ነገር ግን በባሃኢ ስብሰባ ለመካፈል የመጓጓዣ ገንዘብ የማይኖረው ከምን መላቀቅ አለበት?* ____________________

____________________

*6. ለእምነቱ አገልግሎት ስንሰጥ ምስጋና በመሻት መሆን እንደሌለበት ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የማስተማር ልምዳችንን ከሌሎች ጋር መካፈል አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን በመናደርግበት ጊዜ ግን ስላከናወናቸው ተግባሮች ጉራ መንዛት የለብንም፡፡ ከዚህ በታች ያሉት ዓረፍተነገሮች አንድ ሰው በአንድ የማስተማር ዘመቻ ላይ ከተካፈለ በኋላ ሊላቸው የሚችላቸው አነጋገሮች ናቸው፡፡ የጨዋነትን ገደብ ሳያልፉ ሊባሉ የሚችሉትን ለይተው ምልክት ያድርጉባቸው፡፡*

*_______ በማስተማር ዘመቻ እጅግ ብዙ ልምድ ያካበትኩ በመሆኔ 15 ወይም 20 አዲስ አማኞችን በአንድ ቀን ማስመዝገብ ለእኔ ቀላል ነው፡፡*

*_______ እጅግ ጥልቅ የመረዳት ችሎታ ካላት ሴት ጋር ዛሬ ተዋወቅሁ፡፡ በትንሽ ማብራሪያም እምነቱን ተቀበለች፡፡ ብዙ ጊዜያችንን ያሳለፍነው ስለባሃኦላህ ግልጸት እውነተኛነት ማረጋገጫ ስሰጣት ሳይሆን የጥልቀት ጥናት ስናደርግ ነው፡፡*

*_______መቅደስ እጅግ ጎበዝ ተማሪ ወጥቷታል፡፡ እምነቱን በሚገባ ያስተማርኳት እኔ ነኝ፡፡*

*_________እኔ በማስተማሩ ዘመቻ ላይ ባልሳተፍ እጅግ ብዙ አማኞችን ማስመዝገብ እንደማይችሉ ስላወቅሁ ከስራዬ ፈቃድ ወስጄ በዘመቻው ላይ ተሳተፍኩ፡፡*

*_______ባለፈው ሳምንት አስተምረነው እምነቱን የተቀበለው መኮንን ቤተሰቡን ሲያስተምር አይቼው ልቤ በደስታ ተሞላ፡፡*

*_______ሰዎች እምነቱን አልቀበልም ሊሉ የማይችሉበትን የማስተማር ዘዴ በመጨረሻ ደረስኩበት፡፡*

*_______ለአዛውንቱ ባልና ሚስት ገና እምነቱን መንገር ስጀምር ባልየው ተነስተው በቀደመው ሳምንት መጀመሪያ ላይ የእግዚአብሔርን መልእክት ይዞላቸው ስለሚመጣ ሰው ያለሙትን ሕልም ተናገሩ፡፡ ይህንን ሳስታውስ በስሜት እዋጣለሁ፡፡*

*7. መላቀቅ እምነቱን ለማስተማር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ያሉትን ጥቅሶች ሁሉ በቃልዎ ቢይዟቸው መልካም ነው፡፡*

## *ምዕራፍ 7*

*በእምነቱ አገልግሎት ሐሴት ማግኘታችንን እንድንቀጥል የሚረዳን ሌላው አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ጥረት የማድረግና በስዋዕት የመክፈል ፈቃደኝነታችን ነው፡፡ በዕለታዊ ጉሮአችን “መስዋዕት” የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ እንጠቀማለን፡፡ መልካም ወዳጃችን በንጋት ላይ ለጉዞ የሚነሳ ከሆነ እርሱን ለመሸኘት በማለዳ እንነሳለን፡፡ ከእንቅልችን ጥቂት ሰዓታት መስዋእት*

አደረግንም እንላለን፡፡ በጣም ውድ ወዳጃችን የሆነ ታሞ ይሆናል፣ እርሱን ለማስታመም በጣም ከምንወደው የጊዜ ማሳለፊያችን ጥቂት ሰዓታት መስዋዕት እናደርጋለን፡፡ ትምህርት ቤት ለመሄድ ረዥም ጉዞ ስንጓዝ ምቾታችንን መስዋዕት አደረግን ወይም ለአንድ ቁም ነገር ዓላማ ገንዘብ ብናዋጣ ገንዘባችንን መስዋዕት አደረግን እንላለን፡፡

ለእምነቱ አገልግሎት መስጠትም መስዋዕት መክፈልን ያስከትላል፡፡ የባሃኢ እንቅስቃሴ ላይ ለመገኘት ከሌሎች ነገሮች ላይ ጊዜን መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ድካምን ወይም መጉላላትን መቀበል አንዳንድ ቁሳዊ ሃብታችንን ማውጣት ወይም መስጠት እንዲያውም አልፎ ተርፎ አንዳንድ ምኞቶቻችንንና ዕቅዳችንን መሰረዝ ይኖርብን ይሆናል፡፡ ሆኖም እነዚህን ሁሉ በማድረግ መንፈሳዊ ደስታን እያገኘን መሆናችንንና መንፈሳዊ እድገታችንን ወደፊት ማራመዳችን መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡ እምነቱን በምናገለግልበት ጊዜ ለአምላክ ውለታ መዋላችን ነው ብሎ ከማሰብ እግዚአብሔር ይጠብቀን፡፡ አገልግሎት የመስጠት ዕድል የሰጠን አምላክ ነው በምናገለግልበት ጊዜ በትህትናና በአመስጋኝነት ስሜት መሞላት አለብን፡፡

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

"እርሱን ለመሻት ከፈለግን ጥረት ያስፈልጋል፣ ከእርሱ ጋር የመገናኘት ማር ለመጠጣት ከፈለግን፥ ጽኑ ፍላጎት ያስፈልጋል፥ ከዚህ ጽዋ ብንቀምስ፥ ዓለምን እርግፍ አድርገን እንተዋለን፡፡"[11]

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፡-

"አትረፉ፥ ምንም እርጋታ አትፈልጉ፥ ራሳችሁን ከዚህ በቅጽበት አላፊ ከሆነው ዓለም የቅንጦት ነገሮች ጋር አታጣብቁ፥ ራሳችሁን ከእያንደንዱ ቁራኛነት ነፃ አውጡ፥ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተደላደላችሁ ለመሆን በሙሉ ልባችሁና በሙሉ ነፍሳችሁ ጥረት አድርጉ፡፡ የመንግሥተ ሰማይን የከበረ ሀብት አትርፉ፡፡ ዕለት ተዕለት ይበልጥ የምታንጸባርቁ ሁኑ፡፡ ወደ አንድነት ደጀሰላም ያለማቋረጥ ይበልጥ እየቀረባችሁ ሂዱ፡፡"[12]

እውነተኛ መስዋዕትነት ከፍተኛውን ለማግኘት ከዝቅተኛው መገለል ነው፡፡ ምንም እንኳ መስዋእትነት ችግርን የሚያስከትል ቢመስልም በእውነቱ የደስታ ምንጭ ነው፡፡

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፡-

"አንድ ፍጡር እግሩን በመስዋዕትነት ዓለም ውስጥ እስካላሳረፈ ድረስ ከእያንዳንዱ ችሮታና ጸጋ የተነፈገ ነው፣ ይህም የመስዋዕትነት ዓለም፥ የሕያው ብረሃን ይበራ ዘንድ፥ ከራስ ወደድነት የመሞት ዓለም ነው፡፡"[13]

### *መልመጃዎች*

1. አንድ ህፃን በኪሱ ሙሉ ድንጋይ ይዟል፡፡ በእጁ ሙሉ እንቁ የሚሰጠው ሰው አጋጠመው፡፡ ሆኖም እንቁዎቹን ተቀብሎ በኪሱ ለመክተት ድንጋዮቹን አውጥቶ መጣል አለበት፡፡ ይህ ልጅ መስዋዕት ሊያደርግ የሚገባው ምንድን ነው? ____________________

2. አንድ ገበሬ አንድ ማሳ ሙሉ ፍሬ የማይሰጡ ያረጁ ዛፎች አሉት፡፡ አዲስ ዛፎችን ለመትከል ከፈለገ እነዚህን ዛፎች መቁረጥ ይኖርበታል፡፡ መስዋዕት የሚያደርገው

ምንድን ነው? ______________________________________________
______________________________________________________
____________________

3. አንዷት የዘር ፍሬ ማቆጥቆጥ ስትጀምር ትበሰብሳለች፡፡ እራሷንም መስዋዕት አደረገች ይባላል፡፡ እራሷን መስዋዕት የምታደርገው ለምንድን ነው?____________________
______________________________________________________
______________________________________________________
______________________________________________________
_________________________

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች አንድ ሰው ሊያስባቸው ወይም ሊናገራቸው የሚችለው ናቸው፡፡ ከተሰጡት ጥንድ አረፍተ ነገሮች ውስጥ መልካም አመለካከት ያለው ሰው ሊናገራቸው የሚችላቸው ላይ ምልክት ያድርጉ፡-

ሀ.__________ በማስተማር ጉዞ ለመካፈል ስል አንድ ቀን ሙሉ መስዋዕት አደረግሁ፡፡

__________ ቀኑን ሙሉ የማስተማር ደስታና እድል አግኝቼ ነበር፡፡

ለ.__________በአስራዘጠነኛ ቀን በዓል ለመገኘት ስል ሶስት የጥናት ሰዓቶችን መስዋዕት አደረግሁ፡፡

__________ዛሬ በአስራዘጠኛ ቀን በዓል ላይ ስለምገኝ ሰአቴን ለማካካስ ስል አርፍጄ እተኛ ለሁ፡፡

ሐ.__________ተጨማሪ ጫማ የምገዛበትን ገንዘብ ለመዋጮ መስዋዕት አደርጋለሁ፡፡

__________ለጫማ መግዣ ያጠራቀምኩትን ገንዘብ ለእምነቱ መዋጮ እሰጣለሁ፡፡ ግን በምንም ዓይነት ይህንን ለሌላ ለማንም አልናገርም፡፡

መ.__________ዛሬ ለእምነቱ በጣም ብዙ ስሰራ ስለነበር ምሳዬን መስዋዕት አደረግሁ፡፡ ምንም እንኳ ቢርበኝም የበላሁት ቁራሽ ዳቦ ብቻ ነበር፡፡

__________ሐሳቤ በሙሉ በእምነቱ ስራ ላይ ስለነበር ምንም እንኳን ቢርበኝም ቁራሽ ዳቦ በቅቶኝ ነበር፡፡

5. ዓላማችንን ለማሳካት ከፈለግን ጥረት ግድ ነው፡፡

ከዚህ በታች የአንድ ባሃኢ ማህበረሰብ ግቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በእያንዳንዱ ግብ ስር የተለያዩ የጥረት ደረጃን የሚሹ ተዛማጅ እንቅስቃሴዎች ተዘርዝረዋል፡፡ የተሰጠውን ግብ ለመምታት የሚያስፈልገውን ጥረት በሚያንጸባርቁ እንቅስቃሴዎች ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡

የሕፃናት መንፈሳዊ ትምህርት

______ በዓመት አንድ ጊዜ የህፃናት ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፡፡

________ጎብኚ አስተማሪ በመጣ ጊዜ የመንደሩን ህፃናት ለግማሽ ሰዓት ማሰባሰብ፡፡

________የተለያዩ ዕድሜ ላላቸው ህፃናት ቋሚ የህፃናት ትምህርት እንዲያካሂዱ የመንደሩን ወጣቶች በዓመት አንድ ጊዜ ስልጠና መስጠት፡፡

የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ማጠናከር

__________መንፈሳዊ ጉባኤዎችን እንዲመርጡ ለመርዳት የአካባቢ ማኅበረሰቦችን በዓመት አንድ ጊዜ በሪዝቫን መጎብኘት።

__________ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባሮችን ያዘለ ዝርዝር ለአካባቢ መንፈሳዊ ጉባኤዎች መስጠት።

__________እያንዳንዱ የአካባቢ ማኅበረሰብና መንፈሳዊ ጉባኤዎች እንዲጠናከሩ በቅርብ መከታተል የአስራ ዘጠነኛ ቀን በዓልን በማክበር፥ የህፃናት ትምህርት በማካሄድ የአካባቢ መዋጮ በመጀመርና የአካባቢ የማስተማር እቅዶችን በመተግበር መስኮች መርዳት።

ብዛት ያላቸውን አማኞችን ማጥለቅ

__________የተቋማቱ አባላትና ልምድ ያላቸው አማኞች ንግግር የሚያደርጉበት ኮንፈረንስ በየጥቂቱ ወራት ማዘጋጀት።

__________አማኞች ቅዱሳን ጽሁፎችን እንዲያጠኑ በተገኘው አጋጣሚ ማስታወስ።

__________አማኞችን ለማጥለቅ ስልት ያለው ኘሮግራም መቀየስ። ለዚህም የጥልቀት ትምህርት የሚያስፈልጉ መማሪያዎችን ማዘጋጀትና እነዚህን መማሪያዎች በብቃት ለመጠቀም የሚችሉ የሰለጠኑ አስተማሪዎችን ማፍራት።

በግል በማስተማር ግለሰቦች እምነቱን እንዲቀበሉ ማድረግ

__________ለእምነቱ ፍላጎት ለሚያሳይ ሰው ብዙ የሚነበቡ ጽሑፎችን መሰጠት።

__________ለአንድ ሰው ስለእምነቱ እውነታዎች በታላቅ ስሜት ማስረዳት እና እንደተቀበለ ከፈለገ ማጥናቱን እንዲቀጥል ለራሱ መተው።

__________ስለእምነቱ ለማወቅ ስለፈለገው ሰው ሁኔታ ማወቅ በምን ዓይነት ስልት ስለእምነቱ ቢገልጽለት እንደሚሻል ማሰብና መወሰን ብዙ ደግነት ለእርሱ ማሳየት እርሱን መንከባከብና በባሃኦላህ ማመኑን እንዲገልጽ መርዳትና ራሱ ሌሎችን ነፍሶች ለማስተማር ወደሚነሣበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ማጥለቅና መርዳት።

## ምዕራፍ 8

ከዚህ በታች ገንቢ እና አፍራሽ በሚል ርዕስ ጭውውቶች ተዘርዝረዋል። አንድ ጓደኛ ይምረጡና ጭውውቶቹን ያጥኑ። የ"ገንቢ" እና የ"አፍራሽ" አነጋገሮችን በየተራ እየቀያየራችሁ በቡድናችሁ ፊት ተጨዋወቱ። በተሰጡትም ምሳሌዎች ብቻ ሳትወሰኑ በመመካከር ተጨማሪ ሁኔታዎችን የሚወክሉ ተመሳሳይ ጭውውቶችን እየፃፋችሁ ተጫወቷቸው:-

ገንቢ:- እኔ ባሃኢ ነኝ የባሃኦላህን መልእክት ከሌሎች ጋር መካፈል ትልቅ ደስታን ይሰጠኛል። እምነቱን ባስተማርኩ ቁጥር ልቤ በደስታ ይሞላል።

አፍራሽ:-እኔ ባሃኢ ነኝ እምነቱንም ማስተማር በእውነቱ ያስደስተኛል። ነገር ግን በጣም አስቸጋሪ ነው። የትምህርት ኮሚቴው እንዳስተምር ወደጠየቀኝ መንደር ለመሄድ በጧት መነሳት አለብኝ።

ገንቢ:- ህፃናትን ማስተማር በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንንም ማድረግ በጣም ያስደስተኛል። በማስተምርባቸው መንደሮች ውስጥ ያሉ ህፃናት በጣም ልዩ ናቸው። በጣም የቅርብ ጓደኞቼ አድርጌም እቆጥራቸዋለሁ።

አፍራሽ:-ህፃናትን ማስተማር በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ለእኔ ግን ይህ የማይቻል ነገር ነው:: የዛሬ ጊዜ ልጆች ባህሪያቸው የተበላሸ ከመሆኑ የተነሳ ማንም ከእነርሱ ጋር ለጥቂት ጊዜ እንኳን መቆየት አይችልም::

ገንቢ:-በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ያለ ሳምንታዊ የህፃናት ትምህርት አለኝ:: የማስተምራቸው ህፃናት ቅዱስ ናቸው:: ማለት አልችልም:: በማስተምራቸው ጊዜ አልፎ አልፎ ችግሮች ይፈጠራሉ:: ይሁንና የበሃኦላህንና የአብዶል በሃን ምክሮች በመከተል በፍቅርና በትእግስት ሁሉንም ነገር ይስተካከላል:: ባስተማርኩበት አመት እነዚህ ህፃናት ያሳዩትን እድገት መመልከት እንዴት ያስደስታል::

አፍራሽ:-በእርግጥ ማድረግ ከሚገቡኝ ነገሮች አንዱ ህፃናትን ማስተማር ነው:: ግን አይገባቸውም:: ስጀምር ሰላሳ ህፃናት ነበሩ:: ወዲያው ሃያ ብቻ ቀሩ:: አሁን የሚመጡት አምስት ብቻ ናቸው:: በተመቸኝ ጊዜ አልፎ አልፎ ከማስተምራቸው ነገሮች እነዚህ አምስት ህፃናት ምን ሊጠቀሙ ይችላሉ?

ገንቢ:-በቀደም የዜና መጽሔት ለመስጠት ወደ አንድ የባሃኢ ቤተሰብ ሄጄ ነበር:: እነርሱን በቤታቸው አላገኘኋቸውም:: ይሁንና ከዚህ በፊት የማላውቀው አንድ ዘመዳቸውን አገኘ ሁት:: ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም እምነቱን አስተማርኩት:: እርሱም እምነቱን ተቀበለ::

አፍራሽ:-በቀደም የዜና መጽሔት ለመስጠት ወደ አንድ የባሃኢ ቤተሰብ ሄጄ ነበር:: ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው አንድ ዘመዳቸው እቤት እንደሌሉ ነገረኝ:: በልፋቴ በጣም ተናድጄ ተመለስኩ::

ገንቢ:-በዚህ አካባቢ ሰዎችን በተከታታይ ማሰባሰብ ያስቸግራል:: ነገር ግን ጽናት ካለ የማይቻል ነገር አይደለም:: ከአንድ ዓመት በፊት በማኅበረሰባችን የእሮብ ማታ የጥልቀት ትምህርት ጀምረን ነበር:: ስንጀምር ሁለት ሰዎች ብቻ መጡ:: ነገር ግን ተስፋ አልቆረጥንም:: በማይመጡት አማኞች ላይም መጥፎ አመለካከት አልነበረንም:: ይልቁንም እነርሱን መጎብኘትና እሮብ ማታ ምን እንደተማርን ለእነርሱ ማካፈልን ቀጠልን:: ባለፉት ጥቂት ወራት አስር ባሃኢዎች በቋሚነት ትምህርቱን መካፈል ጀመረዋል:: ቁጥሩ አሁንም እየጨመረ ነው::

አፍራሽ:-ተመልከቱ! አማኞቹ ወደ ስብሰባዎች አይመጡም! አይገኙም! ታዲያ ምን ተስፋ አለ! ምንም ማድረግ አይቻልም::

## ምዕራፍ 9

በባሃኦላህ ግልጸት ታላቅነት ላይ አሰላስለናል:: የእርሱንም ቃል ለሌሎች ማካፈል ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነም ተመልክተናል:: የማስተማር ደስታ የእርሱን ቃል ከማካፈሉ ተግባር ብቻ የሚመነጭ መሆኑንም ሙሉ በሙሉ ተረድተናል:: ይህንን ደስታ ለመጠበቅም ከዚህ ዓለም ነገሮች ምስጋናንና ታዋቂነትን ከመሻት ለመላቀቅና በፈቃደኝነት መስዋዕትነትን ለመክፈል እንድንችል ጥረት ማድረግ ይኖርብናል::

ከዚህ በታች በሚገኙት ጥቅሶች አማካኝነት ባሃኦላህ ነፍሶችን ለመምራት እንድንነሳሳ ይነግረናል:: ይህንን ካደረግን መለኮታዊ ቡራኬ በእኛ ላይ እንደሚወርድና እንደሚረዳን ያረጋግጥልናል:: በማይነጥፈው የበሃኦላህ እርዳታ በመተማመን ራሳችንን ከሁሉም ነገሮች ማላቀቅ ሳንገታም እንደንፋስ የእርሱን ግልጸት የምስራች በሁሉም አቅጣጫ ማሰራጨት ይኖርብናል::

ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥቅሶች በቃልዎ በመያዝ ይህንን ትምህርት ቢጨርሱ መልካም ይመስለናል፡-

“ምናልባት ጎረቤትህን ወደ እጅግ በጣም ምህረተኛው አምላክ ሕግ ትመራ ዘንድ፥ የጥረትህን ሽንጥ አጥብቅ፡፡ በእውነት፥ እንዲህ ያለው ተግባር፥ የሁሉ ባለቤት በሆነው በእጅግ በጣም ከፍተኛው አምላክ ዓይን ከሌሎች ተግባራት ሁሉ ይበልጣል፡፡”[14]

“በአምላክ ትክክለኝነት! በዚህ ቀን አፉን ከፍቶ የጌታውን ስም ለሚያነሳው ለምንም ሰው የመለኮታዊ መነቃቃት ሠራዊት ከሁሉን አዋቂው ከፍጹም ጠቢቡ ሰማይ ይወርዱለታል፡፡”[15]

“እምነታችንን ለማስተማር የሚነሳ ማንኛውም ሰው ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ ራሱን ማላቀቅና ሁል ጊዜ የእምነታችንን ድል እንደ ላቀ ግቡ መቁጠር አለበት፡፡”[16]

“የእርሱን የመለኮታዊ መርሖ ጎህ እንዲቀድ ያደረገውን መልእክት በምታስተላልፍበት ጊዜ እንደ ነፋስ ያልተገታህ ሁን፡፡”[17]

“ድል ሲገኝ እያንዳንዱ ሰው አማኝ ነኝ ይላል፡፡ ወደ አምላክ እምነት መጠለያም ይሮጣል፡፡ እነዚያ ዓለምን በከበቡት ፈተናዎች ቀናት በእምነቱ በጽናት የቆሙትና ከእውነቱ አንዣነፍም ያሉት ደስተኞች ናቸው፡፡”[18]

“የሕያው ልጅ ሆይ! በሰማዬ አስታውስህ ዘንድ በምድሬ ስሜን ተዘከር የእኔ ዓይኖችና የአንተ የሚጽናኑት በዚህ መንገድ ነውና፡፡”[19]

## የጥቅሶች ማመሳከሪያ


1. ከባሃኦላህ ጽሁፎች ቅስማት ቁ 129 ገጽ 279-80
2. ከላይ ከተጠቀሰው ቁ 153 ገጽ 326
3. ከላይ ከተጠቀሰው ቁ 153 ገጽ 326
4. ከላይ ከተጠቀሰው ቁ 43 ገጽ 97
5. አብዶል በሃ የመለኮታዊ እቅድ ዕላቶች ገጽ 41-42
6. በሃኦላህ ህቡዓተ ቃላት ፋርስኛው ቁ 12
7. ከላይ ከተጠቀሰው  ፋርስኛ ቁ 14
8. ከላይ ከተጠቀሰው አረብኛ ቁ 15
9. ከላይ ከተጠቀሰው ፋርስኛ ቁ 32
10. ባሃኦላህ የባሃኢ ዓለም ቅጽ 1 ገጽ 42
11. ባሃኦላህ ሰባቱ ሸለቆዎችና አራቱ ሸለቆዎች ገጽ 7
12. አብዶል በሃ የመለኮታዊ እቅድ ጽላቶች ገጽ 87
13. አብዶል በሃ ጽሁፎች ተዋጽኦዎች ቁ 36 ገጽ 79
14. ከባሃኦላህ ጽሁፎች ቅስማት ቁ 161 ገጽ 339
15. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 129 ገጽ 280
16. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 147 ገጽ 334
17. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 161 ገጽ 339
18. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 150 ገጽ 319
19. በሃኦላህ ህቡዓተ ቃላት አረብኛ ቁጥር 43

# የጥልቀት ትምህርት ጭብጦች

## ዓላማ

*አዲስ አማኞችን በየጊዜው ቤታቸው ድረስ በመሄድ በዛ ያሉ የጥልቀት ትምህርት ጭብጦችን የማካፈልን ችሎታ ለማዳበር::*

## ልምምድ

ጥቂት ቤተሰቦችን በመጎብኘት በዚህ ክፍል ከቀረቡት ቢያንስ የመጀመሪያዎቹን ሶስት ጭብጦች ከእነርሱ ጋር ያጥኑ::

## ምዕራፍ 1

የአገልግሎት ጎዳና ሲጓዙ ሊሳተፉባቸው ከሚችሉ ቀላል የአገልግሎት መስኮች አንዱ አዲስ አማኞችን መጎብኘትና ከእነርሱም ጋር በመሆን ስለእምነቱ የጥልቀት ትምህርት ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያለው ትምህርት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ባሃኢዎች ልምድ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሐሳብዎን ለማቀናጀትና ይህንን የተመሰገነ አገልግሎት እንዴት ለመወጣት እንዲችሉ ለመወሰን እንዲችሉ ይረዳዎታል፡፡

በጣም ውጤታማ በሆነ የማስተማር ዘመቻ ተካፍለው አሁን መመለስዎ ነው ብለን እስቲ እናስብ፡፡ ዘመቻውን ያስተባበረው እርስዎ የሚገኙበት የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባኤ ነበር፡፡ በቀጠናው የትምህርት ኮሚቴ እርዳታም ጥቂት ልምድ ያላቸው አስተማሪዎች በዚህ ዘመቻ እንዲካፈሉ ከጎረቤት የባሃኢ ማኅበረሰቦች ተጋብዘው ተገኝተዋል፡፡ የእነርሱ መገኘት እምነቱን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ለምታደርጉት ጥረት ጥሩ እገዛ ሰጥቷችኋል፡፡ ምንም እንኳን ለብዙ ቀናት ያለማቋረጥ ባደረጉት እንቅስቃሴ ምክንያት የአካል ድካም ቢሰማዎትም አእምሮዎ ግን በጣም ንቁ ሲሆን ደስታም ተሰምቶዎታል፡፡ ልምድ ካላቸው አስተማሪዎች ጋር በመሆን ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ባቀፈው በዚህ ዘመቻ በመካፈልዎ የተሰማዎትን ደስታ በሚገባ ያስታውሱታል፡፡ ዘመቻው ከተካሄደበት ኅብረተሰብ ባለሥልጣናት ጋር ወደጅነት ለመፍጠርና ለእምነቱ ቀና አመለካከት እንደኖራቸው ለመርዳት የተደረጉ ጉብኝቶች በአካባቢው የሚገኙ ቤተሰቦችን ለማስተማርና የጥልቀት ትምህርት ለመስጠት የተደረጉ ጉብኝቶች በአካባቢው የሚገኝ ፡ ቤተሰቦችን ለማስተማርና የጥልቀት ትምህርት ለመስጠት የተደረጉ ጉብኝቶች ልጅነትን የሚያስመኙ የልጆች ትምህርት ዝግጅቶች ነፍሳትን ከፍ ወዳለ መንፈሳዊነት ያነሳሉ የማኅበረሰቡ ስብሰባዎች በዘመቻው የተካፈሉ አስተማሪዎች ያደረጓቸውና እርስዎም የተሳተፉባቸው የጥልቀት ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ሁሉ ትዝ ይልዎታል፡፡ መንፈሳዊ ጉባኤው ከዘመቻው ተሳታፊዎች ጋር በመሰብሰብ ፍቅር የተሞላበትና ጥልቅ መመሪያዎችን የሰጠባቸው ጊዜ ጥልቅ ትዝታ አሁንም ከእርስዎ ጋር ነው፡፡

ለሰላሳ ቀናት የቆየው ዘመቻ ያፈራቸውን ብዛት ያላቸው አማኞች እንዴት ማጥለቅ ይቻላል የሚለው ሐሳብ አሁን አእምሮዎን በጣም አስጨንቆታል፡፡ አዲስ አማኞችን ቤታቸው ድረስ ሄዶ በማጥለቅ ወደጅነትን የማጠናከርና በእምነቱ ጥልቀት እንዲያገኙ የመርዳት አስፈላጊነትን በተመለከተ አንድ ልምድ ያላቸው አስተማሪ በተደጋጋሚ አጠንክረው የተናገሩትን አሁንም ያስታውሳሉ፡፡ ጉዳዩን ረጋ ብለው ካሰቡበትና ከጸለዩበት በኋላ በትንሹም ቢሆን የሚያውቋቸውን ጥቂት ቤተሰቦች መርጠው ያለማቋረጥ ሊጎበኟቸው ይወስናሉ፡፡

ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያዎቹ በጣም የታወቁትና በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ሆነ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ዘንድ እጅግ የተከበሩት አቶ ከበደና ባለቤታቸው ወ/ሮ ደመቀች ናቸው፡፡ የአቶ ከበደና የወ/ሮ ደመቀች ቤተሰቦች ለብዙ ትወልዶች የኖሩ ናቸው፡፡ በስልሳዎቹ አመታቸው ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወልደው ድረው አሁን ለብቻቸው ይኖራሉ፡፡

አቶ ከበደና ወ/ሮ ደመቀች መሃይማን ባይሆኑም በቂ ትምህርት ግን   አላገኙም፡፡ በመልካም ምግባራቸውና ከሰዎች ጋር ባላቸው ንጹህ ግንኙነት በኅብረተሰብ ዘንድ ከበሬታን አግኝተዋል፡፡ እርስዎ በህበረታቸው ወይንም ባላቸው ተቀባይነት ላይ ተመርኩዘው ሰዎችን የሚያበላልጡ ወይም የሚፈርዱ በእርግጥ አይደሉም፡፡ በትምህርትዎ ወይም ባልዎት ደረጃ ምክንያት የበላይነት ስሜትም እንዲያድርብዎ አይፈቅዱም፡፡ የባሃኢ አስተማሪ አስከፊና ድብቅ ጠላት የሆነው ሰዎችን ዝቅ አድረጎ የመመልከት አስተሳሰብ ተጠቂ እንዲሆኑም አይፈቅዱም፡፡ በዘመቻው ወቅት ልምድ ካላቸው አስተማሪዎች ከተማሯቸው ቁም ነገሮች አንዱ የባሃኢ ትምህርቶችን ቀለል አድረጎ ለማቅረብ ሲባል አዋቂ ሰዎችን ለልጆች በሚገባ አነጋገር ማስተማር ተገቢ አለመሆኑን ነው፡፡ አዋቂዎች ማሃይም ቢሆኑም ባይሆኑም በእድሜያቸው ያካበቱት እውቀትና ጥበብ እንዳላቸው አጢነዋል፡፡ በዝቅተኝነት ስሜትና በጸሎት መንፈስ ተቀምጠው የመጀመሪያው የጥልቀት ትምህርት ጭብጥ ስር ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በጥንቃቄ ማስፈርና ማቀናጀት ጀመሩ፡፡ ይህ የጥልቀት ትምህርት ጭብጥ “ዘለአለማዊው የአምላክ ኪዳን” የሚል ነው፡፡ እንደዚህ ያሉ ስብሰባዎች ትንሽ ስለሚያስፈሩዎት በጭብጡ ላይ ጥቂት አንቀጾችን ለመጻፍ ወሰኑ፡፡ ይህም ድፍረትዎን ለማጠናከር እንዲረዳዎ እንጂ ለአቶ ከበደና ባለቤታቸው ወስደው ሊያነቡላቸው አይደለደም፡፡

*መልመጃ*

**1.** ከላይ በተሰጠው ምንባብ አዳዲስ አማኞችን ቤታቸው ድረስ ሄደው በሚጎበኙበት ጊዜ የሚኖርዎት አስተሳሰብና አመለካከት በሚያገኙት ውጤት ላይ ወሳኝ አስተወጽኦ እንደሚኖረው ተረድተዋል። ስለዚህ አንዳንድ አመለካከቶች ጉብኝትዎን እንዴት ፍሬያማ ሊያደርጉልዎ እንደሚችሉ ቆም ብሎ ማሰላሰል ጠቃሚ ነው። አቶ ከበደንና ባለቤታቸውን ለመጠየቅ በመሄድ ላይ ነዎት እንበል። ጉብኝትዎን አቶ ከበደንና ባለቤታቸውን እና ጥልቀት ትምህርቱን የሚያካሂዱበትን መንገድ አስመልክቶ በአእምሮዎ ሊመላለሱ ከሚችሉ አስተሳሰቦች መካከል ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ከእነዚህ መካከል አዲስ አማኞችን ለማጥለቅ ለሚያደርጉት ጥረት ፍሬያማነት የተሻለ አስተዋጽኦ ላላቸው የሚሏቸው ላይ ምልክት ያድርጉ።

ጉብኝትዎን አስመልክቶ

_______ እምነቱን ማስጠናትና ብዙ መማራቸውን ማረጋገጥ የእኔ ስራ ነው።

_______ ከእነዚህ ድንቅ ባልና ሚስት ጋር ጥቂት ጊዜ ማሳለፍና ከቅዱሳን ጽሁፎች ምንባቦችን መቋደስ እንዴት ያለ መልካም እድል ነው።

_______ አዳዲስ አማኞችን ማጥለቅ አስፈላጊ እንደሆነ አውቃለሁ። ይህንንም በደስታ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ። ይሁንና ሌሎች ማከናወን የሚገባኝ ተግባሮች ስላሉብኝ ብዙ ጊዜ እንደማይወስድብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

_______ ዛሬ ከአቶ ከበደና ከባለቤታቸው ጋር የምወያይባቸው በዛ ያሉ ዝርዝር ነጥቦች አሉኝ። አንዷንም ነጥብ ሳልዘነጋ ሁሉንም ነግሬያቸው መመለስ አለብኝ።

አቶ ከበደና ባለቤታቸውን አስመልክቶ

_______ አቶ ከበደና ባለቤታቸው ንጹህ ልብ ያላቸው ጥሩ ሰዎች ናቸው። የመረዳት አቅም ያላቸው ግን አይደሉም። በእርግጥ ባሃኦላህን ተቀብለዋል። ግን ስለ ትምህርቱ ምን ሊገባቸው ይችላል።

_______ ከአቶ ከበደና ከባለቤታቸው ጋር ስነጋገር ከበድ ያለ ነገር እንዳልናገር መጠንቀቅ አለብኝ። ብዙዎቹን የእምነቱ አስተሳሰቦችን በቀላሉ ሊረዷቸው አይችሉ ይሆናል። አስፈላጊው ነገር ለእነርሱ ፍቅር ማሳየት ነው። በቂ ትምህርት ስላላገኙ አይፈረድባቸውም።

_______ እነኝህ ምስኪን አዛውንቶች በዚህ እድሜያቸው ምን ሊማሩ ይችላሉ

_______ እያንዳንዱ አዲስ አማኝ አዲስ ተሰጥኦን ወደ ባሃኢ ማኅበረሰብ ይዞ ይመጣል። አቶ ከበደና ባለቤታቸው ውጥስ የባሃኦላህ ፍቅር ሲሰርጽና እውቀታቸው ሲጨምር ብዙ ጠቃሚ ግልጋሎቶችን ለማኅበረሰቡ ያበረክታሉ።

ጥልቀት ትምህርቱን የሚያካሂዱበት መንገድ አስመለክቶ

_______ የበሰሉ ሰዎች ናቸው። ማንበብም ይችላሉ። ጥቂት አጫጭር ጥቅሶችን እሰጣቸውና እራሳቸው እንዲያጠኑ ነግሬያቸው እመለሳለሁ።

_______ ከእነርሱ ጋር ተቀምጬ እያንዳንዱን ቃል በትእግስት ማብራራት እንዳለብኝ ማስታወስ አለብኝ። ካልሆነ እነዚህን አስቸጋሪ ሐሳቦች እንዴት ሊረዱ ይችላሉ።

_______ ሐሳባችንን መለዋወጥ የምንችልበትን መድረክ መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሐሳቤን በምገልጽበት ጊዜ በተደጋጋሚ ቆም በማለት ጥቅሶቹን በጋራ እንድናጠናና እንድንወያይባቸው ማድረግ አለብኝ፡፡

_______ እስቲ ቆይ! በመጀሪያ ሐሳቤን አንድም ሳይቀር አስተላልፋለሁ፡፡ በመጨረሻም ጠያቂ ካላቸው እጠይቃቸዋለሁ፡፡

2. ጥቂት ተሳታፊዎች በያዙ ቡድኖች ተከፋፈሉና በአስጠኚአችሁ በመታገዝ ወደ አቶ ከበደ ቤት ስለምታደርጉት ጉብኝት አሰላስሉ፡፡ የእያንዳንዱ ቡድን አባል ወደ አቶ ከበደ ቤት እንዴት እንደሚገባ፥ ሰላምታ እንዴት እንደሚሰጥ የሚያሳይ አጭር ጭውውት ለቡድኑ ያቅርቡ፡፡ ከዚያም ቡድኑ እያንዳንዱ ተሳታፊ ያቀረበውን ጭውውት ይገምግም፡፡ ግምገማውም የአቅራቢውን ትህትና ደግነትና እራሱን ዝቅ አድርጎ ማቅረብ አለማቅረቡን መመዘኛ ያድርግ፡፡ ሁሉም አባል ያዘጋጀውን ጭውውት ካቀረበ በኋላ በአንድነት በመሆን ተገቢ ናቸው ብላችሁ የምታምኑባቸውን የሰላምታና የመንደርደሪያ ሐረጎችን አቅርቡ፡፡

## ምዕራፍ 2

ከዚህ በታች ዘለአለማዊው የአምላክ ኪዳን በሚል ጭብጥ አጭር ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ አዲስ አማኞችን ቤታቸው ድረስ ሄደው ለማካፈል ያዘጋጁትን ማብራሪያ ይመስል ይሆናል፡፡

የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ አንዱ ተወዳዳሪ የሌለውና እራሱን ችሎ የሚኖረው እግዚአብሔር ነው፡፡ ሰማያትን ምድርንና በእርሷ ላይ ያሉ ተራሮችን፥ ሸለቆዎችን፥ ሜደዎች፥ በረሃዎችን፥ ወንዞችንና ባህሮችን ሁሉ የፈጠረው እርሱ ነው፡፡ ህይወት ያላቸው ነገሮችን ሁሉ የፈጠረው አምላክ ነው፡፡ ሰውንም ጭምር ፈጥሮ በእርሱ ላይ አምሳሉን አኖረበት፡፡

ውሱን የሆነ ወሰን የሌለውን ማወቅ ስለማይችል ሰውም የእግዚአብሔርን ሕላዌ ማወቅ እንደማይችል ባሃኦላህ ያስተምረናል፡፡ የተለያዩ እምነት ተከታዮች ለአግዚአብሔር የሚሰጡት ቅርጾች የእራሳቸው አእምሮ ወጤቶች ናቸው፡፡ የህልውናችን ምንጭ የሆነውን አምላክ ለመጥራት የምንጠቀምባቸው እንደ የሰማዩ አባታችን፥ የሰማዩ ኃይል፥ ታላቁ መንፈስ የመሳሰሉት እያንዳንዳቸው ከእርሱ ስሞችና በሕርያት አንዱን በሰው ቋንቋ ለመሰየም የሚያገለግሉ ቃላት እንጂ እርሱን ለመግለጽ ብቃት ኖሯቸው አይደለም፡፡

በህቡአተ ቃላት ይህንን እናነባለን፡-

“የሰው ልጅ ሆይ! የአንተን መፈጠር ወደድሁ ስለዚህም ፈጠርሁህ፡፡ ስለዚህ ስምህን እንዳነሳና ነፍስህን በሕይወት እስትንፋስ እሞላት ዘንድ አንተም አፍቅረኝ፡፡”

የህልውናችን ምክንያት እግዚአብሔር ለእኛ ፍቅር እንደሆነ እነዚህ የባሃኦላህ ቃላት ያሳስቡናል፡፡ ከክፉ የሚጠብቀን የሚመግበንና በሕይወት መንፈስ የሚሞላን ይህ ፍቅር መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ ችግር ወይም ድሉት ሐዘን ወይም ደስታ በሚገጥመን ጊዜ የአምላክ ፍቅር ያለማቋረጥ በእኛ ላይ እንደሚፈስ ማስታወስ አለብን፡፡

ከፍቅሩ የተነሳ ከፈጠረን በኋላ ለዘለአለም የሚቆይ ኪዳን አምላክ ከእኛ ጋር እንደገባ ከባሃኢ ጽሑፎች እንማራለን፡፡ “ኪዳን” የሚለው ቃል በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በመሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡ በዘለአለማዊው ኪዳን መሰረት የሁሉ ጸጋ ባለቤት የሆነው ፈጣሪ አይተወንም፡፡ ይልቁንም ከዘመን ዘመን ከክስተቶቹ አንዱን እየላከ ፈቃዱንና አላማውን በክስተቱ አማካኝነት ይገልጽልናል፡፡

“መከሰት” የሚለው ግስ መገለጽ ከዚህ በፊት የማይታወቅን ነገር ማሳየት ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ክስተቶች የእግዚአብሔርን ቃል የሚገልጹ ልዩ ነፍሶች ናቸው፡፡ በአምላክ ፈቃድ መሰረት እንዴት መኖር እንደሚገባንና እውነተኛ ደስታ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል የሚያስተምሩን እነዚህ ዓለም አቀፍ መምህሮች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክስተቶች መካከል ጥቂቶቹ

ክሪሽና፥ ሙሴ፥ ዞራስተር፥ ቡድሃ፥ ክርስቶስ፥ መሐመድና የዚህ ዘመን መንትያ ክስተቶች የሆኑት ባብና በሃኦላህ ናቸው፡፡

አንድ ስምምነት ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ ስምምነቱ የሚደረሰው በሁለት ወገኖች መካከል ሲሆን ሁለቱም የተወሰነባቸውን ድርሻ ለመፈጸም ቃል ይገባሉ፡፡ በዘለአለማዊዉ የአምላክ ኪዳን መሰረት አምላክ ሁልጊዜ ድርሻውን እንደፈጸመ ነው፡፡ በዚህ ኃይል ኪዳን ውስጥ ያለብንን ድርሻ መፈጸማችንን እንዴት ልናረጋግጥ እንችላለን?

ይህ ኪዳን የእግዚአብሔር ክስተትን እንድናወቅና ለፈቃዱም እንድንገዛ ይጠበቅብናል፡፡ የሕይወታችን ዓላማ አምላክን ማወቅና ለእርሱም መስገድ እንደሆነ ማስታወስ አለብን፡፡ በብዙ የባሃኦላህ ጽሑፎች መካከል ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው አጭሩ የግዴት ጸሎት ነው፡፡

"አምላኬ ሆይ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንደፈጠርከኝ እመሰክራለሁ፡፡ በዚህች ሰዓት የእኔን ደካማነትና ያንተን ኃያልነት የእኔን ምስኪንነትና ያንተን ሃብታምነት አረጋግጣለሁ፡፡

ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳት ከመትሆነውና በገዛ ራስህ ከምትኖረው አምላክ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡"[2]

አምላክን ልናውቀው የምንችለው በክስተቶቹ አማካኝነት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የሕይወታችንን ዓላማ ልናሟላ የምንችለው ለዘመናችን የመጣውን የእግዚአብሔር ክስተት በማወቅ ብቻ ነው፡፡ ባሃኦላህን የመቀበልን በረከት ያገኘን ሰዎች የቀድሞዎቹ ትንቢቶች በተሟሉበት በዚህ ዘመን ለመኖር በመታደላችን አመስጋኞች ልንሆን ይገባል፡፡ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ የባሃኦላህን ክብር ለማየት ባልቻሉበት በዚህ ወቅት እርሱን የመቀበልን ልዩ ስጦታ ስለቸረን ለአምላክ ምስናጋና ማቅረብ አለብን፡፡

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

"ይህ ቀን የእግዚአብሔር እጅግ በጣም የላቁ ችሮታዎች በሰዎች ላይ የፈሰሱበት የእርሱ እጅግ በጣም ታላቅ ጸጋ በተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጥ የተናኘበት ቀን ነው፡፡ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ልዩነቶቻቸውን በማስወገድ በእርሱ እንክባካቤና ፍቅራዊ ደግነት ዛፍ ጥላ ሥር በፍጹም አንድነትና ሰላም መኖር አለባቸው፡፡"[3]

በዚህ ቀን አንድ ሰው የባሃኦላህን ግልጸት የምስራች ሰምቶ ባይቀበለውና የቀድሞውን ሰርዓት ለመከተል ቢመርጥ እንዴት የሚያሳዝን ነው ይህ ሰው በየዘመኑ ትንቢት የተነገረለት ክስተት እንዲመጣ ተስፋ አድርገው ሲጠብቁ ቆይተው እርሱ በመጣ ጊዜ ግን ከካዱትና ለዘለአለማዊው የአምላክ ኪዳን ታማኞች ሳይሆኑ አጉል አምልኮዎቻቸውን የሙጥኝ ካሉት ጋር ተቆጠረ ማለት ነው፡፡

ባሃኦላህን ከተቀበልን በኋላ በእምነቱ የጸናንና ለትእዛዛቱም ታዛዦች ልንሆን ይገባል፡ መንገዱን የሳቱት የሚደርሱብን ነቀፋ ከመረጥነው እውነተኛ ጎዳና ሊያስወጣን አይገባም፡፡ በኪዳኑ ቆራጥና የጸናን ሆነን ልንቆይ ይገባል፡፡

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

"እርሱን ዘለዓለማዊውን እውነት ከማወቅ ቀጥሎ ለሰዎች የታዘዘው የመጀመሪያውና ከሁሉ ቀደሚ የሆነው ተግባር በእርሱ እምነት የመጽናት ተግባር ነው፡፡ አጥብቀህ ያዘው ከእነዚያ አዕመሮዎቻቸው በአምላክ ላይ በጥብቅ ከተተከሉትና መሰረት ከያዙት ሁን፡፡"[4]

የባሃኦላህን ሕይወት የደረሰበትን መከራም ሆነ የተቀዳጀው እጹብ ድንቅ ድሎች እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሰው የነበረውን ወሰን የሌለው ፍቅር ማስታወስ በተለይ በፈተና ጊዜ ለኪዳኑ ጽንተን እንድንቆይ ያለንን ቁርጠኝነት የበለጠ እየጠነከረ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ እስቲ የሚከተሉት ቃላት በአእምሮአችንና በልባችን ውስጥ እንዲቀረጹ እናድርግ፡፡

“ጥንታዊው ውበት የሰው ልጅ ከእሥረኝነቱ ነፃ ይወጣ ዘንድ በብረት ሰንሰለት ለመታሰር ፈቀደ፤ መላው ዓለም እውነተኛ ነፃነት ይቀዳጅ ዘንድ በዚህ እጅግ በጣም ብርቱ ምሽግ ውስጥ እሥረኛ መሆንን ተቀበለ፡፡ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ዘላቂ ፍስሐን ይቀዳጁ በደስታም የተሞሉ ይሆኑ ዘንድ የኃዘንን ጽዋ እስከ መጨረሻዋ ጠብታ ጨለጠ፡፡ ይህ ከሩኅሩኅ ከእጅግ በጣም ምህረተኛው ጌታችሁ ምሕረት የተነሳ ነው፡፡ በአምላክ አንድነት አማኞች ሆይ እናንተ ትከበሩ ዘንድ መዋረድን እናንተ ትበለጽጉና ታብቡ ዘንድ ብዙ ከባድ መከራዎችን ተቀብለናል፡፡ እርሱን መላውን ዓለም እንደአዲስ ይገነባ ዘንድ የመጣውን እነዚያ ከእግዚአብሔር ጋር ራሳቸውን ያወዳደሩት ከተሞች እጅግ በጣም ባድማ በሆነው ውስጥ እንዲኖር እንዴት እንዳስገደዱት ተመልከቱ!”[5]

***መልመጃ***

1. ከዚህ ቀደም ካጠናችሁት ክፍል ለየት ባለ መልኩ ይህ ክፍል የተለያዩ ጭብጦች የያዙ ረዘም ያሉ ምንባቦችን ያቀርብላችኋል፡፡ ዘለአለማዊው የአምላክ ኪደን በሚል ጭብጥ ጥናት ስታደርጉ ይህ የመጀመሪያችሁ ከሆነ ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ በራሳችሁ ቃላት መግለጽ እንድትችሉ በቡድን ሆናችሁ አንቀጽ በአንቀጽ በመደጋገም እያነበባችሁ አጥኑት፡፡ የምንባቡን ይዘት ለመረዳት እርስ በእርስ ልትረዳዱ የምትችሉባቸው ብዙ መንገዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድን አንቀጽ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ካነበባችሁ በኋላ ጥያቄ መጠያየቅ ትችላላችሁ፡፡ የጥያቄዎቹ መልሶች ባነበባችሁት አንቀጽ ውስጥ ሊገኝ ይገባል፡፡ ከአዲስ አማኞች ጋር በዚህ ርዕስ ውይይት በምታደርጉበት ጊዜ ቅዱሳን ጽሑፎችን ማካፈል ዋነኛ ስፍራ ስለሚይዝ በምንባቡ ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተሰጡ ጥቅሶች ትርጉም ላይ እንዲያሰላስሉ ይረዱዋችኋል፡፡

ሀ. የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ማን ነው? ________________________________________

ለ. አምላክ ያልፈጠረው ነገር አለን? ________________________________________

ሐ. አምላክ የሰውን ዘር ለምን ፈጠረ? ________________________________________

መ. ኪዳን የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ________________________________________

ሠ. አምላክ ከሰው ጋር ለምን ኪዳን አደረገ?________________________________________

ረ. አምላክን ካላፈቀርን የእርሱን ፍቅር አይደርሰንም ማለት የቻላልን? ________________________

ሰ. አምላክን ካላፈቀርን እርሱም አያፈቅረንም ማለት ይቻላልን? ________________________

ሸ. አምላክ ይተወን ይሆንን? ________________________________________

ቀ. የሕይወታችን ዓላማ ምንድን ነው? ________________________________________

በ. የአምላክን ሕላዌ ማወቅ የማንችል ከሆነ የህይወታችን ዓላማ አምላክን ማወቅ ነው ማለት ምን ማለት ነው? ________________________________________

ቸ. ከእግዚአብሔር ክስተቶች መካከል ጥቂቶቹን ይጥቀሱ? ______________________________

ኀ. የሚከተለውን አረፍተ ነገር ያሟሉ:-

በዚህ ቀን የእግዚአብሔር ______________________________ በሰዎች ላይ የፈሰሱበት ቀን ነው::
በዚህ ቀን ልዩነቶቻችንን ______________________________ በፍጹም አንድነትና ሰላም መኖር አለብን በዚህ ቀን የእግዚአብሔር ______________________________ በተፈጠሩት ነገሮች ተናኝቷል::

ኘ. በዘለአለማዊው የአምላክ ኪዳን ድርሻችንን ለማሟላት ምን ማድረግ አለብን? ______________________________

አ. በሃኦላህን ስንቀበል አስቀድሞ የመጡትን የእግዚአብሔር ክስተቶች ካድን ማለት ይቻላልን? ______________________________

ከ. በሃኦላህ ስለደረሰበት መከራ ማሰላሰል በኪዳኑ ፀንተን እንደንቆይ የሚረዳን ለምንድን ነው? ______________________________

ወ. በሃኦላህ በሰንሰለት እንዲታሰር ለምን ፈቀደ? ______________________________

ዘ. በሃኦላህ መዋረድን ለምን ፈቀደ? ______________________________

ዠ. በሃኦላህ ብዙ መከራ ለምን ደረሰበት? ______________________________

የ. በሃኦላህ መከራን የተቀበለው ጠላቶቹን ለማሸነፍ ኃይል ስለሌለው ነበርን? ______________________________

ደ. በሃኦላህ ጠላቶቹን ማሸነፍ የሚችል ከነበረ ታዲያ ለምን መከራን ተቀበለ? ______________________________

ጀ. የአምላክን እምነት በማገልገል መንገድ መከራንና ችግርን መቀበል የሚኖርብን ለምንድን ነው? ______________________________

2. የተለያዩ የጥልቀት ትምህርት ጭብጦችን ከአዲስ አማኞች ጋር ለመወያየት ሲነሱ በመጀመሪያ ሊያስተላልፉ የሚፈልጓቸውን መሠረታዊ ነጥቦች ግልጽ አድርገው በአእምሮዎ ሊይዟቸው ይገባል:: ከላይ በተሰጠው ምንባብ ውስጥ የተሰጡት መሰረታዊ ሐሳቦች እነማን ናቸው? ሊዘረዝሯቸው ይችላሉ? ______________________________

3. ሰዎች የምንናገረውን ቁም ነገር በሚገባ እንዲረዱልን ከፈለግን ሐሳባችንን ምክንያታዊ በሆነ ቅደም ተከተል ማቅረብ ይገባናል፡፡ ከላይ ያሰፈሯቸው የመሰረታዊ ሐሳቦች ዝርዝር ምክንያታዊ በሆነ ቅደም ተከተል አቅርበዋቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ካደደረጉ ግን ሐሳቦቹ ሊነገሩ በሚገባቸው ቅደም ተከተል ቁጥር ይስጧቸው፡፡

4. በኪዳኑ ስለመጽናት ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ከቀድሞ የእምነቱ ታሪክም ሆነ በቅርብ ከሚያውቁት ታሪክ ያስታውሱና በቡድንዎ ላሉ ተሳታፊዎች ይንገሯዋቸው፡፡ አንዳንዶቹን ታሪኮች በጭውውት መልክ ለማቅረብ ከተመቻችሁ አቅርቧቸው፡፡

5. ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አዲስ አማኞች ቤት ሔደው የሚያደርጉትን የውይይት ጭብጥ በሚገባ ከማወቅዎ በተጨማሪ ስለአማኞቹ ስለጉብኝትዎ ውይይቱን ስለሚያካሂዱበት መንገድ የሚኖርዎ ስሜት ግምትና አመለካከት ጉብኝትዎ ፍሬያማነት ላይ ዋና አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል በተለይ በወይይቱ ጊዜ ሁሉ በጸሎት ውስጥ እንዳሉ አድርገው ሊቆጠሩ ይገባል፡፡ በጉብኝትዎ ወቅት ከሌሎች ጋር ውይይት በሚያደርጉ ጊዜ ፊትዎን ሁልጊዜ አምላክን ወደማሰብ የእርስዎንና ከእርስዎ ጋር ያሉትን ሁሉ አእምሮና ልብ እንዲያበራ መለመን ይኖርብዎታል፡፡ በቃልም ይዘው በልብዎ ሊደግሟቸው የሚችሉ ከጸሎቶች የተወሰዱ ብዙ ሐረጎችና አረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በታች ያሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

"ልቦቻችንን አብራልን የሚያስተውሉ ዓይኖችንና ንቁ ጆሮዎችን ስጠን፡፡"[6]

"ጌታ ሆይ! የማያልቁ ስጦታዎችህን ስጠን የአንተ መርሖ ብርሃንም እንዲበራ ፈቃድህ ይሁን፡፡"[7]

"የእውነተኛ ግንዛቤ በሮችን ክፈት የእምነትም ብርሃን በድምቀት እንዲበራ አድርግ፡፡"[8]

"ጌታ ሆይ አገልጋዮችህ አንተን ለማየት ይችሉ ዘንድ ፊቶቻቸውን አብራላቸው..."[9]

"ጌታችን ሆይ! ፊታችንን ምሕረት ወደተመላው ገጽታህ አዙርልን..."[10]

## ምዕራፍ 3

ወደ አቶ ከበደ ቤት ያደረጉት የመጀመሪያ ጉብኝት በደስታ ሞልቶዎታል፡፡ እንደጠበቁት እንግዳ ተቀባይና ለመማር ጉጉ ሆነው አግኝተዋቸዋል፡፡ ለውይይቱ በጥንቃቄ መዘጋጀትዎ ትልቅ እርዳታ አድርጎሎታል፡፡ አስተሳሰብን በግልጽ ለማቅረብና የመረጧቸው ጥቅሶች ላይ ደግሞ ፍሬያማ ውይይት ለማድረግ ረድቶዎታል፡፡ የቀረቡልዎትን ጥያቄዎች ራስዎን ከፍ ከፍ ሳያደርጉ በዝቅተኝነት መንፈስ መልሰዋል፡፡

ብዙ አደጋች ጥያቄዎች ቀርበውልዎ ሊመልሷቸው እንደማይችሉ አምነው የበለጠ የሚያውቁ አማኞችን ጠይቀው ወይም ጽሑፎቹን አንብበው መልስ እንደሚያቀርቡ ቃል ገብተዋል፡፡

በጣም የሚያስደስተው አጋጣሚ ደግሞ የአቶ በከደና የባለቤታቸው የልጅ ልጅ የሆነችው ኤደን በውይይቱ መሳተፏ ነበር:: ኤደን ከአያቶቿ ጋር ጥቂት ሳመንታት ለማሳለፍ መጥታለች:: በውይይቱ ያደረገችው ንቁ ተሳትፎ በጣም አስደንቆዎታል:: ገና የ15 ዓመት ልጅ ብትሆንም ጥልቅ ጉዳዮችን ለመረዳት ያላትን ችሎታ አስተውለዋል:: ይህ ደግሞ በእርሷ እድሜ ካለ ሰው የማይጠበቅ ነው:: ስለዚህ ፍላጎቷና ችሎታዋ በሚፈቅድላት መጠን በእምነቱ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራት ሊረዷት ይወስናሉ:: የበሃኦላህ የሕይወት ታሪክ ላይ የተመሰረተ ምንባብ አጥንታ በእርስዎ እርዳታ በሚቀጥለው ላይ ንግግር ለማቅረብ ስትስማማ ደግሞ በጣም ተደስተዋል:: እርሷም በጉዳዩ ከመደሰቷ የተነሳ ከጓደኞቿ መካከል አንዳንዶቹን ለወይይቱ እንደምትጋብዝ አረጋግጣልዎታለች::
ከዚህ በታች የሚገኘው የበሃኦላህ የህይወት ታሪክን አስመልክቶ የቀረበው ዘገባ ኤደን ለንግግሯ የምታጠናውን ምንባብ ይመስላል::

በሃኦላህ ህዳር 12 ቀን 1817 ዓ.ም የፋርስ ዋና ከተማ በሆነችው በቴህራን ተወለደ:: ከልጅነቱ ጀምሮ እጅግ ያልተለመዱ ባህሪያትን ያሳይ ነበር:: በዚህ ባህሪው ምክንያት ትልቅ ደረጃ እንደሚጠብቀው ወላጆቹ አመኑ:: በንጉሱ ዘንድ ልዩ የሚንስቴርነት ማእረግ ያላቸው አባቱ ልጃቸውን በጣም ይወዱት ነበር:: አንድ ቀን በህልማቸው በሃኦላህ ወሰን በሌለው ባህር ሲዋኝ ያዩታል:: ሰውነቱ ሰፊው ባህርን እንዲያበራና እንዲያንፀባርቅ አድርጎታል:: ጥቁር ፀጉሩ በሁሉም አቅጣጫ ተንሳፎ ያብረቀርቅ ነበር:: ቁጥር ስፍር የሌላቸው አሳዎች በዙሪያው ተሰብስበዋል:: እያንደንዱም አሳ አንዱን የፀጉሩን ቅንጣት ይዟል:: ፀጉሩን የያዙት አሳዎች ብዙ ቢሆኑም አንዲት የፀጉር ቅንጣት እንኳን አልተነቀለችም:: በነፃነትና ያለምንም ገደብ በውሃው ላይ ሲንሳፈፍ ሁሉም ይከተሉት ነበር:: የበሃኦላህ አባትም በህልም ፈቺነቱ የታወቀ ጠቢብን የህልሙን ፍቺ ጠየቁት፣ ሰውየውም ወሰን የሌለው ባህር የሰው ዘር እንደሆነ ነገራቸው:: ብቻውንና ያለማንም ረዳት በሰው ዘር ላይ ንግስናን ይቀዳጃል:: ቁጥር ስፍር የሌላቸው አሳዎችም በዓለም ህዝቦች መካከል የሚያስነሳውን ንቅናቄ ይወክላሉ:: የሃያሉ አምላክ የማይቋረጥ ጥበቃ ስለሚከተለው ማንም ሊጎዳው አይችልም ሲል ህልሙን ፈታላቸው::

14 አመት በሆነው ጊዜ በጥበቡና በእውነቱ በንጉሱ እልፍኝ የታወቀ ነበር:: አባቱ ሞተው የእርሳቸውን ከፍተኛ ቦታ እንዲተካ ከመንግስት ጥያቄ ሲቀርብለት 22 ዓመቱ ነበር::

በሃኦላህ ግን አለማዊ ጉዳዮችን ለማስተደደር የሚያውለው ጊዜ አልነበረውም:: የንጉሱን እልፍኝና ምኒስትሮቹን ወደኋላ ትቶ በኃያሉ አምላክ የተመመደበለትን ጎዳና መከተል ቀጠለ:: ጊዜውን ጭቁኖችን፥ ህሙማንና ድሆችን በመርደት ያሳልፍ ነበር:: ብዙ ሳይቆይ የፍትህ ባላባት በመባል ታወቀ:: በሃያ ሰባት አመቱ ከአንድ ልዩ መልእክተኛ የባብን ፅሑፎች ተቀበለ:: ባብ አዲስ የእግዚአብሔር ክስተት የሚከሰትበትና ለዓለም ሰላም አንድነትና ፍትህ የሚያመጣበት ለረዥም ዘመናት ሲጠበቅ የቆየው የአምላክ ቀን መድረሱን ያወጀው የአምላክ መልእክተኛ ነው:: ወዲያውኑ በሃኦላህ የባብን መልእክት ተቀበለ፥ ከጠንካራ ተከታዮቹም አንዱ ሆነ:: የፋርስ ሕዝብ መሪዎች በእኔነት ስሜቶቻቸው ታውረው የባብን ተከታዮች በአሰቃቂ ጭካኔ ማሰቃየት ጀመሩ:: ምንም እንኳን በሃኦላህ ከተከበረ ቤተሰብ መሆኑን ቢታወቅም አልማሩትም:: ባብ ማንነቱን ካወጀ ከስምንት አመታት በኋላ ወይንም መስዋዕት ከሆነ ከሁለት አመታት በኋላ በሃኦላህ ጥቁሩ ጉድጓድ በተባለ የምድር በታች እስር ቤት ተጣለ:: በአንገቱ ዙሪያ አሸክመውት የነበረው የብረት ሰንሰለት በጣም ከባድ ስለነበር ጭንቅላቱን ቀና ማድረግ እንኳን አይችልም ነበር:: በዚያም በሐይለኛ ስቃይ የተሞላ ወራትን አሳለፈ:: ይሁንና ነፍሱ በአምላክ መንፈስ የተሞላውና ለዘመናት ሲጠበቅ ቀነበረው ታላቁ መምህር እንደሆነ የተገለጸለት በዚህ እስር ቤት ሳለ ነበር:: ከዚህ ጨለማ ወህኒ ቤት የበሃኦላህ ፀሐይ ፈንጥቃ በፍጥረት ሁሉ ላይ አንፀባረቀች::

በጥቁሩ ጉድጓድ አራት ወራት ካሳለፈ በኋላ ንብረቱን ሁሉ ተገፎ ከነቤተሰቡ ለስደት ተዳረገ:: በጣም ቀዝቃዛ በሆነው የክረምት ወራት በምዕራባዊው የፋርስ ተራራ በኩል በዚያን ጊዜ የኦቶማን ግዛት ከተማ የአሁኗ ኢራቅ ዋና ከተማ ወደሆነችው ባግዳድ ተጓዘ:: ወደዚያች በትእይንቶች ወደምትሞላው ከተማ በበረዶ የተሸፈነውን ምድር ለማቋረጥ ብዙ መቶ ማይሎችን ሲጓዙ የደረሰባቸውን መከራ ቃላት ሊገልጹት አይችሉም::

ብዙም ሳይቆዩ የበሃኦላህ ዝና በባግዳድና በአካባቢው ባሉ ሌሎች ከተሞች በመሰራጨቱ የተጋዘውን እስረኛ ምርቃት ለመቀበል ወደ እርሱ ቤት የሚመጡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ:: በሃኦላህ በጣም ታዋቂ በመሆኑ ቅናት ያደረባቸውም ጥቂት ሰዎች ነበሩ:: ከእነዚህ መካከል በበሃኦላህ ፍቅራዊ ጥበቃ ስር ይኖር የነበረው ወንድሙ ሚርዛ ያሕያ ነበር:: በጊዜው የባብ ተከታዮች ለሚርዛ ያሕያ ትልቅ ከበሬታ ያሳዩት ስለነበር በሃኦላህን የተቃወመው መሪያቸው ያደርጉኛል ብሎ በማሰብ ነበር:: የእግዚአብሔር መልእክተኛን በመቃወም የእራሱን ውድቀት እንደሚያስከትል አላወቀ! የእግዚአብሔር ክስተት በተገለፀ ጊዜ ለእርሱ ታዛዥ በመሆን የሚኖሩ ብቻ እውነተኛ ትልቅነትን የማግኘት ተስፋ ይኖራቸዋል:: የቅርብ ዘመዶቹ እንኳን እርሱ ከሌሎች ሰዎች የተለየና ማንም የማይጋራው ደረጃ እንዳለው መርሳት የለባቸውም::

ሚርዛ ያሕያ ሴራ ተከታዮች ዘንድ መከፋፈልን በመምጣቱ በሃኦላህ በጣም አዘነ:: አንድ ለሊትም ለማንም ሳይናገር ቤቱን ትቶ ወደኩርዲስታን ተራሮች ሄደ:: በዚያም ከማንም ሳይገናኝ የፀሎትና የሱባዔ ሕይወት አሳለፈ:: ማንም ከየት እንደመጣና ማን ተብሎ እንደሚጠራ አያውቅም ነበር:: ይሁንና ቀስ በቀስ የአካባቢው ሰዎች በአምላክ የተቸረ እውቀት ስላለው አንድ ታላቅና "ስም የለሽ" ጻድቅ ሰው ማውራት ጀመሩ:: የዚህ ቅዱስ ሰው ዜና የበሃኦላህ ትልቁ ልጅ አብዶል በሃ ዘንድ ሲደርስ የተወዳጁን አባቱን ምልክቶች ወዲያው አወቀ:: ከልዩ መልእክተኞችም ጋር ወደ ባግዳድ እንዲመለስ በሃኦላህን የሚለምኑ ደብዳቤዎች ተላኩ:: ይህንን ልመና በመቀበሉ ለሁለት አመታት የቆየው አሳዛኝ መለያየት አበቃ::

በሃኦላህ ተገልሎ በቆየባቸው ጊዜያት የባቢ ሕብረተሰብ ሁኔታ በፍጥነት አሽቆልቁሎ ነበር:: በሃኦላህም የተሰቃዩትንና ግራ የተጋቡትን የባብ ተከታዮች በአዲስ መንፈስ መሙላት ጀመረ:: ምንም እንኳ ትልቁ ደረጃውን ያላወጀ ቢሆንም የቃላቱ ኃይልና ጥበብ ብዛት ያላቸው ባቢዎችን ታማኝነትና በተለያዩ የሕይወት ጎዳና ላይ የተሰማሩ ሰዎችን አድናቆት አተረፈ:: ይሁንና አክራሪ የእስልምና ቀሳውስትና ቀናተኛ ወንድሙ ሚርዛ ያሕያ እንደዚያ ብዛት ባላቸው ነፍሶች ላይ የሚያሳድረውን የመለወጥ ውጤት በዝምታ መመልከት አልቻሉም:: ስለዚህም በተደጋጋሚ ለባለሥልጣናት በሃኦላህን ከሰሱ:: በመጨረሻም የፋርስ መንግስት ከአንዳንድ የኦቶማን ግዛት ባለሥልጣናት ጋር በማበር ከትውልድ ሐገሩ ይበልጥ እንዲርቅ ቁስጥንጥንያ ወደተባለች ከተማ አጋዙት::

ለባግዳድ ሕዝብ ሚያዝያ ወር 1863 ዓ.ም የትልቅ ሐዘን ወር ነበር:: ከጊዜ ወደጊዜ እያፈቀሩት የመጡት ወዳጃቸው ከተማቸውን ለቅቆ ወደማያውቁት ቦታ ሊሄድ ሆነ:: ከተማዋን ከመልቀቁ ጥቂት ቀናት በፊት ከባግደድ ወጣ ብሉ በምትገኝ መናፈሻ ድንኳኑን ጥሎ ሊሰናበቱት የመጡትን ብዛት ያላቸው ሰዎች ለአስራ ሁለት ቀናት ተቀበለ:: የባብ የከታዮች ወደዚያ መናፈሻ የሚሄዱበት በከፍተኛ ሐዘን ነበር:: ጥቂቶቹ በቀጣዩ ግዞት አብረውት ይሄዳሉ:: አብዛኞቹ ግን እዚያው ስለሚቀሩ ከዚያ በኋላ እንደፈለጉ አያገኙትም:: ይሁንና ይህ ጊዜ የሐዘን እንዲሆን አምላክ አልፈቀደም:: የበረከቱ በር በሰፊው ተከፈተ:: ባሃኦላህም ባብ እርሱ እግዚአብበሔር የሚከስተው እያለ የተነበየለት እርሱ እንደሆነ በዙሪያው ለነበሩት አወጀ:: ሐዘን ወሰን በሌለው ደስታ ተተካ:: ልቦች ተነቃቁ ነፍሶችም በእርሱ ፍቅር እሳት ተለኮሱ:: ከሚያዝያ 13 እስከ 21 ያሉት አስራ ሁለት ቀናት በሁሉም አካባቢ ባሉ ባሃኢዎች ዘንድ በሃኦላህ ለመጪዎቹ ምእተዓመታት ይከበራሉ::

ቁስጥንጥንያ የኦቶማን ግዛት ዋና ከተማ ነበረች:: የበሃኦላህ ጥበብና ግርማ እዚያም ቢሆን ብዙ ሰዎችን መሳብ ጀመረ:: በቁስጥንጥንያ መቆየት የለበትም ሲሉ አክራሪዎቹ የእስልምና ቀሳውስት አጉረመረሙ:: ባለስልጣናቱን ካሳመኑት በኋላ አድርያኖጵሎስ ወደበትባል ከተማ እንደገና አጋዙት:: በአድርያኖጵሎስም የጭቆና አሰራራቸውን ትተው ለሕዝቦቻቸው እድገት እራሳቸውን እንዲሰጡ ጥሪ በማድረግ ለዓለም ነገሥታትና የሃይማኖት መሪዎች ጽላቶችን ገለጸ:: በዚህ በኋላም ጠላቶቹ እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላው ቅጣት አውጠነጠኑ:: በዚያን ጊዜ በኦቶማን ግዛት ውስጥ ካሉት ሁሉ እጅግ አስከፊ ወደነበረው የአቆር የእስር ከተማ ከነቤተሰቡ እናግዘው ሲሉ አሰቡ:: የእስር ከተማውን አስከፊ ሁኔታ መቋቋም ስለማይችል እዚያው ይሞታል ሲሉ አሴሩ:: አምላክ እራሱ የለኮሰውን ማንም ሊያጠፋ እንደማይችል እነዚህ ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አላሰላሰሉም::

በሃኦላህ በአቆር የደረሰበት ችግር ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ለመግለጽ ያዳግታል:: በመጀመሪያ በአንዲት ጠባብ ክፍል ወስጥ ብቻውን ታሰረ:: ልጆቹ እንኳን እንዲያዩት አልተፈቀደላቸውም

ነበር፡፡ ምንም አይነት ምቾት ሳያገኝ ቀንና ለሊት በጠላቶቹ ተከበበ፡፡ ይሁንና የእስሩ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተለወጠ መጣ፡፡ የአቆር ነዋሪዎችና መንግሥት ወደ ከተማቸው የተጋዙት ጥቂት ባሃኢዎች ወንጀል የሌለባቸው መሆናቸውን እያመኑበት ሄዱ፡፡ ምንም እንኳ አብዛኛው ሕዝብ የበሃኦላህን ትልቅ ደረጃ ባያውቁም አሁንም ብዙ ሰዎች በእርሱ ጥበብና ፍቅር መሳብ ጀመሩ፡፡ ከጥቂት አመታትም በኋላ የእስር ከተማው በሮች ለበሃኦላህና ለተከታዮቹ ክፍት ሆኑ፡፡ በመጨረሻም የተሻለ ምቾት ባለው ባሕጂ በሚባል ቤት እንዲኖር ተፈቀደለት፡፡ በዚያም በከፍተኛ ክብርና ግርማ እየኖረ ሳለ በግንቦት ወር 1892 ዓ.ም ከዚህ ዓለም ተለየ፡፡

በሃኦላህ የዓለም አቀፍ ሰላምና ወንድማማችነትን ሰንደቅ አንስቷል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ከስቷል፡፡ ምንም እንኳን ጠላቶቹ ሐይላቸውን አስተባብረው ቢነሱበትም በቴህራን በሰንሰለት ታስሮ በነበረበት ወቅት አምላክ ቃል እንደገባለት በጠላቶቹ ላይ ድልን አግኝቷል፡፡ በሕይወት ዘመኑ የእርሱ መልእክት የብዙ ሺህ ሰዎችን ልቦች ያነቃቃ ሲሆን ብዙዎች በእርሱ መንገድ ሕይወታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ዛሬም የእርሱ ትምህርት በዓለም ዙሪያ መሰራጨቱን እንደቀጠለ ነው፡፡ የሰውን ዘር በአንድ ዓለም አቀፍ እምነት÷ አንድ የጋራ ሐይማኖት አንድ ማድረግ የሆነውን የመጨረሻ ግቡን ሳይቀዳጅ ምንም ሊያስቀረው አይችልም፡፡

***መልመጃ***

1. ከላይ የተጠው የበሃኦላህ ታሪክ ረዥም ሆኖብዎ ይሆናል፡፡ ወደቀጣዮቹ መልመጃዎች ከማለፍዎ በፊት በቡድን በመሆን ምንባቡን አንቀጽ በአንቀጽ በተደጋጋሚ ያንብቡት ይዘቱን በደንብ እስከሚረዱት ድረስ እርስ በእርስ ጥያቄ እየተጠያየቃችሁ አጠኑት፡፡ ከዚያም ምንባቡን ሳይመለከቱ በራስዎ ቃላት ታሪኩን ይናገሩ፡፡

2. በበሃኢ ሕይወትዎ የበሃኦላህን ታሪክ አንዳንድ ጊዜ አሳጥረው በሌላ ጊዜ ደግሞ በዝርዝር ለብዙ ሰዎች ይናገራሉ፡፡ ለዚህም የበሃኦላህን ሕይወት ዋና ክንውኖች በአእምሮዎ መቅረጽ እጅግ ይረዳዎታል፡፡ ከዚህ በታች በተሰጠው ባዶ ቦታ የሚያዘጋጁት ዝርዝር መነሻ ነው፡፡ ስለእምነቱ ታሪክ ያለዎ እውቀት እየጨመረ ሲሄድ ተጨማሪ ክንውኖችን በማካተት ዝርዝርዎን ያዳብሩታል፡፡ __________________________________

3. ኪዳን ወይም የበሃኦላህ ሕይወት በመሰሉ ጭብጦች ላይ ከአዲስ አማኞች ጋር ሲወያዩ እያንደንዱን ዝርዝር ነጥብ አድማጭዎ እንዲያስታውሱ መጠበቅ የለብዎትም፡፡ ይሁንና ባለፈው ምእራፍ እንደተጠቀሰው ጭብጡን ለመረዳት እጅግ አስፈላጊና በውይይትዎ ጊዜ አጽንኦት ሰጥተው ሊናገሩ የሚገቡ አንዳንድ ነጥቦች አሉ፡፡ ከላይ በተሰጠው የበሃኦላህ ሕይወት ምንባብ ውስጥ የተካተቱና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ሐሳቦች ከዚህ በታች ባለው ክፍታ ቦታ ይዘርዝሩ፡፡ ይረዳዎ ዘንድ አንድ ምሳሌ ተሰጥቶታል፡፡

ምሳሌ፡- በሃኦላህ ታላቅ መከራ ተቀብሏል

**1.** ____________________
**2.** ____________________
**3.** ____________________
**4.** ____________________
**5.** ____________________

**6.**__________________________________________
**7.**__________________________________________
**8.**__________________________________________
**9**__________________________________________
**10.** ________________________________________
**11.** ________________________________________
**12.** ________________________________________
**13.** ________________________________________
**14.** ________________________________________
**15.** ________________________________________

**4.** *በሃኦላህ ለሰው ልጅ ባለው ፍቅር ሲል ብዙ መከራ መቀበሉን እንደ ባሃኢነታችን ሁላችንም ልናስታውሰውና ልናሰላስልበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ስለዚህ መከራ በምንናገርበት ወቅት አቅመ ቢስ የጠላቶቹ ሰለባ እንደሆነ አድርገን ማቅረብ የለብንም፡፡ የስደትና የእስራትን ጎዳና የመረጠው በገዛ ፍቃዱ ነው፡፡ የሰው ልጅ ነፃ ይሆን ዘንድ በሰንሰለት መታሰርን ተቀበለ፡፡ የሕይወት ታሪኩ ምንም እንኳን በመከራ የተሞላ ቢሆንም በመሰረቱ የድል ታሪክ ነው፡፡ ስለበሃኦላህ ሕይወት እስከአሁን ባለዎ እውቀት ላይ በመመርኮዝና በአስጠኚው እርዳታ በበሃኦላህ ላይ ስለደረሱት መከራዎችና ስለ ተቀደጃቸው ድሎች አጭር ንግግር አዘጋጅተው ያቅርቡ፡፡*

*ራስን ዝቅ አድርጎ መመልከት አዲስ አማኞችን በማጥለቅ ለሚያበረክቱት ግልጋሎት ከሚያስፈልጉ ባህሪያት አንዱ ነው፡፡ በአምላክ ፊት ራስን ዝቅ ማድረግ ራስን ዝቅ አድርጎ የመመልከት ሁሉ መሰረት ነው፡፡ ከዚህም በፍጥረቱ ፊት ራስን ዝቅ ማድረግ ይመነጫል፡፡ ከሁሉም በላይ ስለአምላክና ስለክስተቶቹ በምንናገርበት ጊዜ የዝቅተኝነት አመለካከት በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች በተሰጠው ጥቅስ ላይ በሚገባ ካሰላሰሉ በኋላ በቃልዎ ለመያዝ የተቻለዎትን ጥረት ያድርጉ፡፡*

*"እነዚያ የእግዚአብሔር ተወደጆች የሆኑት፤ በማንኛውም ቦታ ሲሰበሰቡና ከማንኛውም ሰው ጋር ሲገናኙ ስለእግዚአብሔር ባላቸው ስሜት፥ የእርሱን ምስጋናና ወዳሴ በማያቀርቡበትም ሁኔታ ምክንያት፥ ከእግሮቻቸው በታች የሚገኘው አቧራ እያንዳንዱ ከፍተኛ ትሕትናና ታዛዥነት ማሳየት አለባቸው፡፡ እነዚህ ቅዱሳን ነፍሶች ከሰዎች ጋር የሚያደርጉት ንግግር በሚያስተላልፈው ስሜት ምክንያት፥ እነዚሁኑ የአቧራ አቶሞች በጥልቅ ስሜት እንዲነኩ እንዲያደርግ በከፍተኛ ኃይል የተመላ መሆን አለበት፡፡ በላይዋ የሚራመዱባት ምድር፡- "እኔ ከእናንተ የተሻልኩ ነኝ፥ ምክንያቱም ገበሬው የሚጭንብኝን ሸክም ለመሸከም እንዴት ትዕግስተኛ እንደሆንኩ ተመልከቱ፡፡ እርሱ የፀጋ ሁሉ ምንጭ የሆነው አደራ የጣሉብኝን ቡራኬዎች ለሕያዋን ሁሉ ያለማቋረጥ የማካፍለው መሣሪያ እኔ ነኝ፡፡ የተሰጠኝ ክብርና የማይቆጠር ሀብት ሁሉ እያለኝ፥ የትሕትናዬን ጥልቀት አስተውሉ፥ በምን ዓይነት ፍጹም የሆነ ተገዥነት ራሴን በሰዎች እግሮች ሥር ለመርገጥ እንደፈቀድኩ ተመልከቱ... "የሚሉትን ቃላት እንድትናገራቸው እንዳይፈቀድላት ራሳቸውን ከፍተኛ በሆነ ሥነምግባር መምራት አለባቸው..."*

# ምዕራፍ 4

*ኤደን ስለበሃኦላህ ሕይወት ያቀረበችው ንግግር ከጠበቁት በላይ ግሩም ነበር፡፡ ንግግሩ ጣፋጭና በእርግጠኝነት የተሞላ ነበር፡፡ አቶ ከበደና ባለቤታቸው በኤደን ንግግር መነካታቸው አስታውቆባቸዋል፡፡ የጋበዘቻቸው ሁለት ጓደኞቿ ሲስቁ የነበረ ቢሆንም ስለእምነቱ የማወቅ ፍላጎት አድሮባቸዋል፡፡ እርሶዎም ወደ አቶ ከበደ ቤተሰብ ያደረጓቸው ሁለት ጉብኝቶች ባሳየው ፍሬ በመበረታታትዎ በዚሁ ስልት አዲስ አማኞችን ማጥለቅን ለመቀጠል ተነሳስተዋል፡፡ እነዚህ አጭርና አስደሳች ውይይቶች እንዴት መቀጠል አለባቸው? አቶ ከበደና ወ/ሮ ደመቀች ጠንካራ አማኞችና የባሃኢው ማህበረሰብ ንቁ ተሳታፊዎች ለመሆን ከሚያስችሏቸው የጥልቀት ትምህርት*

ጭብጦች መካከል ጥቂቶቹ እነማን ናቸው? ይህ ጥያቄ ለቡዙ ቀናት አእምሮዎ ውስጥ ሲመላለስ ቆይቷል፡፡ በአንድ በኩል ማንፈሳዊ ሕይወታቸው በጽኑ መሰረት ላይ እንዲቆም ይረዳቸው ዘንድ ስለ ጸሎት፥ የነፍስ ሕይወት፥ የመስዋዕትነት እውነተኛ ትርጉምን በመሰሉ ርዕሶች ላይ ውይይት ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ አማኞች ከባሃኢ ማህበረሰቡ ጋር በሚገባ ተቀላቅለው በእንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መርዳት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ ለነገሩ ወደ አቶ ከበደ ቤት የሚያደርጉት ቋሚ ጉብኝት በእርስዎ ላይ ጥገኛ ስለሚያደርጋቸው ለዘላለም አይቀጥልም፡፡ በተጨማሪም በራሳቸው ጥረት እምነቱን የሚያገለግሉ ባሃኢዎች እንዳይሆኑም ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ "ያም ሆነ ይህ ለአሁን የሚገባውን በጊዜው መፈፀም ያስፈልጋል" ሲሉ ለራስዎ ነገሩ፡፡ አሁን ማሰብ ያለብኝ በሁሉት ቀናት በኋላ በማደርገው ጉብኝት የሚኖረኝ ውይይት በምን ጭብጥ ላይ በሆን እንደሚገባው ነው፡፡

በአእምሮዎ ለተነሳው ውዝግብ ባልጠበቁት መንገድ መልስ አገኙ፡፡ አንድ ምሽት በተካፈሉት የባሃኢ ስብሰባ በአማኞቹ መካከል ከፍተኛ አለመስማማት እንዳለ አስተዋሉ፡፡ ጥቁር ደመና አካባቢውን የሸፈነው ይመስል ነበር፡፡ የደስታ ነፀብራቅ ጠፍቷል፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ነበር፡፡ የእምነቱ ከፍተኛ ጠላት የሆነው መከፋፈል ሾልኮ ወደ ማህበረሰቡ ገብቷል፡፡ "በባሃኢ ማህበረሰብ ሊኖር ስለሚገባው ፍቅርና አንድነት" አሉ ለራስዎ "ይህ የሚቀጥለው ጉብኝቴ የውይይት ጭብጥ ይሆናል፡፡"

ስለ መከፋፈል አስከፊነት ለአቶ ከበደና ለባለቤታቸው ለመንገር በጣም ከመጓጓትዎ የተነሳ የጨዋነት ገደብ ሊያልፉ ምንም አልቀረዎ፡፡ ከአጭር ሰላምታ በኋላ "ለበሃኦላህ እምነት ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች ዋነኛው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?" ሲሉ በድንገት ጠየቋቸው፡፡ ጥያቄዎን ያቀረቡበት መንገድ አቶ ከበደና ባለቤታቸውን አላስደሰታቸውም፡፡ ሆኖም ባዳበራችሁት ቀረቤታ ምክንያት ለእርስዎ በቂ ፍቅር ስላላቸው አልተናደዱብዎትም፡፡ "ትንሽ መረበሽ ይታይብሃል፡፡ "አሉ ወ/ሮ ደመቀች በፈገግታ፡፡ "በእርግጥ ጥያቄህ መሰረታዊ ሲሆን መልስም ለመስጠት የምንችል ይመስለኛል፡፡ ይህንን እምነት የተቀበልነው በሃኦላህ የሰውን ዘር አንድ ለማድረግ እንደመጣ በመረዳታችን ነው፡፡ ስለዚህ በባሃኢዎች መካከል ሊኖር ከሚችል መከፋፈል በላይ እምነቱን ሊጎዳ የሚችል ነገር የለም፡፡"

በቅንነትና ፍቅር የተሞላው የወ/ሮ ደመቀች አነጋገር ወደቀድሞው እርጋታዎ መለሰዎ፡፡ "ጥያቄዬን በመሰንዘሬ ይቅርታ አድርጉልኝ" አሉ ድምጽዎን ዝቅ አድርገው፡፡ "አንድነትን አስመልክቶ ብዛት ያላቸው ጥቅሶችን ይዤ መጥቻለሁ፡፡ አብረን ለማጥናት ይመቻችኋልን?" በዚህ አኳኋን በጣም አስፈላጊ በሆነው በዚህ ጭብጥ ላይ ውይይት ማድረግ ጀመራችሁ፡፡ ከዚህ በታች በወይይታችሁ ልታካትቷቸው የምትችሏቸው ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡

- አንድ የባሃኢ ማኅበረሰብ እውነተኛ አንድነት እንዲኖረው ከፀብና ከጭቅጭቅ መራቅ አለበት፡፡ በሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

"በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ግጭት እንደ ውዝግብ እንደመቃቃርና እንደመጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡ በአምላክ ኃይልና በእርሱ ሉዓላዊ እርዳታ ሽሹአቸው በእርሱም፥ በአዋሐጁ፥ በሁሉን አዋቂው፥ በፍጹም ጠቢቡ ስም የሰዎችን ልቦች ለማስተሳሰር ተጣጣሩ፡፡"[13]

- በባሃኢ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ አማኞችን ሁሉ መውደድ አለብን፡፡ ፍቅራችን ደግሞ ለእግዚአብሔር ፍቅር ስንል ብቻ መሆን አለበት፡፡

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፡-

"ፍጹም የሆነ አንድነት ይኑራችሁ፡፡ አንዱ በሌላው ፈጽሞ አይቆጣ... ፍጡሮችን ለእነርሱ ብላችሁ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ስትሉ አፍቅሩ፡፡ ለእግዚአብሔር ብላችሁ የምታፈቅሩአቸው ከሆናችሁ ልትቆጡ ወይም ትዕግሥት ልታጡ ከቶ አትችሉም፡፡ ሰው ፍጹም አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ጉድለቶች አሉ ስለዚህ ሰዎቹን ራሳቸውን ከተመለከታችሁ ሁልጊዜ ደስታ ያጣችሁ ትሆናላችሁ፡፡ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ከተመለከታችሁ ታፈቅሩአቸዋላችሁ

እንዲሁም ደጎች ትሆኑላቸዋላችሁ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዓለም ፍጹም የሆነና የተሟላ የምህረት ዓለም ነውና።"

- እርስ በእርሳችን እየተዋደድን እንኳን በመካከላችን አለመስማማት ቢፈጠር የሚከተለውን የአብዶል በሃ ምክር ማስታወስ ይገባናል።

"እያንዳንዳችሁ የልባችሁ ሃሳቦች ሁሉ በፍቅርና በአንድነት ላይ እንዲያተኩሩ እንድታደርጉ እጠይቃችኋለሁ። የጦርነት ሃሳብ ሲመጣባችሁ ይበልጥ ጠንካራ በሆነው የሰላም ሃሳብ ተቃወሙት። የጥላቻ ሃሳብ ይበልጥ ኃይል በተመላው የፍቅር ሃሳብ መደምሰስ አለበት። የጦርነት ሃሳቦች በስምምነት፥ በደህንነት፥ በእረፍትና በእርካታ ሁሉ ላይ ጥፋትን ያመጣሉ። የፍቅር ሃሳቦች ወንድማማችነትን፥ ሰላምን፥ ወዳጅነትንና ደስታን ለማጠናከር ጠቃሚዎች ናቸው።"[15]

- አለመስማማታችን ለማስወገድ ብዙ ብናደርግም ስሜታችን አሸንፎን ወደፀብ እያመራን ከተገኘን በእነዚህ የደካማነት ጊዜያት እነዚህ የበሃኦላህ ቃላት ሊረዱን ይችላሉ።

"በመካከላችሁ ማንኛውም ልዩነት ቢነሳ ከፊታችሁ እንደቆምኩ ተመልከቱኝ ለእኔም ስም ብላችሁ ለግልጹና ለአንጸባራቂው እምነቴም ላላችሁ ፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ የእርስ በርሳችሁን ስህተቶች አትመልከቱ።"[16]

- የሌሎችን ስህተት አለመመልከት፥ መልካም ባህሪያቸው ላይ ማተኮርና ከሐሜት ሙሉ በሙሉ መገለልን የመሰሉ መንፈሳዊ ስነምግባሮች መከፋፈልን የሚያስወግዱ ውጤታማ እርምጃዎች ናቸው። የምንወዳቸውን ሰዎች ስህተት ያለመመልከት አዝማሚያ እንዳለንና እነርሱንም ኃጢአትን በሚሸፍን ዓይን የመመልከት ችግር እንደሌለብን ማስታወስ አለብን። አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፦

"ጉድለት ያለበት ዓይን ጉድለቶችን ያያል። ስህተቶችን የሚሸፍን ዓይን ወደነፍሶች ፈጣሪ ይመለከታል። እርሱ ፈጠራቸው፥ ያሰለጥናቸዋል፥ የሚያስፈልጋቸውንም ያድላቸዋል፥ ችሎታን፥ ሕይወትን፥ የማየትንና የመስማትን ሃይል ይሰጣቸዋል ስለዚህም የታላቅነቱ መልክቶች ናቸው። ሁሉንም ሰው ማፍቀርና ለሁሉም ደግ መሆን ድሆችን ማንከባከብ ደካማውን መጠበቅ ለታመሙት ፈውስ መሻት፥ እውቀተ ቢሶችን ማስተማርና ማሰልጠን አለባችሁ።

በሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

"የዙፋኔ ጓደኛ ሆይ! እርኩስ ነገር አትስማ እርኩስ ነገርም አትመልከት እራስህን አታዋርድ እንዲሁም አትዘን አታልቅስ። እርኩስ ነገር አትናገር፤ በአንተም ላይ ሲነገር እንዳትሰማ የሌሎችን ስህተት አታሉላ። የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ የማንንም ውርደት አትመኝ፤ የራስህ አራዳነት እንዳይገለጽብህ። እንግዲህ በነጻነትና በዕርካታ ይህንን ሟች አካል ጥለህ ወደ ረቂቋ ነገት ተመልሰህ በማይጠፋው መንግሥት ለዘላለም ትኖር ዘንድ፤ ከቅጽበት ከሚያልፍ ጊዜ ያነሱትን የሕይወትህን ቀኖች በአእምሮ እንከን አልባ በልብህ የልጎደፍህ፥ በሃሳብህ ንጹህ፥ በተፈጥሮህም የተቀደስክ ሆነህ ኑር።"[18]

- በእርግጥ አንድነት የግጭትና የጭቅጭቅ አለመኖር ብቻ አይደለም። ፍቅርም የሚገለጸው በቃላት ብቻ አይደለም። በባሃኢ ማህበረሰባችን እውነተኛ ፍቅር አለ ብለን ልንመካ የምንችለው አንዱ ለሌላው ያለው ፍቅር በግልጋሎት ሲተረጎምና እንቅስቃሴዎቻችን በመተባበርና እርስ በእርስ በመረዳዳት መንፈስ ሲታቀፉ ነው።

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፦

"አንዳንድ ፍጡራን በገለልተኝነት ለብቻቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ዛፍ ያለ ሌሎች ዛፎች እርዳታና ትብብር ሊኖር ይችላል። አንዳንድ እንስሳት በገለልተኝነት ከመሰሎቻቸው ርቀው የተናጠል ኑሮን ይኖራሉ። ይህ ግን ለሰው አይቻልም። በሕይወቱና በኑሮው ትብብርና ማኅበራዊ ንግኙነት ፍጹም አስፈላጊዎች ናቸው። በመቀራረብና በግንኙነት አማካይነት የግልና የጋራ ደስታና ዕድገት እናገኛለን።"[19]

- ፍሬያማ የሆነ የማህበረሰብ ምክክር ማድረግ እጅግ ወሳኝ ነው። በምክክር አማካኝነት ስለአንድ ጉዳይ የሚኖረን የተለያዩ አመለካከቶች ይጠቃለሉና በጋራ እንቅስቃሴዎቻችን ልንወስደው የሚገባንን ከሁሉም የተሻለ አቅጣጫ እናገኛለን ልንወስደው የሚገባንን ከሁሉም የተሻለ አቅጣጫ እናገኛለን። በምክክር አማካኝነት ካለን ደግሞ ለማህበረሰባችን እድገት የሚበጁ እቅዶችን እናወጣለን።

አብዶል በሃ ለመመካከር ለሚነሱ እንዲህ ይላል፡-

"በሚሰበሰቡበት ጊዜ ፊታቸውን ወደ ላይኛው መንግስት ማዞርና ከክብር ግዛት እርዳታ መጠየቅ አለባቸው። ከዚያም በኋላ በከፍተኛ ታማኝነት፥ አክብሮት፥ ክብር፥ ጥንቃቄና ሚዛናዊነት ሃሳቦቻቸውን መግለጽ መጀመር አለባቸው። ሃሳበ ግትርነትና የራስ ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ መጎትጎት በመጨረሻ ወደ ሃሳብ መለያየትና ወደንትርክ ስለሚመራና እውነት ተደብቆ እንዲቀር ስለሚያደርግ የራሳቸው ሃሳብ ብቻ ይሰማ ማለት ሳይሆን፥ በሁሉም ጉዳይ እውነቱን መፈለግ አለባቸው። የተከበሩት አባላት በመሉ ነፃነት የየግል ሃሳቦቻቸውን መግለጽ አለባቸው። እንዲሁም ማንም ሰው የሌሎችን ሃሳብ ማቃለል በምንም ዓይነት አይፈቀድም፤ ይልቁንም ሚዛናዊ በሆነ አነናገገር፥ እውነቱን መግለጽ አለበት። የሃሳብ ልዩነት ቢፈጠርም የድምጽ ብልጫ ያገኘው ሃሳብ መጽናት አለበት ሁሉም ለብዙኃኑ ድምጽ መታዘዝና መገዛት አለባቸው።"[30]

- የሐሳብ አንድነት ወደ ተግባር አንድነት ካልተለወጠ የተሟላ አይሆንም። የተግባር አንድነት ሲባል ሁሉም ሰው አንድ አይነት ስራ ይሰራል ማለት አይደለም። በአንፃሩ አንድ ማህበረሰብ የተግባር አንድነት እቅድ ሲነድፍ የእያንዳንዱን ግለሰብን ልዩ ስጦታ ወይም ችሎታ ሙሉ በሙሉ ይጠቀማል። በዚህም ሐይላችን ይበዛል፥ ትንሹን የባሃኢ ማህበረሰብ ትልቅና ሐያል የሆኑ የዓለም ድርጅቶች እንኳን ሊያገኙ ያልቻሉትን ውጤት ይቀዳጃል።

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፡-

"ለሰው ዘር ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገው ትብብርና መደጋገፍ ነው። በሁሉም የሰው እንቅስቃሴዎች ደረጃ የወንድማማችነትና የኅብረት ትስስር እየጠነከረ በሄደ ቁጥር የገንቢነትና የስራ ውጤት መጠንም ይበልጥ ከፍ እያለ ይሄዳል።"[21]

***መልመጃዎች***

**1.** በቡድን ተከፍለው ከላይ የተሰጡትን ሐሳቦች ነጥብ በነጥብ በጥንቃቄ ካነበቡ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያጠናቁ። ይህም በጥቅሶቹ ትርጉም ላይ የበለጠ እንዲያሰላስሉ ይረዳዎታል።

ሀ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አሟሉ።

- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ____________ እና አንደ ግጭት፥ እንደ____________ ውዝግብ፥ እንደ መቃቃርና ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።
- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል አንደ አለመግባባትና እንደ ____________ እንደ ውዝግብ፥ እንደ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።
- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደግጭት እንደ ወዝግብ እንደመቃቀርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ____________________
- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወደጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ግጭት፥ እንደ ውዝግብ እንደ መቃቃርና ________________ ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉደት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወደጆች መካከል አንደ አለመግባባትና እንደ ግጭት ______ ______ እንደ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉደት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።
- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ግጭት እንደውዝግብ ______ ______ ና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።
- በዚህ ቀን በእግዚአብሔር ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባትና እንደ ግጭት እንደ ውዝግብ እንደ መቃቃርና እንደ መጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ ______ ______ ላይ ጉደት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።

ለ. በማህበረሰብዎ መከፋፈል እንዳይኖር ለማገዝ እርስዎ ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ይዘርዝሩ። ______

ሐ. ሁል ጊዜ ሰዎችን ለማፍቀርና ለእነሱም ደግ ለመሆን ምን ማድረግ አለብን? ______

መ. በሁለተኛው ጥቅስ ውስጥ አብዶል በሃ ሲመክረን

- ፍጹም በሆነ______ መኖር አለብን።
- ______ አንዱ ሌላውን ፈጽሞ______
- ሁሉን ሰዎች ለእነርሱ ብለን ሳይሆን ______ ማፍቀር አለብን።
- ______ ብለን የምናፈቅራቸው ከሆነ ______ ______
- ወይንም ______ ልናጣ ከቶ አንችልም።
- ሰው______ አይደለም
- ወደ ______ የምንመለከት ከሆንን ሰዎችን ______ ______ እንዲሁም
- ______ እንሆንላቸዋለን።

ሠ. በሶስተኛው ጥቅስ ውስጥ አብዶል በሃ ሲመክረን

- እያንዳንዳችን የልባችንን ሃሳቦች ሁሉ በ______ እና ______ እንዲያተኩሩ እንድናደርጋቸው ይነግረናል።
- የጦርነት ሃሳብ ሲመጣብን ______ ______ እንድንቃወም ይነግረናል።
- የጥላቻ ሃሳብ______ ______ መደምሰስ እንደሚቻል ይነግረናል።
- የጦርነት ሃሳቦች ______ ______ እና ______ ላይ ጥፋትን ያመጣሉ።

- የፍቅር ሃሳቦች ______________________ _______________________________________
  __________ __________________________________
  ለማጠናከር ጠቃሚዎች ናቸው፡፡

ረ. እርስዎና በሌሎች የማህበረሰቡ አባላት መካከል ልዩነት ሲፈጠር ሲመለከቱ ምን ማድረግ አለብዎ? ____________________________________________________________
________________________________________________________________________
_________________________________________

ሰ. ለማህበረሰብዎ አንድነት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያስችልዎት መንፈሳዊ ሥነ ምግባራትን ይዘርዝሩ______________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
_________________________________________

ሸ. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አድራጎቶች ከበሃኦላህ ትምህርቶች ጋር የሚስማሙ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ይወስኑ

| | | |
|---|---|---|
| • የሌሎችን ጉድለቶች መመልከት | አዎን__________ | አይደለም___________ |
| • የሌሎችን ስህተት አለመመልከት | አዎን__________ | አይደለም___________ |
| • ለአካባቢ መንፈሳዊ ጉባኤ የአንድን ሰው መጥፎ አድራጎት መንገር | አዎን__________ | አይደለም___________ |
| • ስለሌላ ሰው ጉድለት ለባልንጀራ አስተያየት መስጠት | አዎን__________ | አይደለም___________ |
| • ሌላን ሰው በማንቋሸሽ አጋኖ ወይም ታሪኩን አጣሞ መናገር | አዎን__________ | አይደለም___________ |
| • ስለሌሎች ስህተት ማሰብ | አዎን__________ | አይደለም___________ |

ቀ. አንዳንድ ሰዎች ስህተት ሲሰሩ የምንነቅፈው ሌሎች ግን ያንኑ ስህተት ሲሰሩ የማንነቅፈው ለምንድን ነው? ________________________________________________________
________________________________________________________________________
_______________________________________________

በ. ሰዎች እርስ በእርስ በሚተማሙበት ሁኔታ አንድነትን ለመመስረት ይቻላልን? __________
_______________________________________________ ለምንስ አይቻልም? _________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
____________________________

ተ. ሆን ብሎ ስለሌላ ሰው ውሸት መናገር ትክክል እንዳልሆነ አያጠያይቅም፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው በእርግጥም ስለፈጸማቸው ነገር ለሌላ ሰው የነቀፌታ አስተያየት መሰንዘር ክፋት አለውን ?______________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
_____________________

ቸ. ሐሜት በሐሜተኞች መንፈሳዊ እድገት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምንድን ነው?___________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
________________________________________________________________________
_______________________________________________

ኀ. በአሉባልታ በሐሜትና በነቀፌታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ነ. እነዚህን ልማዶች ከእኛ የምናስወግደው እንዴት ነው ?____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ኘ. አንድ ሰው ስለ ሌላ ሰው ስህተት ሊነግረን ቢጀምር ምን ማድረግ አለብን____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

አ. አንድ ባሃኢ እንደ መዋሸት ወይም መስረቅን የመሰሉ መጥፎ ነገሮች ሲያደርግ ብንመለከትና ይህም ተግባር በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እያስከተለ መሆኑን ብናውቅ ዝም ማለት አለብን? ከሌለብን ምን ማድረግ ይኖርብናል? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ከ. ሐሜትና አሉባልታ በባሃኢ ማህበረሰብ ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው? ____________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ኸ. ስለሌሎች ሰዎች ስናወራ በአጠገባችን እንዳሉ አድርገን ብናወራ ምን ይሆናል? ____________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ወ. በህፃናት ፊት ብናማ በእነርሱ ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ዐ. እርስ በእርሳችን የመተማማት አዝማሚያ ያለን ለምን ይመስልዎታል? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ዘ. ፍቅር በቃላት ብቻ አይገለጽም? ሌላ ምን ያስፈልጋል? ____________________

____________________________________________________________

______________________________________________
______________________________________

ዠ. ፍሬያማ የሆነ የማህበረሰብ እንቅስቃሴና ተግባር ለማራመድ እጅግ ወሳኙ ነገር ምድን ነው?______________________________
______________________________________________
______________________________________________
__________________________________

የ. ፍሬያማ የሆነ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ ዋነኞቹ እንቅፋቶችን ይጥቀሱ? ________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________

Å. U¡¡`” ›eSM¡„ Ÿ}cÖ¨< Øpe LÃ nLƒ uS¨<cÉ ¾T>Ÿ}K<ƒ” N[Ô‹ ÁTEK<::

- ለምክክር አንድ ላይ በምንሰበሰብበት ጊዜ ፊቶቻችንን ወደ ____________ ____________ማዞርና ______________________ እርዳታን መጠየቅ አለብን::
- ከዚያም በኋላ በከፍተኛ ______________________________ ________________ ______________________ እና ____ ____________________ ሃሳቦቻችንን መግለጽ መጀመር አለብን::
- የራስ ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኙ ______________________ በመጨረሻ ወደ________________ ______________ ስለሚመራና ________________ እንዲቀር ስለሚያደርግ ____________ ____________ ______________ ______________ ____________ ማለት ሳይሆን ______________________ ____________ ______________ ______________ አለብን::
- በሙሉ ነፃነት ____________ ______________ ______________ አለብን::
- እንዲሁም ማንኛውንም ________________ ______________ ማቃለል የለብንም::
- የሃሳብ ልዩነት ቢፈጠርም ______________ ______________ ያገኘ ው ሃሳብ መጽናት አለበት ሁላችንም ______________________ ____________ እና ________________ አለብን::

2. የአንድ ማህበረሰብ አማኞች በመተባበር መንፈስ ሊያካሂዷቸው ከሚችሏቸው የባሃኢ እንቅስቃሴዎች ጥቂቶቹን ይዘርዝሩ:- ______________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
__________________________

3. በባሃኢ ማኅበረሰብ ውስጥ ካሉዎት ባልንጀራዎችዎ መካከል አንዳንዶቹን ይዘርዝሩና ከእምነቱ ግልጋሎት መስክ እያንዳንዳቸውን እንዴት ሊረዱዋቸው እንደሚችሉ ያሰላስሉ:: ______________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

## ምዕራፍ 5

በባሃኢ ማህበረሰብ ሊኖር ስለሚገባው አንድነት ከአቶ ከበደና ከባለቤታቸው ጋር ውይይት ሲያደርጉ የሚቀጥለው ጉብኝትዎ መወያያ ጭብጥ ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ ይሆንልዎታል። ወ/ሮ ደመቀች በርዕሱ በተለይ በመመሰጥ ባሃኢዎች በይበልጥ አንድነታቸው እየዳበረ እንዲሄድ በጋራ ተሰባስበው መጸለይና ቅዱሳን ፅሁፎችን ማንበብ ይገባቸዋል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል። አንድነት ሲባል አብሮ በደስታ ጊዜ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን በጋራ መሥራትና መገንባት ነው ሲሉ አቶ ከበደም ጨምረውበታል። “ይሁንና የማህበረሰብ እቅዶችን ለማስፈጸም ገንዘብ ያስፈልጋል” ካሉ በኋላ “ለምን ለእምነቱ ገንዘብ እንድናዋጣ ተጠይቀን እንደማናወቅ አይገባኝም። ሐብታሞች ነን ማለቴ አይደለም። ሆኖም ከዚህ በፊት ለቤተ ክርስቲያን መዋጮ እናደርግ ነበር። የመዋጮአችንን ማነስ ሳይመለከቱ ይቀበሉን ነበር።” በማለት ምሬት የተቀላቀለበት አስተያየት ሰጡ። በጉዳዩ ትንሽ በመደናገጥም “የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓልና የባሃኢ መዋጮ” በተሰኘ ርዕስ ላይ ከአቶ ከበደና ከባለቤታቸው ጋር ውይይት ለማድረግ ለመዘጋጀት ውሳኔ ላይ ደረሱ። ኤደን ተጨማሪ ሁለት ሳምንታት ከአያቶቿ ጋር ለማሳለፍ ስለወሰነች በሚቀጥለው ጉብኝትዎ ጊዜ ስለመዋጮ ጥቂት ንግግር እንድታቀርብ ረዷት።

በቀጣዩ ጉብኝትዎ ቀን ውይይቱን ለመጀመር ሁላችንም ከተሰናዳችሁ በኋላ “ስብሰባን አስመልክቶ ወ/ሮ ደመቀች የተናገሩት በጣም አስፈላጊ ነው። የምትፈቅዱልኝ ከሆነ የባሃኢን ስብሰባዎች በተለይም የአስራ ዘጠነኛ ቀን በዓልን አስመልክቶ አንዳንድ ነጥቦችን ለመሰንዘር እወዳለሁ። አቶ ከበደ መዋጮን አስመልክተው ያቀረቡትን አስተያየት አስመልክቶ ኤደን አጭር ንግግር እንድታዘጋጅ ጠይቂያት ተዘጋጅታለች። ንግግሯን ካዳመጥን በኋላ በጉደዩ ላይ ውይይት እናደርጋለን።” ካሉ በኋላ የባሃኢ ስብሰባዎችን አስመልክቶ የተያያዙ ሐሳቦችን የያዙ ጥቅሶችን በመዘርዘር ተሳታፊዎቹ በቅጥሶቹ መልእክት ላይ እንዲወያዩ ረዷቸው። ከዚህ ቀጥሎ በውይይቱ ሊያካትቷቸው ከሚችሉ ሐሳቦች ጥቂቶቹ ቀርበዋል።

- በአንድ የባሃኢ ማህበረሰብ አማኞች ለተለያዩ ምክንያቶች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከሌሎችም ጋር በተደጋጋሚ ይገናኛሉ። ከእነዚህም ምክንያቶች መካከል መጸለይ፥ ጽሁፎችን ለማጥናት፥ እምነቱን ለማስተማር፥ በአላትን ለማክበር፥ በማህበረሰቡ ጉዳይ ላይ ለመመካከር፥ እቅዶችን ለማንደፍ፥ እቅዶቻቸውን ለማስፈጸምና ከተባበረ ተግባራቸው ምን እንደተማሩ ለማወቅና እንዴትስ ሊያሻሽሉ እንደሚገባ ለመምከር ጥቂቶቹ ናቸው። ከዚህም ሌላ ባሃኢዎች አብረው በፍቅርና አንድነት ጊዜን ለማሳለፍ ይገናኛሉ። ሁልጊዜ ማስታወስ የሚገባን ቁም ነገር የባሃኢ ስብሰባዎች መንፈሳዊ ይዘት እንዳላቸውና በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊ ኃይል የተሞላ መሆናቸውን ነው።

በሃኦላህ እንዲህ ይላል:-

“በሕይወቴና በእምነቴ! የእግዚአብሔር ወዳጆች በሚገቡበት ከውስጡም ጌታን ሲያመሰግኑና ሲያወድሱ ጩኸታቸው ከሚሰማበት በማንኛውም መኖሪያ ቤት ዙሪያ፣ የእውነተኛ አማኞች ነፍሶችና የተመረጡ መላእክት ሁሉ ይዞራሉ።”[22]

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል:-

“ለአንድነትና ለስምምነት የተዘጋጀ እያንዳንዱ ስብሰባ ባእድን ወደ ወዳጅ፥ ጠላትን ወደ ጓደኛ ለመለወጥ አመቺ ይሆናል፣ አብዶል በሃም በሙሉ ልቡ በዚህ ስብሰባ ላይ ይገኛል።”[23]

- ምንም እንኳን የተሰብሳቢዎቹ ቁጥር ትንሽ ቢሆንም እንዲህ አይነቱ መንፈሳዊ ስብሰባ የሚካሄድባቸው ቤቶች ሊገለጽ የማይችል በረከት ይሰባሉ።

አብዶል በሃ ለአንድ አማኝ እንዲህ በማለት ጽፏል፡፡

"ቤትህን በየጊዜው ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ፍጹም ክብር የተመላውን ጌታ በማወደስ ተግባር ላይ በሚሰማሩበት በባሃኢዎች ስብሰባ ለማሸብረቅ ሃሳብ እንዳለህ ሰምተናል... ይህን ብታደርግ ያ መድራዊ ቤት የመንግስተ ሰማይ ቤት ያም የድንጋይ ውቅር የመንፈስ ምክር ቤት እንደሚሆን እወቅ፡፡"[24]

- የባሃኢ ጽሁፎችን አማኞች በተሰበሰቡበት ማንበብ የትልቅ ደስታ ምንጭና ለእምነቱም እድገት አስፈላጊ ነው፡፡ በሃኦላህ ተከታዮቹን እንዲህ ሲል አዟል፡-

"ወዳጆች በማንኛውም አገር ቢሆኑ በስብሰባዎች በአንድ ላይ መገናኘት፥ በዚያም (ስብሰባ) በጥበብና በአንደበተ ርቱዕነት መናገር፥ የእግዚአብሔርንም ጥቅሶች ማንበብ አለባቸው፤ የፍቅርን እሳት የሚለኩሱትና እንዲንበለበል የሚያደርጉት የእግዚአብሔር ቃላት ናቸውና፡፡"[25]

አብዶል በሃ ይህንን ጽፏል፡-

"ያቺ ከተማ በእውን ብርሃን እንድትብራ፥ ያም አገር በቅዱስ መንፈስ ኃይል እውነተኛ ነገት እንዲሆን፥ ስብሰባዎች በማድረግ የመንግሥተ ሰማይን ትምህርቶች አንብቡ አዚሙአቸውም፤ ምክንያቱም ይህ ዑደት ክብር የተመላው ጌታ ዑደት ስለሆነ፤ የሰው ዘርም ዓለም አንድነትና ኅብረት ጣፋጭ ዜማ ለምሥራቁም ለምዕራቡም ጆሮዎች መድረስ ይኖርብታል፡፡"[26]

- በባሃኢ ስብሰባዎች ወቅት የአማኞች ውይይት ሙሉ በሙሉ በመንፈሳዊ ጉዳዮችና በእምነቱ እድገት ላይ ማተኮር አለበት፡፡

አብዶል በሃ እንዲህ ብሏል፡-

"በዛሬው ጊዜ ሁላቸውም ስለሌላ ስለማንኛውም ነገር ማንሣትን መተው፤ እንዲሁም ሁሉንም ነገሮች መርሳት ይገባቸዋል... ሃሳቦቻቸውን ሁሉ፥ ቃሎቻቸውንም ሁሉ የአግዚአብሔርን ሃይማኖት በማስተማርና የእግዚአብሔርን እምነት በማስራጨት፥ ሁሉንም ራሳቸውን በእግዚአብሔር ባሕርያት ተለይተው የታወቁ እንዲሆኑ በማነቃቃት፥ የሰውን ዘር በማፍቀር፥ በሁሉም ነገሮች ንጽህና ቅዱስ በመሆን ፥ በመኅበራዊም ሆነ በግል ሕይወታቸው ጉድፍ የሌለባቸው በመሆን ትክክለኞችና የተላቀቁ፥ የነደዱም፥ የተቀጣጠሉም በመሆኑ ላይ ያትኩሩ፡፡

- ከባሃኢ ስብሰባዎች ሁሉ የአስራ ዘጠኝ ቀን በመባል የሚታወቀው አማኞች በአስራ ዘጠኝ ቀናት አንድ ጊዜ የማያደርጉት ስብሰባ ልዩ ቦታ አለው፡፡ የባሃኢ የቀን መቁጠሪያ አስራ ዘጠኝ ቀናት ያሏቸው አስራ ዘጠኝ ወራት አሉት፡፡ አማኞች ይህንን ወርሃዊ ስብሰባ እንዲያከብሩ በሃኦላህ እራሱ አዟቸዋል፡፡

"የሚቀርበው ውሃ ብቻም እንኳ ቢሆን፥ በእውነቱ በየወሩ አንድ ጊዜ ግብዣ (የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓል) እንድታደርጉ ታዛችኋል ምክንያቱም በምድራዊውም በመንግሥተ ሰማያዊውም ሃብት (ሁሉ) አማካይነት ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር የሰዎችን ልቦች ለማስተሳሰር አቅዷልና፡፡"[28]

- የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓል ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የፀሎትና የምንባብ ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ፀሎቶች ይደረጋሉ፡፡ ከእምነቱ ቅዱሳን ጽሁፎች አንዳንድ ክፍሎች ይነበባሉ፡፡ ሁለተኛው የአስተዳደር ክፈለ ጊዜ ሲሆን አማኞች ሶስተኛው ደግሞ ማህበራዊ ክፍለ ጊዜ ሲሆን ከውሃ ጀምሮ አቅም በፈቀደ መጠን የሚገባበዙበትና እርስ በእርስ የሚቀላቀሉበት ክፍለ ጊዜ ነው፡፡
- የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓል የፀሎትና የምንባብ ክፍል ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ከሚከተሉት የአብዶል በሃ ቃላት መረዳት ያቻላል፡፡

"እናንተ የጥነታዊው ውበት ታማኝ አገልጋዮች ሆይ! በእያንዳንዱ ዑደትና የሃይማኖት ዘመን ግብዣ የተመረጠና የተወደደ ነበር፤ ለእግዚአብሔር አፍቃሪዎችም ገበታ መዘርጋት እንዲያስመሰግን ተግባር ሲቆጠር ነበር፡፡ በተለይም በዛሬው ጊዜ፥ ይህ (የአሥራ ዘጠነኛው ቀን

ግብዣ) እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማወደስ ከሚደረጉት ስብሰባዎች መካከል እንደ አንዱ ስለሚቆጠር፥ በዚህ ከወደር በላይ በሆነው ግልጸት ዘመን፥ በዚህ ከዘመናት ሁሉ በላይ በረከት በተመላው ዘመን፥ ይህ እውነት ነው:: እዚህ ቅዱሳን ጥቅሶች፥ መንግሥተ ሰማያዊዎቹ ቅኔዎችና ውዳሴዎች ይዜማሉ፥ ልብም ትቀሰቀሳለች ከራስዋም ተላቅቃ ትነጠቃለች::"[29]

- በበዓሉ የአስተዳደር ክፍለ ጊዜ አማኞች የቅርብና የሩቅ የባሃኢ ማህበረሰቦች ስለሚያደርጉት እንቅስቃሴዎች ሪፖርቶችን ያዳምጣሉ፤ በማህበረሰባቸው ውስጥ ስላለ የእምነቱ ጉዳይና እድገት ይመካከራሉ፤ ከዓለም አቀፍ ቤተፍትህ ከሚመጣ እድገት ይመካከራሉ፤ ከዓለም አቀፍ ቤተፍትህ ከሚመጣ መመሪያ ጋር ይተዋወቃሉ፤ የአካባቢ መንፈሳዊ ጉባኤያቸው እንዲመክርበት፤ ካልሆነም ወደ ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ወደ ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ እንዲተላለፍ የሚፈልጓቸውን ሐሳቦች ያቀርባሉ:: እያንዳንዱ አማኝ በዓለም አቀፍ የባሃኢ ማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ የሚካፈለው በዚህ መንገድ ስለሆነ የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓል ምክክሮች በጣም አስፈላጊ ናቸው::
- የበዓሉ የማህበራዊ ክፍለ ጊዜ የወዳጅነት፤ የመገባበዣና የፍቅር መለዋወጫ ጊዜ ነው:: መዝሙር ይደመጣል፤ አነቃቂ ንግግሮች ይደረጋሉ፤ ሕፃናት ዝግጅቶች ያቀርባሉ፤ በአጭሩ ማህበረሰቡ ባለበት ባህል ክብሩን ሳይነካ ደስታን ሊያመጡ የሚችሉ ዝግጅቶች በጥንቃቄ ተመርጠው ይቀርባሉ::
- የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓል የእምነቱ አስተዳደር ስርዓት ልዩ ገጽታ ነው:: የማህበረሰቡን አምልኮአዊ፤ አስተዳደራዊና ማህበራዊ ሕይወትን ያዋህዳል:: የበዓሉ ስኬታማነት የሚወሰነው እነዚህ ሶስት ክፍሎች ሚዛናቸውን ሲጠብቁ በመሆኑ ለሁሉም እኩል አትኩሮት ሊሰጣቸው ይገባል:: በነሐሴ 1980 ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ ለበሃኦላህ ተከታዮች በሙሉ በጻፈው መልእክት እንዲህ ብሏል፡-

"የበሃኦላህ የዓለም ሥርዓት ሁሉን የሰው ኅብረተሰብ ክፍሎች ያጠቃልላል፤ መንፈሳዊውን፤ አስተዳደራዊውንና ማኅበራዊውን የሕይወት ሂደቶች ያዋህዳል፤ በተለያዩ መንገዶች የሚገለጹትን የሰው አስተሳሰቦች ለአዲስ ስልጣኔ ግንባታ በሚጠቅሙበት አቅጣጫ ይመራቸዋል:: አሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል እነዚህን ገጽታዎች ሁሉ የኅብረተሰቡ መሰረት በሆነው ደረጃ ያቅፋቸዋል:: በመንደሮች፥ በአምባዎች፥ በከተሞች የሚሠራ፥ ሁሉም የባሃ ሕዝብ አባላት አባል የሆነበት ተቋም ነው:: አንድነትን ለማጎልበት፥ ዕድገትን ለማረጋገጥ፥ እና ሐሴትን ከፍ ከፍ ለማድረግ የታቀደ ነው::"[30]

- ይህን ያህል ደረጃ ያለው በዓል በጥድፊያ መዘጋጀት የለበትም:: እያንዳንዱ የበዓሉ ተካፋይ በፀሎትና በማሰላሰል በመታገዝ ራሱን ማዘጋጀት አለበት:: በበዓሉ ጊዜ ፀሎት በማድረግም ሆነ የሚነበቡትን ቅዱሳን ጽሁፎች በማዳመጥ፥ ሪፖርት በማቅረብ፥ መመሪያዎችን በመቀበል፥ አስተያየቶችን በመስጠት፥ መስተንግዶን በማድረግም ሆነ በፈገግታና በደስታ መስተግንዶን በማቀበል ልብንና አእምሮን አሰባስቦ ለመሳተፍ መዘጋጀት ያስፈልጋል:: የአስራ ዘጠኝ ቀን በዓልን አስመልክቶ በጻፈው መልእክት ዓለም አቀፍ ቤተፍትህ እንዲህ ብሏል፡-

"ለበዓሉ ዝግጅት አስፈላጊ ገጽታዎች ተስማሚ ምንባቦች በመመረጥ፥ ጥሩ አንባቢዎችን አስቀድሞ መመደብን፥ በጸሎትና በምንባብ አቀራረቡና በአቀባበሉ መንፈሳዊ ኘሮግራም ውስጥ ተገቢ ሥርዓትን እንዲኖር ማድረግን ያካትታል:: የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓሉ በሚደረግበት አካባቢ፥ ቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ ትኩረት መስጠቱ የሚገኘውን ትዝታ በእጅጉ ያዳብራል:: ንጽህና፥ ሥፍራውን ለአከባበሩ በሚያመችና በተዋበ ሁኔታ ማዘጋጀቱ ሁሉ ጉልህ ሚና አላቸው:: ሰዓት ማክበሩም የመልካም ዝግጅት መመዘኛ ነው::

"ለበዓሉ አከባበር መሳካት በአብዛኛው በእያንዳንዱ አማኝ ዝግጅትና ተሳትፎ ጥራት ይወሰናል:: ተወዳጁ ጌታ (አብዶል በሃ) የሚከተለውን ምክር ሰጥቷል:: እነዚህ በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ የጌታ የተዳጀችና የምሕረተኛው ሴት አገልጋዮች ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር መግንሥት እንዲያዞሩ፤ ምቁራባትን እንዲያዜሙ፥ የእግዚአብሔርን እርዳታ እንዲማፀኑ፥ በሐሴት እርስ በርሳቸው እንዲዋደዱ፥ በንጽህናና በቅድስና፥ በፈሪሃ እግዚአብሔር፥ ምድራዊ ብርቱ ስሜትንና

እኔነትን በመግታት ተግባር እንዲያድጉ፥ ለአሥራ ዘጠኝ ቀን በዓል ስብሰባዎች ትልቅ ክብደት እንዲሰጡ። በዚህ ሁኔታ ራሳቸውን ከዚህ ዓለም በማላቀቅ፥ በመንፈስ ግለት እሳት ውስጥ ይሰጥማሉ።"[31]

***መልመጃዎች***

**1.** እንደተለመደው ከላይ የተሰጠውን ምንባብ በቡድናችሁ ውስጥ በተደጋጋሚ አንብባችሁ ከተወያያችሁባቸው በኋላ በራስዎ ቃላት ለመግለጽ ይሞክሩ። ከዚህ በታች ያሉት ጥያቄዎች በዚህ ምእራፍ የተሰጡትን ጥቅሶች የበለጠ ለመረዳት ይረዱዎታል።

ሀ/ ወዳጆች ተሰባስበው አምላክን የሚያወድሱና የሚያመሰግኑባቸው እያንዳንዱ መኖሪያን ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው? ____________________

ለ/ ለአንድነትና ለሰላም ዓላማ የሚደረጉ ስብሰባዎች ከሚኖራቸው ውጤቶች ጥቂቶቹን ይጥቀሱ፡____________________

ሐ/ አምላክን ለማወደስ አማኞች በየጊዜው የሚገናኙበት ቤት "መንግሥተ ሰማያዊ ቤት" እንደሚሆን አብዶል በሃ ይነግረናል። "መንግሥተ ሰማያዊ ቤት" የሚለው ሐረግ በአእምሮዎ ምን እንዲቀረጽ ያደርጋል?____________________

መ/ አንድ ላይ ለመሰብሰብ ስንመጣ ማድረግ ያለብን በ__________ እና በ__________ መናገር የ __________ ማንበብ አለብን። በዛሬው ጊዜ ስለ __________ ስለ__________ __________ እና ሃሣቦቻችንን ሁሉ ቃሎቻችንንም ሁሉ የእግዚአብሔር ሃይማኖት __________ እና የአምላክን እምነት__________ ሁሉም ራሳቸውን በእግዚአብሔር ባህሪያት __________ __________ እንዲሆኑ __________ የሰውን ዘር__________ በሁሉም ነገሮች__________ እና __________ በመሆን __________ ሆነ __________ __________ የሌለብን መሆን __________ __________ እና የ__________የ__________ የ__________ በመሆን ላይ ማተኮር አለብን።

ረ/ በባሃኢ የቀን መቁጠሪያ ስንት ወር አሉ? ____________________

ሰ/ በእያንዳንዱ የባሃኢ ወር ስንት ቀናት አሉ?____________________

ሸ/ ባሃኢዎች በየወሩ የሚያደርጉት ልዩ ስብሰባ ምንድን ነው? ________________

________________

ቀ/ የአስራዘጠኝ ቀን በዓል ሶስት ክፍሎች እነማን ናቸው ? ________________

________________

በ/ እነዚህን ሶስት ክፍሎች በፈለግነው ቅደም ተከተል ማድረግ እንችላለን? ________________

________________

ተ/ የበዓሉ የፀሎትና የምንባብ ክፍል አላማ ምንድን ነው ? ________________

________________

ቸ/ የበዓሉ አስተዳደራዊ ክፍል ዓላማ ምንድን ነው? ________________

________________

ኀ/ የበዓሉ ማህበራዊ ክፍል ዓላማ ምንድን ነው? ________________

________________

ነ/ በበዓሉ የአስተዳደር ክፍል ጊዜ ልንወያይባቸው የምንችላቸው ርዕሶች ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

- የአካባቢ የማስተማር ዘመቻ ሂደት ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የመዋጮ አስፈላጊነት ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን ውጤት ይቻላል☐ አይቻልም☐
- በሁለት የባሃኢ ማህበረሰብ አባላት መካከል የተነሳ አለመስማማት የሚወገድበት መንገድ ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የማህበረሰቡ አባላት የባሃኢ ማዕከሉን ኘሮግራም ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ የአቅኚነት ግብ ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የባሃኢ ማህበረሰብ ሕፃናት ትምህርት ይቻላል☐ አይቻልም☐
- የመንደሩ ወይም የከተማው ሕፃናት ትምህርት ይቻላል☐ አይቻልም☐
- አንድ የማህበረሰቡ አባል ባለፈው ሳምንት ቅዱሳን ጽሁፎችን ሲያጠና ያልገባው የአንድ ምንባብ ትርጉም ይቻላል☐ አይቻልም☐

2. ሶስቱ የበዓሉ ክፍሎች ሚዛናቸውን መጠበቅ የሚገባቸው ለምንድን ነው? በቡድንዎ ውስጥ ተወያዩበት።
3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያብራሩ፡-

ሀ/ በዓሉን የሚያስተናግዱት እርስዎ ቢሆኑ ለበዓሉ እንዴት ይዘጋጃሉ። ________________

________________

ለ/ በበዓሉ ላይ ተካፋይ ብቻ ቢሆኑ ለበዓሉ እንዴት ይዘጋጃሉ:: ______________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

4. በምንባቡ መሰረት ለውይይቱ ርዕስ የመረጡት በአቶ ከበደና በወ/ሮ ደመቀች አስተያየት ላይ በመነሳት ነበር:: ይህንን በማድረግም አንድ ባሃኢ አስተማሪ ሊኖሩት ከሚገቡ ዋነኛ ባህሪያት አንዱ እንዳለዎት አሳይተዋል:: ይህም ባህሪይ የሚያስተምሩትን ሰው በጥንቃቄ ማዳመጥና ችግሮቹንና ፍላጎቶቹን ማወቅ ከዚያም ለችግሮቹና ፍላጎቶቹ መልስ የማሆኑ እውነታዎች ከቅዱሳን ጽሁፎች ማካፈል ነው:: የአንድ ጥሩ አድማጭና የሌሎች ችግሮች የሚሰማው ሰው ከሚያንፀባርቃቸው መንፈሳዊ ባሕርያት ጥቂቶቹን ይጥቀሱ:: ______________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 6

ስለባሃኢ ስብሰባዎችና የአስራዘጠኝ ቀን በዓል ያደረጋችሁት ሰፋ ያለ ውይይት ጊዜ ስለወሰደባችሁ ስለመዋጮ ለመነጋገር የተረፋችሁ ጊዜ ትንሽ ነበር:: ባደረጋችሁት ውይይት በጣም የተቀሰቀሰችው ኤደን ከአያቶቿ ጋር ጥቂት ተጨማሪ ቀናት ስለምትቆይ ስለመዋጮ የምታቀርበው ዝግጅት ለሌላ ቀን እንዲተላለፍ ሐሳብ ስታቀርብ ቀለል አለዎት:: ይህም ኤደን በእርስዎ እርዳታ ያሰፈረቻቸው የሚከተሉት ሐሳቦች ላይ ክለሳ ለማድረግ እንድትችሉ እድል ሰጥቷችሁ ነበር::

እኛ ባሃኢዎች ልንገነባው የምንጥረው ስልጣኔ በቁሳዊና በመንፈሳዊ ጎኑ የበለፀገ ነው:: ሐብት ተቀባይነትን የሚያገኘው አንዳንድ ነገሮች ከተሟሉ ብቻ ነው:: በመጀመሪያ በሐቀኝነት ላይ በተመሰረተ ሥራ መገኘት አለበት:: ከዚያም ለሰው ልጅ ደህንነት መዋል ይገባዋል:: አብዛኛ ው ሕዝብ ለህይወት የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ነገሮች ሳያገኝ ጥቂቶች ከመጠን ያለፈ ሐብት ማካበት ተቀባይነት የለውም:: መላው ማህበረሰብ መሻሻል ይኖርበታል::

ከፍትህ አልበኝነትና ከችግር የተላቀቀ ህብረተሰብ ለመገንባት ለጋሾች መሆን አለብን:: እውነተኛ ብልጽግና ሊገኝ የሚችለው በመለገስ ብቻ በመሆኑ የነጣን ድሆች ብንሆንም እንኳን ለሰው ዘር እድገት ትንሽ ነገር ልናበረክት እንችላለን:: ልግስና የሰው ነፍስ ባህሪይ እንጂ ከድህነት ወይም ከሐብት ጋር የተያያዘ አይደለም::

በህቡዓተ ቃላት ውስጥ በሃኦላህ እንዲህ ይላል:-

"*መስጠትና መቸር የእኔ ባህርያት ናቸው በባህሪያቴ ራሱን ያስጌጠ የበጀው ነው::*"[32]

*ያከማቸነው ማንኛውም ሐብት እውነተኛ ምንጭ ቸሩ አምላክ እንደሆነ ማስታወስ አለብን:: ለመኖር የሚያስፈልጉንን ነገሮች ይሰጠናል፣ ለማደግ እንድንችል ያመቻችልናል::* ስለዚህ ለባሃኢ መዋጮ በመናደርግበት ጊዜ እርሱ ከሰጠን ውስጥ የተወሰነውን ለእምነቱ እናውላለን ማለት ነው:: በመሆኑም ለባሃኢ መዋጮ መስጠት ልግስና ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ በረከትና ትልቅ የግል ኃላፊነትም ጭምር ነው:: ካካበትነው ሐብት ራሱን ያለማቋረጥ ባዶ በማድረግ ከማይታይ

ምንጭ ያለማቋረጥ እንደሚሞላ ምንጭ መሆን እንደሚገባን ሞግዚቱ ይነግረናል፡፡ በተለያየ ደረጃ የእምነቱን ሥራ የሚያግዙ ብዛት ያላቸው የባሃኢ መዋጮ አይነቶች አሉ፡፡ ለአካባቢው መዋጮ፥ ለብሔራዊ መዋጮ፥ ለአህጉራዊ መዋጮ፥ ለዓለም አቀፍ መዋጮ በመባል ይታወቃል፡፡ ግለሰቡ አማኙ ለፈቀደው መዋጮ መስጠት ይችላል፡፡ በእነዚህ መዋጮዎች መሳተፍ የሚችሉት ግን ባሃኢዎች ብቻ ናቸው፡፡ መዋጮ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በተጨማሪም መዋጮ በሚያዋጣው ሰውና በተቋማቱ መካከል ብቻ የሚቀር በመሆኑ ምስጢራዊ ነው፡፡ በሌሎች እምነቶች አማኞች እንዲያዋጡ የሚደረገው ከመጠን ያለፈ ግፊት በባሃኢ እምነት የለም፡፡ ተቋማቱ ስለመዋጮ ምንነትና የገንዘብ ፍላጎታቸውን በመግለጽ ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ ማህበረሰብ ለእራሱ የመዋጮ ግብ ያደርጋል፡፡ ይሁንና እያንዳንዱ ግለሰብ ምን ያክል ማዋጣት እንዳለበት አይወሰንለትም እንዲሰጥም አይጠየቅም፡፡ ስለመዋጮ ባላቸው መረዳት ላይ ተመስርተው ለተለያዩ የመዋጮ ዓይነቶች ምን ያክል ማዋጣት እንደሚገባቸው መወሰን ለግለሰብ አማኞቹ የተተወ ድርሻ ነው፡፡

"ምን ያክል ማዋጣት እንደሚገባን ማንም ካልነገረን ከእኛ ምን ያክል እንደሚጠበቅ በምን እናውቃለን? እምላክስ ለእምነቱ በምናደርገው መዋጮ ይደሰት አይደሰት እንዴት እናውቃለን? ብለው እራስዎን ይጠይቁ ይሆናል፡፡ የዚህ ጥያቄ መልስ በአንዲት ሐረግ ውስጥ ይገኛል፡፡ የመስዋዕትነት ምስጢር፡፡ በባሃኢ እምነት ምንም ገቢ ከሌለው አማኝ የተዋጣች አንዲት ሳንቲም ከሐብታም አማኝ ከተዋጣ ብዙ ገንዘብ ጋር እኩል ክቡር ልትሆን ትችላለች፡፡ የአንድን መዋጮ ዋጋ የሚወስነው በማዋጣቱ የተደረገው መስዋዕትነት ነው፡፡ ለእምነቱ ምን ያክል ማዋጣት እንዳለብን ለመወሰን እያንዳንዳችን በልባችን ስለመስዋዕትነት ማሰላሰል ይገባናል፡፡

ለአምላክ እምነት መስዋዕትነቶችን በምንከፍልበት ጊዜ እርሱን ለመጥቀም እንዳላደረግነው ማስታወስ አለብን፡፡ አምላክ የእኛ እርዳታ አይፈልግም፡፡ የምናደርገው መዋጮ መልካም ዓለምን ለመገንባት የሚውል ነው፡፡ መስዋዕትነትም ማለት ዝቅተኛውን ነገር ሰጥቶ፣ ከፍተኛውን ነገር መቀበል ነው፡፡ መስዋዕትነት ስናደርግ የተጎዳን ሊመስለን ይችላል፡፡ በእውነቱ ግን መስዋዕትነት እውነተኛ ደስታን ያመጣል፡፡

አብዶል በሃ እንዲህ ብሏል፡-

"የመስዋዕትነት ምስጢሩ ሰው የራሱን ሁኔታዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር መለኮታዊ ደረጃ መሰዋዕት ማድረግ እንዳለበት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ደረጃ ምሕረት፥ ደግነት፥ ይቅር ባይነት፥ መስዋዕትነት፥ ችሮታ፥ ጸጋ፥ እንዲሁም ለመንፈሶች ሕይወት መስጠትና በልቦችና በደምሥሮች ውስጥ የእርሱን ፍቅር እሳት ማቀጣጠል ነው፡፡"[33]

***መልመጃዎች***

1. ኤደን ስለመዋጮ ያደረገችውን ንግግር እንድታዘጋጅ ሲረዷት በቅደም ተከተል ልታስተላልፋቸው የሚገቡ ነጥቦችን ጠቁመዋት ይሆናል፡፡ ከላይ በተሰጠው ምንባብ ውስጥ የተላለፉ ነጥቦችን በቅደም ተከተላቸው ይዘርዝሩ፡ ______________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________
______________

2. በአስጠኚዎ እርዳታ "መስጠት የብልጽግና መንፈሳዊ መሰረት በሚል ርእስ አጭር ንግግር አዘጋጁ፡፡

## ምእራፍ 7

ወደ አዲስ አማኞች ቤት የሚያደርጉት ቋሚ ጉብኝት ትልቅ የደስታ ምንጭ ሆኖልዎታል፡፡ በእርግጥ ሁሉም አዲስ አማኞች የአቶ ከበደንና የቤተሰባቸውን ያህል ለውይይቱ የጋለ ምላሽ አልሰጠዎትም፡፡ እንዲያውም አንድ ቤተሰብ እምነቱን የተቀበሉት በችኮላ ነው ብለው ስላሰቡ በውይይቱ ለመቀጠል እንደማይፈልጉ የማያሳይ ግልጽ ምልክት ሰጥቶዎታል፡፡ ሁለት ወይም ሶስት አዲስ አማኞችን ለመተዋወቅ ዕድል በማግኘትዎ በፊት ሰፈር ቀይረዋል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ብዛት ያላቸው አማኞች በእምነቱ ጥልቀት እንዲያገኙ ከመርዳትዎ በተጨማሪ ስልት ያለው የማስተማር ጥረት አስደናቂ ፍሬዎችን ሲያሳይ ተመልክተዋል፡፡ በድካምዎ ውጤት በመበረታታት አዲስ አማኞች በእርስዎ ጉብኝት ላይ ያላቸው ጥገኝነት እንዲቀንስ ወሳኝ እርምጃ ለማድረግ ይወስናሉ፡፡ "ቀጣዩ ጥቂት አማኞችና እነዚህ አዲስ አማኞች በሳምንት አንድ ጊዜ ተሰባስበው ጽሁፎቹን የሚያጠኑበት ቋሚ ስብሰባ የመሰየሚያ ጊዜ አሁን አይደለም?" ሲሉ ራስዎን ይጠይቃሉ፡፡ "እራሳቸው በቀጥታ ከጽሑፎቹ ጋር ካልተገናኙና ከማህበረሰቡ ጋር ካልተቀላቀሉ በቀር እምነቱን በማገልገል መንገድ በሁለት እግራቸው ሊራመዱ አይችሉም፡፡" በዚህ ጉዳይ ከጥቂት ቤተሰቦች ጋር ሲመካከሩ የጋለ አወንታዊ ምላሽ በማግኘትዎ ሐሳብዎ ትክክል መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ "ወደፊት የምንራመድበት ጊዜ አሁን ነው፡፡" አሉ ወ/ሮ ደመቀች፡፡ "የመጀመሪያውን ስብሰባችንን እዚህ ቤታችን ብናደርግስ?„

በቀጠሮው ቀን ሰባት ሰዎች በእነ አቶ ከበደ ቤት ተገኙ፡፡ ምንም እንኳን የተገኙት ሰዎች ቁጥር ትንሽነት ባይደሰቱም ስብሰባው በእውነተኛ መንፈሳዊ መንገድ ከተካሄደ ሌሎች ነፍሳትን እንደሚስብ ያደረጉትን ውይይት በማስታወስ ይጽናናሉ፡፡ ነገር ግን ለዚህ ስብሰባ መንፈሳዊ ሁኔታዎች መሟላታቸውንና እስከማለቂያውም መጠበቃቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይችላሉ? በአዲስ አማኞች ቤት በመገኘት በሚያደርጉት ውይይት ከእርስዎ ሌላ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ብቻ ስለሚካፈሉ የውይይቱን አቅጣጫ ለመቆጣጠር ችለዋል ለማለት ይቻላል፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች ግን እርስዎ ብዙ ጣልቃ ሳይገቡ ተሳታፊዎቹ ሐሳብ እንዲለዋወጡ መፍቀድ አለብዎ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብጥብጥ እንዳይፈጠርና አማኞቹ እንዳይወናበዱ አንድ ሰው ስብሰባውን ማቀለጣጠፍ እንዳለበት ተገንዝበዋል፡፡ "ሁሉም ነገር በስርዓቱ ይካሄዳል ብለን እንመን፡፡" ይላሉ ለራስዎ፡፡ እየሰራን እንማራለን፡፡ ደግሞ ውይይቱ በጽሁፎቹ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ከግባችን መድረሳችን አይቀርም፡፡"

በዚህ የመጀመሪያ ስብሰባ ለማጥናት የመረጧቸው ጥቅሶች ሁሉም ከማስተማር ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ስብሰባው ካበቃ በኋላ እያንዳንዱ የስብሰባው ተካፋይ ለማስተማር ቁርጠኛ ውሳኔ ላይ ይደርሳል ብለው ተስፋ አድርገዋል፡፡ እንደተለመደው ከማስተማር ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥቅሶችን መርጠው ተሳታፊዎቹ ጭብጡን በተሻለ መንገድ ሊረዱ ይችላሉ ባሉት የሃሳቦች ቅደም ተከተል አሰልፈዋቸዋል፡፡ እምነቱን ለማስተማር ያነሳሷቸዋል ያሏቸውን ጥቂት ነጥቦች ከማንሳት በቀር ብዙ ነጥቦችን ለመሸፈን አይከጅሉም፡፡ የተሳታፊዎች መብዛት ሃሳብዎን ለማስተላለፍ ከመረጡት ቅደም ተከተል እንዳያስወጣዎ ስብሰባውን በሚያቀለጣጥፉበት ወቅት ግትር መሆን እንደሌለብዎም አጢነዋል፡፡

- የማስተማር ዓላማ በንግግር ቁልፍ የሰዎችን ልቦች ለበሃኦላህ መክፈት ነው፡፡

በሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

"ከምድራዊ ርኩሰቶች ሁሉ ያነፃቸው ዘንድ፣ የአላማኒዎች እጆች ሊያረክሱዋቸው ከቶ ወደማይችሉት ወደ ተቀደሰው ነጥብ ለመቅረብም ያስችላቸው ዘንድ እርሱ ለይቶ ለራሱ ያደርጋቸው ነገሮች የሰዎች ልቦች ከተሞች ናቸው፡፡ ሕዝብ ሆይ፥ የሰውን ዘር ልብ ከተማ በንግግራችሁ ቁልፍ ክፈቱ፡፡ በዚህ ሁኔታ አዘናችኋል፡፡"[34]

- በዓለም ካሉ ሁሉ ትልቁ ኃይል አምላክ ቃል ኃይል ነው፡፡ በማስተማር ጊዜ የዚህ ለዋጭ ቃል ኃይል በአድማጩ ነፍስ ውስጥ መለወጥን ይጀመራል፡፡

በሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

“ከእነዚያ ይህንን እውነት ከሚረዱት ብትሆኑ ሆሮ ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣው እያንዳንዱ ቃል በእያንዳንዱ የሰው አካል አዲስ ሕይወትን በሚዘራ ኃይል የተመላ ነው፡፡”[35]

- ማስተማር በእያንዳንዱ አማኝ ላይ የተጣለ ቅዱስ ኃላፊነት ነው፡፡

“እግዚአብሔር የእርሱን እምነት የማስተማርን ተግባር ለእያንዳንዱ ሰው ሰጥቷል፡፡ ይህን ተግባር ለመወጣት የሚነሳ ማንም ሰው÷ የእርሱን መልእክት ከማወጁ አስቀድሞ ቃሎቹ የጥሪው ተቀባዮች ጌጥ ማስጌጥ ለበት፡፡

- የእምነቱ አስተማሪ የእውቀትን ብርሃን በሁሉም አቅጣጫዎች እንደሚፈነጥቅ ሻማ ነው፡፡ አብዶል በሃ በአንድ ወቅት አግኝቶት ለነበረ አማኝ ይህን ጽፏል፡-

“እንደ ሻማ ተቀጣጥለህ (ለሽ) እንደ እሳት እራትም በእግዚአብሔር ፍቅር እሳት ራስህን (ሽን) ስታነድ (ጂ) በፍቅርና በመሳብ ታላቅነት እንደ ደመና ስታለቅስ (ሺ) እንደ መስክ ስትስቅና (ቂና) እንደ ታዳጊ (ወጣት) ዛፍ በአብሃ (በላቀው ጌታ) ነገት ነፋስ ሽውታ ማርበብ ወደ ደስታ ተቀስቀስህ (ሽ) አይህ (ሽ) ዘንድ የዚህን ስብሰባ ውጤቶች እየተጠባበቅሁ ነኝ፡፡”

- የእምነቱ አስተማሪ የበሃኦላህን መልእክት በሁሉም አካባቢ ሲያደርስ እነደ ነፋስ አይገታም፡፡

በሃኦላህ እንዲህ ይላል፡-

“የእርሱን የመለኮታዊ መርሖ ጎህ እንዲቀድ የአደረገውን መልእክቱን በመታስተላልፍበት ጊዜ እንደ ነፋስ ያልተገታህ ሁን፡፡ ነፋስ ለዚያ አምላክ ላዘዘው ታማኝ በመሆን በምድር አካባቢዎች ላይ ሁሉ ሰው በሰፈረበትም በጠፉም ላይ እንዴት እንደሚነፍስ አስተውል፡፡ የባድማነት ትርኢት ወይም የልምላሜ ማስረጃዎች ሊያሳዝኑት ወይም ሊያስደስቱት አይችሉም፡፡ በፈጣሪው እንደታዘዘው በሁሉም አቅጣጫ ይነፍሳል፡፡ እያንዳንዱም አንዱንና እውነተኛውን አምላክ አፍቃሪ ነኝ ባይ እንዲሁ መሆን አለበት፡፡ ትኩረቱን በእሱ እምነት መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ በማድረግ እንዲስፋፋ በትጋት መሥራት አለበት፡፡ ሙሉ በሙሉ ለአምላክ ብሎ የእርሱን መልእክት ማወጅ በዚሁ መንፈስ ቃሎቹ በሰሚው ውስጥ የቀሰቀሱትን ማንኛውም ስሜት መቀበል አለበት፡፡ የሚቀበልና የሚያምን ዋጋውን ያገኛል፡፡ የማይቀበለው ግን ከራሱ ቅጣት በቀር ሌላ ምንም አያገኝም፡፡”[38]

- የእምነቱ አስተማሪ በፍቅር ኃይል በመሞላት በማይነጥፍ ኃይል በአምላክ መንገድ ይጥራል፡፡

አብዶል በሃ እንዲህ ይላል፡-

“ሊያጠናክራችሁ የሚጠባበቀውን የእግዚአብሔር ምህረት ስትጠይቁ ኃይላችሁ አሥር እጥፍ ይሆናል፡፡ እኔን ተመልከቱኝ፤ እኔ በጣም ደካማ ነኝ፤ ሆኖም ይህን መልእክት ለእናንተ ለመስጠት እንድችል የተደረገሁ ምስኪን የእግዚአብሔር አገልጋይ መጥቼ በመካከላችሁ ለመገኘት ብርታት ተሰጠኝ ከእናንተ ጋር ብዙ አልቆይም ሰው ስለ ራሱ ደካማነት ማሰብ የለበትም ለማስተማር ችሎታ የሚሰጠው የፍቅር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡ ስለ ራሳችን ደካማነት ማሰቡ ሊያመጣ የሚችለው ተስፋ መቁረጥን ብቻ ነው፡፡ ከምድራዊ ሃሳቦች ሁሉ በላይ መመልከት ከሁሉም ቁሳዊ ሃሳብ ራሳችንን ማላቀቅ ለመንፈሳዊ ነገሮች መጓጓት እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ለሚለው ትእዛዙ ሐሴት የተመላበት አገልግሎት ነፍሳችንን በደስታ ስሜት በሚሞላው በፍጹም ኃይሉ ቸርነት የተመላበት ዘለዓለማዊ ምህረት ላይ ዓይኖቻችንን ማተኮር አለብ፡፡”[39]

- ሁላችንም በድፍረትና በራስ በመተማመን እምነቱን ለማስተማር መነሳት አለብን፡፡ ማመንታት የለብንም፡፡

“ስለዚህ ተናገር በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ በታላቅ ድፍረት ተናገር፡፡ ንግግርህን ለማጀመር ትንሽ ጊዜ ሲቀርህ በመጀመሪያ ወደ በሃኦላህ ዞርና የመንፈስ ቅድስን ማረጋገጫ ጠይቅ ከዚያም በኋላ

አፍህን ከፍተህ በልብህ የመጣውን ማንኛውንም ነገር ይህ ግን በከፍተኛ ድፍረት ክብር እና እምነት ይሁን::"[40]

ሞግዚቱ እንዲህ ይላል:-

"የባሃኢ አስተማሪ ሙሉ በሙሉ ልበ ሙሉ መሆን አለበት:: የእርሱ ጥንካሬና የዓላማው መሳካት ምስጢር የሚገኘው እዚህ ላይ ነው:: ብቻህን ብትሆንም በዙሪያህ የሚገኙት ሰዎች ጥላቻ የቱንም ያህል ታላቅ ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር መንግሥት ሰራዊት በጎንህ መሆናቸውንና በእነርሱ እርዳታ በእግዚአብሔር እምነት ፊት የተደቀኑትን የጨለማ ሃይሎች ለማሸነፍ እምነት ያለህ መሆን አለብህ:: ስለዚህ አትሰልች ደስተኛና ልበ ሙሉ ሁን::"[41]

***መልመጃዎች***

1. ቅዱሳን ጽሁፎችን ለማጥናትና በዚያም ላይ ለመወያየት አማኞች በሚያደርጉት ስብሰባ ላይ አዘወትሮ መካፈል የባሃኢ ሕይወትዎ አስፈላጊ ክፍል ነው:: በእርስዎ ቡድን ካሉት ተሳታፊዎች ጋር ከላይ በተሰጡት ሐሳቦችና ጥቅሶች ላይ በመመሥረት ስለማስተማር ውይይት ያድርጉ:: ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ በወይይታችሁ ወቅት ከተነሱ ዋና ሐሳቦች መካከል ጥቂቶቹን ያስፍሩ:: ______________________________

2. እንደዚህ ያሉ ስብሰባዎች ሊያስገኙ ከሚፈለጉ ውጤቶች አንዱ እምነቱን በማገልገል መስክ ተሳታፊዎች በወደፊት ሕይወታቸው ሊፈጽሟቸው የሚገቡ የተግባሮች ዝርዝር ውሳኔ ላይ መድረስ ነው:: በስብሰባው ወቅት በተሳታፊዎች ከተደረሱ ውሳኔዎች መካከል ጥቂቶቹ ምንድን ናቸው? ______________________________

***የጥቅሶች ማመሣከሪያ***


***1.	ከበሃኦላህ ኀቡዓተ ቃላት አረብኛ ቁጥር 4***
***2.	ከበሃኦላህ ከባሃኢ ጸሎቶች የአሜሪካው ገጽ 4***
***3.	ከበሃኦላህ ጽሁፎች ቅስማት ቀጥር 4 ገጽ 6 የአሜሪካ እትም***
***4.	ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 134 ገጽ 290***
***5.	ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 45 ገጽ 99-100***
***6.	ከአብዶል በሃ የባሃኢ ጸሎቶች የአሜሪካው ገጽ 83***
***7.	ከላይ ከተጠቀሰው  ገጽ 102***
***8.	ከላይ ከተጠቀሰው  ገጽ 102***
***9.	ከበሃኦላህ የባሃኢ ጸሎቶች የአሜሪካው ገጽ 140***
***10.	ከአብዶል በሃ የባሃኢ ጸሎቶች የአሜሪካው ገጽ 140***
***11.	ከኒው ጋርደን ሃሳቡ የተወሰደ የህንድ እትም***
***12.	ከበሃኦላህ ጽሁፎች ቅስማት ቁጥር 5 ገጽ 7-8***
***13.	ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 5 ገጽ 9***
***14.	ከአብዶል በሃ ንግግሮች ኘሮሙልጌሽን ኦብ ዩንቨርሳል ፒስ የአሜሪካ እትም ገጽ 93***
***15.	አብዶል በሃ የፓሪስ ንግግሮች የእንግሊዝ እትም ገጽ 29***
***16.	ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት ቁጥር 146 ገጽ 315***
***17.	ከአብዶል በሃ ኘሮሙልጌሽን ኦቭ ዩንቨርሳል ፒስ ገጽ 93***
***18.	ከበሃኦላህ ኀቡዓተ ቃላት ከፋርስኛ ቁጥር 44***
***19.	ከአብዶል በሃ ኘሮሙልጌሽን ኦቭ ዩንቨርሳል ፒስ ገጽ 35***
***20.	ከአብዶል በሃ ጽሁፎች ከተውጣጣው የዓለም አቀፍ ማዕከል እትም ገጽ 88***
***21.	ከአብዶል በሃ ኘሮሙልጌሽን ኦቭ ዩንቨርሳል ፒስ***
***22.	ከበሃኦላህ የባሃኢ ስብሰባዎች ከሚለው ጥንቅር የአሜሪካን እትም ገጽ 3***
***23.	ከአብዶል በሃ አባስ ጽላቶች የአሜሪካን እትም ቅጽ 3 ገጽ 553***
***24.	ከአብዶል በሃ ጽሁፎች ከተውጣጣው ከሚለው መጽሐፍ ቁጥር 57 ገጽ 94***
***25.	ከበሃኦላህ በባሃኢ ስብሰባዎች ገጽ 3***
***26.	ከአብዶል በሃ አባስ ጽላቶች ቅጽ 3 ገጽ 631***
***27.	ከአብዶል በሃ ጽሁፎች ከተውጣጣው ከሚለው ቁጥር 54 ገጽ 93***
***28.	ከበሃኦላህ እጅግ በጣም ቅዱስ መጽሐፍ የዓለም አቀፍ ማዕከል እትም ገጽ 40***
***29.	ከአብዶል በሃ ጽሁፎች ከተውጣጣው ከሚለው መጽሐፍ ቁጥር 48 ገጽ 90***
***30.	ከዓለም አቀፍ ቤተ ፍትሕ ደብዳቤ የአሥራ ዘጠነኛው ቀን በዓል ከሚለው ጥንቅር የእንግሊዝ እትም ገጽ 5***
***31.	ከላይ ከተጠቀሰው ገጽ 7***
***32.	ከበሃኦላህ ኀቡዓተ ቃላት ከፋርስኛው ቁጥር 39***
***33.	ከአብዶል በሃ አባስ ጽላቶች ቅጽ 1 ገጽ 65***
***34.	ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት ቁጥር 139 ገጽ 304***
***35.	ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 74 ገጽ 341***
***36.	ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 158 ገጽ 335***
***37.	ከአብዶል በሃ አባስ ጽላቶች ቅጽ 2 ገጽ 473***
***38.	ከበሃኦላህ ጽሁፎች ቅስማት ቁ 161 ገጽ 339***
***39.	ከአብዶል በሃ ጽሁፎች ከተውጣጣው ቁጥር 216 ገጽ 269***

# ክፍል ሶስት

# የባሃሊ ትምህርቶችን ማስተዋወቅ

**ዓላማ**

**የባሃኢ ትምህርቶችን በጭውውት ውስጥ**
**የማስተዋወቅን ችሎታ ለማግኘት**

## *ምዕራፍ 1*

*እምነቱን በማገልገል ጎደና ሲጓዙ በበሃኦላህ የተገለጸውን የአምላክ ቃል ለሌሎች ማካፈል ሊለካ የማይችል ደስታ እንደሚያስገኝ አሁን አውቀዋል። በበሃኦላህ ግልጸት ውስጥ ያሉትን በዋጋ ሊገመቱ የማይቻሉ የጥበብ ዕንቁዎች ለሌሎች ለማካፈል የሚችሉበት አጋጣሚዎች በተለያዩ መንገዶች ይመጡልዎታል። አንዳንድ ባልንጀራዎችዎን ከእምነቱ ጋር ሊያስተዋውቁበት የሚችሉበት ስብሰባ እቤትዎ ሊያካሂዱ ይችላሉ። በአካባቢዎ ላለ ድርጅት ስለ እምነቱ ግንንር ሊሰጡ ይችላሉ። በቅርብና በሩቅ በሚገኙ አካባቢዎች በሚደረጉ የማስተማር ዘመቻዎች ይካፈሉም ይሆናል። አዲስ አማኞችን ቤታቸው ድረስ በመሄድ ከቅዱሳን ጽሁፎች መርጠው ያካፍሏቸዋል ይሆናል። ሕፃናት የማስተማር ፍላጎት ካለዎ ደግሞ የህፃናት ትምህርት በማካሄድ ህይወታቸውን በበሃኦላህ ትምህርት መሰረት መቅረጽን እንዲማሩ ሊረዷቸው ይችላሉ።*

*ብዙዎቹ እምነቱን የማስተማር እድሎችዎ የሚገኙት ከጓደኞችዎ ጋር በየእለቱ በሚያደርጉት ጭውውት ነው። በተለያዩ ርዕሶች በምትጨዋወቱበት ጊዜ ከጽሁፎቹ ያገኟቸውን ጥልቅ ሐሳቦች ለጓደኞችዎ ለማካፈልና ነገሮችን በበሃኦላህ ግልጸት ብርሃን ለማየት እንዲችሉ ሊረዷቸው ይችላሉ። የባሃኢ አስተሳሰቦችን በጭውውታችሁ ውስጥ በሚያስገቡ ጊዜ መስመር የለቀቀ ወይም በግድ የተደነቀረ መምሰል የለበትም። አንዳንድ ጊዜ ጥልቅ አስተሳሰብዎን እምነቱን ሳይጠቅሱ ለመግለጽ ይችሉ ይሆናል። ብዙ ጊዜ ደግሞ ሐሳብዎን "በሃኦላህ ሲያስተምር..." ወይም "አብዱል በሃ እንዳለው..." በማለት ለመግለጽ ይችላሉ። እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ሲናገሩ በሃኦላህ ማን እንደሆነ ወይም የባሃኢ እምነት ምን እንደሆነ የማብራራት ግደታ አይኖርብዎትም።*

*በዚህ ክፍል በአብዶል በሃ ንግግሮች ጽላቶች ላይ የተመሠረቱ ብዛት ያላቸው ምንባቦች ቀርበዋል። እነዚህ ምንባቦች የአብዶል በሃ ሙሉ ጥቅሶች ባይጨምሩም እርሱ የተጠቀመባቸውን ብዙ ሐረጎች ይዘዋል። ምንባቦቹን በተደጋጋሚ አንብበው በጥንቃቄ ካጠኗቸው በኋላ ያዘሉትን ሃሳቦች በራስዎ ቃላት መግለጽን ተለማማዱ። በዚህ መንገድ ትምህርቶቹን በትክክል ለሌሎች ደማብራራት ችሎታ ማዳበር እንደሚጀምሩ ተስፋ ይደረጋል። ለበሃኦላህ፥ ለአብዶል በሃ ለሾጊ ኤፌንዲ ጽሁፎች ግልጽ ትርጉም ታማኝ የመሆንንም ችሎታ ማዳበር ይጀምራሉ። ሆኖም ሊጀምሩም ያሉት ጥናት ልዩ ሃይል ያለውን የሰዎችን ልቦች ሰርስሮ የሚገባው የአምላክ ለዋጭ ቃልን በቃል የመያዝ ምትክ አይደለም። ስለዚህ በሚያስተምሩ ጊዜ ከቅዱሳን ጽሁፎች መጥቀስ ማስፈለጉ ይቀጥላል። እንደሌሎች የባሃኢ ሕይወት ተግባሮቻችን እዚህም መጠነኛነት ያስፈልጋል። እምነቱን ለማስተማር ከጽሁፎቹ በመጥቀስ በራሳችን ቃላት በመግለጽ መካከል ሚዛን መጠበቅ ይኖርብናል። ይህንን ሚዛን ለመጠበቅ ጽሁፎቹን ለማጥናት አስተሳሰብዎንና ስሜትዎን እንዲቀርጽልዎ ለማድረግ ብዙ ጊዜና ጉልበት በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።*

### ***መልመጃ***

1. *ሁሉም ጭውውቶች የበሃኦላህን ትምህርቶች ለሌሎች እንዲያካፍሉ ዕድል አይሰጥዎትም። እውነቱን ለመናገር ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚያወሩት ቁም ነገር ስለሌላቸውና ጎጂ ስለሆኑ ነገሮች ነው። ሁሉም ጭውውቶች ከበድ ባሉ ርዕሶች ላይ መሆን አለባቸው። ለማለት አይደለም። አንዳንዶቹ የሚያዝናኑ ሊሆኑ ይገባል። ሆኖም ከማይረባ ወሬ መጠንቀቅ እንዳለብዎና ከጓደኞችዎ ጋር የሚያደርጉት ጭውውት መንፈስዎንና አእምሮዎን የሚያነቃቃ መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎ። ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ከጓደኞችዎ ጋር ካደረጓቸው ጭውውቶች ጥቂቶቹን ለማስታወስ ይሞክሩ። በሚያነቃቁ ርዕሶች ላይ ያደረጓቸውን ጭውውቶችም ዘርዝሩ። የእምነቱን ትምህርቶች ልታስገቡ ትችሉባቸው የነበሩ ርዕሶች የትኞቹ ነበሩ?*

## ምዕራፍ 2

በዚህ ክፍል ውስጥ የተሰጡትን ምንባቦች ማጥናት ከመጀመርዎ በፊት በበሃኦላህ የግልጸት ዘመን አብዶል በሃ ስለያዘው ስፍራ ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል:: በእርግጥ በሌሎች የጥናትዎ ጊዜያት ስለ ሕይወቱ በዝርዝር ማንበብዎን ቃላቱ ከሚለግሱት ጥበብ የበለጠ መቋደስዎ አይቀርም:: አብዶል በሃ በሰው ልጅ ታሪክ ልዩ ስፍራ አለው:: እንደርሱ ያለ ደረጃ ያለው ሰው ባለፉት ሃይማኖቶች አልታየም:: በሃኦላህ ከዚህ ዓለም ከተለየ በኋላ የባሃኢን ማህበረሰብ በአብዶል በሃ ወይም በእጅግ ታላቁ ቅርንጫፍ ጥላ ሥር መተው ቃላት ሊገልጹት የማይችሉት በረከት ነው:: በሃኦላህ ለሰው ልጅ ያበረከተው እጅግ የላቀ ግልጸቱን ብቻ አይደለም:: በእውቀቱና በጥበቡ የሰው ዘር ብርሃን የሚያገኝበት የገዛ ልጁን አበርክቷል:: የአብዶል በሃን ልዩ ደረጃ ሳናውቅ የእምነቱን ትልቅነት በትንሹ እንኳን ለመረዳት ያስቸግራል::

በመጀመሪያ አብዶል በሃ የበሃኦላህ ቃል ኪዳን ማዕከል ነው:: የዚህ ቃል ኪዳን ኃይል የባሃኢ ማህበረሰብ አንድ እንዲሆን አድርጎታል፤ ከጠላቶቹ ተቃውሞ እንዲሁም ከመከፋፈልና ከመፈራረስ ጠብቆታል:: በመጨረሻ ድልን የሚያዳጀውም የዚህ ቃል ኪዳን ኃይል ነው::

በመሠረቱ በሃኦላህ ከተከታዮቹ ጋር የመሰረተው ቃል ኪዳን ሁላችንም ወደ አንድ መዕከል ፊታችንን እንድንመልስና ለማዕከሉም ታዛዥ እንድንሆን የሚጠይቅ ነው:: ይህ ማዕከል አብዶል በሃ ሲሆን በእርሱ ቃለ ጉዛዜ መሠረትም ከእርሱ በኋላ የእምነቱ ሞግዚት ወደሆነው ሾጊ ኤፌንዲ ሁላችንም የምንመልስበት ማዕከል ነው:: ዛሬ የእምነቱ ማዕከል ግልጽ በሆነ የበሃኦላህ ትዕዛዝና በማያሻማው የአብዶል በሃና የሾጊ ኤፌንዲ መመሪያ መሠረት የተቋቋመው ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ ነው::

ሁለተኛው አብዶል በሃ የበሃኦላህ ቃላት የማይሳሳት ተርጓሚ ነው:: የበሃኦላህ ግለጸት በጣም ሰፊና በእያንዳንዱ ቃላትም ውስጥ የተደበቀው ትርጉም እጅግ ጥልቅ በመሆኑ እርሱ እራሱ የሚገልጽበት ተርጓሚ አስፈላጊ ሆኖ አገኘው:: ስለዚህ ለመጪዎቹ ብዙ መቶ ዓመታት ብዛት ባላቸው የአብዶል በሃ ጽላቶችና ትክክለኛነታቸው በተረጋገጠላቸው የንግግሮቹ ቅጂዎች ውስጥ ያሉት ማብራሪያዎቹን በማጥናት የሰው ልጅ የበሃኦላህን ትምህርቶች ሊረዳ ይችላል:: ከአብዶል በሃ ቀጥሎ የበሃኦላህን ቃል የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠው ለሾጊ ኤፌንዲ ብቻ ነው:: በሾጊ ኤፌንዲ የበሃኦላህን ቃል የመተርጎም ሥልጣን አበቃ:: ከአሁን በኋላ በቀሪው የግልጸት ዘመኑ ማንም የበሃኦላህን ቃል የመተርጎም ሥልጣን የለውም:: እራሱ የሾመውን የእምነቱን ተርጓሚ በመተው በሃኦላህ ሌላ እጅግ ትልቅ በረከት በባሃኢ ማህበረሰብ ላይ አፈሰሰ:: ባለፉት ጊዜያት አማኞች በቅዱሳን መጽሐፋቸው ትርጉም ባልተስማሙ ጊዜ ማብራሪያ የሚጠይቁት ሥልጣን ያለው ተርጓሚ ባለመኖሩ በብዙ ቅርንጫፍ በመከፋፈል ተሰቃይተዋል:: በዚህ የግልጸት ዘመን ግን በበሃኦላህ ጽሁፎች ትርጉም አለመስማማት ቢፈጠር ሁሉም ሰው ወደ አብዶል በሃና ሾጊ ኤፌንዲ ትርጉሞች ፊቱን ይመልሳል:: አለመስማማቱ ካልተወገደ ወደ ዓለም አቀፍ ቤተ ፍትሕ ማብራሪያ ይሄዳል:: በትምህርቶቹ ትርጉም ላይ ጭቅጭቅ ለመፍጠር የሚያስችል ቀዳዳ ባለመኖሩ የእምነቱ አንድነት የተጠበቀ ነው::

ሶስተኛ አብዶል በሃ የአባቱ ትምህርት ምሉዕ አርኣያ ነው:: እርሱ ያለበት የምሉዕነት ደረጃ ላይ ልንደርስ የማንችል ቢሆንም እርሱን ከአይናችን አንፃር አድርገን አርአያነቱን መከተል ይኖርበታል:: በቅዱሳን ጽሁፎች ውስጥ ስለ ፍቅር ያነበብነውን በአብዶል በሃ ፍቅርና ደግነት ውስጥ ተንጸባርቆ እናገኛለን:: ሕይወቱን ብናስብ ስለንጽህና÷ ፍትሕ÷ ደስታ÷ ደግነት ያነበብናቸው እነዚህ ባህሪያት እጅግ ምሉዕ መልኩ በእርሱ ውስጥ ተከስተው እናያለን::

“ስሜ አብዶል በሃ (የባሃ አገልጋይ) ነው:: ብቁነቴ አብዶል በሃ ነው:: እውንነቴ አብዶል በሃ ነው:: መወደሻዬ አብዶል በሃ ነው:: ለተባረከው ፍጹምነት አገልጋይነት ክብር የተመላውና አንጸባራቂ የራስ ወርቄ ለመላው የሰው ዘር አገልጋይነት የዘለቄታ ሃይማኖቴ ነው... ወመደሻዬ አብዶል በሃ በስተቀር ሌላ ምንም ስም÷ ምንም ስያሜ÷ ምንም መጠሪያ÷ ምንም መሞገሻ÷ አላሻኝም ለወደፊቱም ከቶ አያሻኝም:: ይህ ነው ናፍቆቴ:: ይህ ነው ለዘለዓለም የሚኖረው የላቀ ጉጉቴ:: ይህ ነው ዘለዓለማዊ ሕይወቴ:: ይህ ነው ለዘለዓለም የሚኖረው ክብሬ::”[1]

ባለፈው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው በዚህ ክፍል የምናጤናቸው ምንባቦች ከአብዶል በሃ የተወሰዱ ባይሆኑም በብዙ ንግግሮቹና ጽሳቶቹ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ እምነቱን በማስተማር ልምድ እያዳበሩ ሲሄዱ አዕምሮዎን በአብዶል በሃ ቃላት መሙላትና ሃሳቦችን የሚያብራራበትን መንገድ ለመማር ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ክፍል ወደዚህ ጥረት እንዲሻገሩ እንደሚረዳዎ ተስፋ እናደርጋለን፡፡

# ምዕራፍ 3

በመጀመሪያ እንዲያጠኑ የሚጠየቁትና በጭውውት አጋጣሚዎች የእምነቱን ትምህርቶች ለማስተዋወቅ ሊረዳዎ የሚችለው ምንባብ መለኮታዊ መምህራንን የተመለከተ ነው፡፡

ሕይወትን ከሁሉም ገጽታዋ ብንመለከታት ሁል ጊዜ መምህር እንደሚያስፈልግ እንገነዘባለን ህፃን ልጅ ያለምንም መታነጽ ቢያድግ የአውሬን ፀባይ ይይዛል፡፡ በሚገባ ከታነጸ ግን እጅግ በጣም ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ መምህራን ባይኖሩ ኖሮ ሥልጣኔም ባልኖረ ነበር፡፡

ትምህርት ሶስት ዓይነት ነው፡፡ እነዚህም ቁሳዊ፥ ሰብአዊና መንፈሳዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ቁሳዊ ትምህርት የአካልን መዳበር የሚመለከት ነው፡፡ ሰብአዊ ትምህርት ደግሞ ሥልጣኔንና ዕድገትን ይመለከታል፡፡ አስተዳደር፥ የልግስና ሥራዎች፥ ንግድ፥ ሥነጥበብና የእጅ ጥበብ፥ ሳይንስ፥ ታላቅ ፈጠራዎችና ግኝቶች በዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ፡፡ መንፈሳዊ ትምህርት ደግሞ መለኮታዊ ባህሪያትን ማዳበርን ያስተምራል፡፡ በመለኮታዊ ትምህርት እርዳታ የሰው መንፈሳዊና ከፍተኛው ባህሪው ስለ ሚዳብር ይህ እውነተኛ ትምህርት ነው፡፡

የሰው ልጅ እንዲያድግ ከተፈለገ ቁሳዊ ሰብአዊ መንፈሳዊ መምህር ስለመሆኑ ግልጽ ማረጋገጫ ያለውን መምህር መከተል ያስፈልገዋል፡፡ አንድ ሰው ተነስቶ "እኔ ምሉዕ የሆነ እውቀት ስላለኝ መምህር አያስፈልገኝም" ቢል ግልጽና የማያሻማ የሆነን ነገር ካደ ማለት ነው፡፡

እርሱም "እኔ መምህር አያስፈልገኝም እንደ አስተሳሰቤና እውቀቴ እየተራመድኩ ያለምንም ረዳት ምሉዕነት ላይ እደርሳለሁ፡፡" እንደሚል ህፃን ሆነ ማለት ነው፡፡

የሰው ልጅ ሁል ጊዜ እንዲህ አይነት መምህር ሲያስፈልጉት ቆይቷል፡፡ ይህም መምህር ከአካሉ መዳበርና ጤንነት ጋር የተያያዙ ጉደዮች እንዲያጤን ረድቶታል በእውቀት በፈጠራና በግኝቶች እንዲራመድ ቀስቅሶታል ከሁሉም በላይ ደግሞ በእውነተኛው የመንፈስ ሕይወቱ ነፍስ ዘርቶበታል፡፡ ማንም ተራ ሰው እነዚህን አስቸጋሪ ተግባሮች በፍሬያማነት ሊያጠናቅቅ አይችልም፡፡ እነዚህን ተግባሮች ከመልካም ፍጻሜ የማድረስ ኃይል ያላቸው የእግዚአብሔር መልእክተኞች ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱም ዓለም አቀፍ የሰው ልጅ መምህራን በመሆን ከጊዜ ጊዜ በአምላክ የሚላኩ የተመረጡ ነፍሶች ናቸው፡፡

***መልመጃዎች***

1. ከላይ የተሰጠውን ምንባብ ከቡድንዎ ጋር ሆነው ደጋግመው ያንብቡትና ይዘቱን እስክትረዱት ድረስ በመረዳዳት ያጥኑት፡፡ በሌሎች ምዕራፎች እንዳደረጉት ሁሉ በምንባቡ ውስጥ ከተሰጡ ሐሳቦች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ልትጠየቁ ይገባል ከዚያ በምንባቡ ውስጥ የተካተቱ ሐሳቦችን በራስዎ ቃላት ይገለጿቸው፡፡

2. አንዳንድ የጭውውት ርዕሶች ከሌሎች በተሻለ መንገድ በምንባቡ የተሰጡ ሐሳቦችን ለማስገባት ይመቻሉ፡፡ ቀጥሎ ከተሰጡት የጭውውት ርዕሶች ዝርዝር መካከል ከውይይቱ መስመር ሳይወጡ በምንባቡ የተካተቱትን ሐሳቦች ሊያስተላልፉ የሚችሉባቸው ርዕሶች ላይ ምልክት ያድርጉ በመረጧቸው ርዕሶች በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው ሀሳቦቹን እንዴት ለማስተላለፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡ የተቀሩት የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና ተወያዩባቸው፡

_______ ዛሬ ኅብረተሰብ ያለበት ሁኔታ
_______ ከሞት በኋላ ሕይወት
_______ መሐይመነትን ማስወገድ
_______ በንግድ ወይም በሙያ የመሰማራት አስፈላጊነት

3. ከላይ በተሰጡት ርእሶች ላይ የሚሰነዘሩት አስተያየቶች ብዙውን ጊዜ ስለ አንዳንድ የእምነቱ ትምህርቶች ውይይት ለማድረግ በር ይከፍታሉ። አንድ ሰው "ከእነዚህ መምህራን መካከል ጥቂቶቹ እነማን ናቸው?" ብሎ ቢጠይቅዎ ምን ይመልሳሉ? _______

4. ከላይ በተሰጠው ምንባብ ውስጥ ከተካተቱ ሐሳቦች ጋር የተያያዙ ከበሃኦላህ ጽሁፎች ውስጥ የተወሰዱ ጥቂት ጥቅሶች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል። ያሰላስሉባቸው። በቃልዎም ለመያዝ የተቻለዎትን ሁሉ ጥረት ያድርጉ። ይህን ካደረጉ በንግግርዎ ጣልቃ ከቅዱሳን ጽሑፎች መጥቀስ ስለሚችሉ የአድማጭዎን ልብ ለመሳብ ይችላሉ።

"ሰው ሁሉ የተፈጠረው የለሚቋረጥ እያደገ የሚሄደውን ሥልጣኔ ወደፊት ለማራመድ ነው።"[2]

"አንዱና እውነተኛው አምላክ ክብሩ ይስፋና ራሱን ለሰዎች የመግለጹ ዓላማ እነዚያን በራሳቸው ውስጥ በሚገኘው እውነተኛና ጥልቅ ማዕድን ውስጥ ተደብቀው የሚገኙትን ዕንቁዎች ለሰዎች ገልጾ ለማሳየት ነው።"[3]

"የእርሱን ነቢያት ወደ ሰዎች በሚልክበት ጊዜ የአምላክ ዓላማ ሁለት ነው። የመጀመሪያው የሰዎችን ልጆች ካለማወቅ ጨለማ ነፃ ለመውጣት ወደ እውነተኛው የመረዳት ብርሃን ለመምራት ነው። ሁለተኛው የሰውን ልጆች ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥና ሊመሠረቱ የማችሉበትንም ነገሮች ሁሉ ለመስጠት ነው።"[4]

"ሰዎች በሁሉ ጊዜያትና በሁሉም ሁኔታዎች የሚመክራቸው÷ የሚመራቸው÷ መመሪያ የሚሰጣቸው ያስፈልጋቸዋል።"[5]

# ምዕራፍ 4

እውነትን በግል ራስን ችሎ መመርመር በሚል ርዕስ ቀጥሎ የቀረቡት ሐሳቦች አጋጣሚዎች ጠቃሚ ይሆናሉ።

ከየትኛውም ኩራዝ ቢበራ ብርሃንን አፍቃሪ መሆነ አለብን። በየትኛውም መናፈሻ ቢያብብ ፍቅራችን ለጽጌሬዳ መሆን አለበት። ከአንድ ኩራዝ ጋር ትስስር ካለን ከሌላ ኩራዝ ብርሃን ሲንፀባረቅ ላናስተውል እንችላለን። ከሐይማኖት ውጫዊ ቅርጾችና ስርአቶች ጋር መተሳሰር የሐይማኖቶችን ሁሉ እውነታ እንዳንረዳ ያደርገናል። እውነትን ለማወቅ ከፈለግን አጉል ጥላቻንና ጊዜ ያለፈባቸውን ልምዶች መተው አለብን። ቀኖናዊነት አጉል አምልኮና አጉል ጥላቻ ከእውነት ጋር አይሄዱም።

እውነትን ስንፈልግ ከአመለካከቶቻችንና ቀድሞ ካዳበርናቸው አስተሳሰቦች እራሳችንን ነፃ ማድረግ አለብን፡፡ ክፍትና ዝግጁ የሆነ አእምሮ ያስፈልጋል፡፡ ብርጭቆአችን በእኔነት የተሞላ ከሆነ ለሕይወት ውሃ ቦታ አይኖረውም፡፡ እራሳችንን ትክክለኞች ሌሎችን ሁሉ ደግሞ ስህተተኞች አድርገን መቁጠራችን በአንድነት መንገድ ላይ ያለ ትልቅ መሰናክል ነው፡፡ እውነት አንድ ስለሆነ እውነት ላይ ለመድረስ ከፈለግን አንድነት አስፈላጊ ነው፡፡

***መልመጃዎች***

1. *እንደቀድሞው ምዕራፍ ከቡድንዎ ጋር በመሆን ተከፋፍለው ከላይ የተሰጠውን ምንባብ ደጋግመው ያንብቡት ከተሰጡት ሐሳቦች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ተጠያየቁ፡፡ ከዚያም በራሳችሁ ቃላት መግለጽ ተለማመዱ፡፡*

2. *አንዳንድ የጭውውት ርዕሶች ከሌሎች በተሻለ መንገድ በምንባቡ የተሰጡ ሐሳቦችን ለማስገባት ይመቻሉ፡፡ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የጭውውት ርዕሶች መካከል ከውይይቱ መስመር ሳይወጡ በምንባቡ የተካተቱትን ሐሳቦች ሊያስተላልፉ የሚችሉባቸው ርዕሶች ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡ በመረጧቸው ርዕሶች በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው ሐሳቦቹን እንዴት ለማስተላለፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡ የተቀሩትም የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና የተያዩባቸው፡፡*

_______ ባህላዊ የግብርና አሰራሮች ከአዲስ ቴክኖሎጂዎች ጋር ሲነፃፀሩ
_______ የአካባቢ ብክለት አደጋ
_______ የሴቶችና የወንዶች እኩልነት

*ከላይ በተሰጡ ርዕሶች ላይ ከጓደኞችዎ ጋር ሲነጋገሩ ስለ አንዳንድ የእምነቱ ትምህርቶች ለመናገር በር ይከፍታሉ፡፡ ከጓደኞችዎ መካከል አንዱ "ሁሉም ሐይማኖቶች ውስጥ ካሉ እውነታዎች መካከል ጥቂቶቹ እነማን ናቸው?" ብለው ቢጠይቅዎ ምን ይመልሳሉ?* __________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
_________________________

*በንግግርዎ ውስጥ ሊጠቅሱ ይችሉ ዘንድ ከዚህ በታች ያሉትን በቃልዎ ቢይዙ መልካም ነው፡፡*

*"የዓለም ሕዝቦች ከማናቸውም ዘር ሆነ ሃይማኖት ቢሆኑ የመንፈስ መነቃቃታቸውን ከአንድ መንግሥተ ሰማያዊ ምንጭ እንደሚያገኙ የአንድ አምላክም ተገዢዎች ለመሆናቸው ምንም ዓይነት ጥርጥር ሊኖር አይችልም፡፡"[6]*

*"ከሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ጋር በጓደኝነትና በወዳጅነት መንፈስ ተቀላቀሉ፡፡"[7]*

*"የአምላክን እምነትና ሃይማኖት ከመሠረቱ የሚያንቀሳቅሰው ኃይል ዓላማ የሰውን ዘር ጥቅም ለመጠበቅና አንድነቱንም ለማጠናከር ነው፡፡"[8]*

*"የእግዚአብሔር ሃይማኖት ለፍቅርና ለአንድነት ነው የጠላትነትና የመቃቃር ምክንያት አታድርገት፡፡"[9]*

## ምዕራፍ 5

*የሚቀጥለው ምንባብ አምላክ በክስተቶቹ አማካኝነት ብቻ እንደሚታወቅ የሚያስረዳ ነው:: ከጓደኞችዎ ጋር ለሚያደርጓቸው ጭውውቶች ይጠቅምዎታል::*

ወሰን የሌለውን ጠፈር ያስቡ:: ያለ አንድ ፈጣሪ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላልን? ወይም የዚህ ወሰን የሌለው ዓለም ፈጣሪ ማሰብ የማይችል ሊሆን ይችላልን? ቁሳካላውያን ሰው የተፈጥሮ የራሷ ውጤት ነው ይላሉ:: ተፈጥሮ ግን የማሰብ ችሎታ የላትም:: ታዲያ ማሰብ የሚችለውን ሰው ልትፈጥር ትችላለችን?

ፍጥረትን በምንመለከት ጊዜ ከበታች ያለ ማንኛውም ነገር የበላዩን ኃይል ለመረዳት አይችልም:: ስለዚህ ድንጋይ፥ ዛፍ፥ እንስሶች ምንም ያክል ቢያድጉ የሰውን እውነታ ሊረዱ ኃይሉንም ሊገምቱ አይችሉም:: በተመሳሳይ መንገድ ፍጡር የሆነው ሰው ደግሞ የፈጣሪውን እውነታ ሊያውቅ እንዴት ይችላል?

የሰው የመረዳት ችሎታ አምላኩጋ ሊደርስ የማይችል ቢሆንም እርሱን ማወቅን ግን አልተነፈገም:: ከዘመን ዘመን የእግዚአብሔር ክስተት የሆነ ነፍስ ይመጣል:: በተወለወለ ንጹህ መስታወት ውስጥ ፀሐይ እንደምታንፀባቅ ሁሉ ከአምላክ የሚመጡት ምሉእነት በረከትና ግርማ በቅዱስ ክስተቱ ውስጥ ይታያሉ:: እነዚህ መስታወቶች የእውነት ፀሐይ ክስተቶች ናቸው ማለት ፀሐይ ከከፍተኛው ክብሯ ወርዳ መስታወቱ ውስጥ ገባች ማለት አይደለም:: ይልቁንም የሰው ልጅ ስለ እግዚአብሔር ስሞች ባሕሪያት እና ምሉዕነቶች የሚያውቀው የሚገነዘበውና የሚረዳው ሁሉ የሚያመለክተው ቅዱስ ክስተቶቹን ነው ማለት ነው::

***መልመጃዎች***

1. ከቡድንዎ ጋር በመሆን ምንባቡን ደጋግመው ካነበቡና በይዘቱ ላይ ተመስርታችሁ ጥያቄ እየተጠያየቃችሁ ከመለሳችሁ በኋላ በራሳችሁ ቃል መግለጽን ተለማመዱ::

2. በዚህ በታች የጭውውት ርዕሶች ተሰጥተዋል:: በምንባቡ የተካተቱትን ሐሳቦች በቀላሉ ሊያስተላልፉባቸው የሚችሉባቸው ርዕሶች በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው ሐሳቦቹን እንዴት ለማስተላለፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ:: የተቀሩትም የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና ተወያዩባቸው::

_______ የዓለም አፈጣጠር
_______ የፀሐይ ሙቀት ኃይል ጥቅሞች
_______ የእግዚአብሔር መኖር
_______ የሰው አዕምሮ ኃይል

3. ከጓደኞችዎ ጋር ሲጫዋወቱ ከላይ ባጠኑት ርዕስ ላይ የመናገር ዕድል አጋጠመዎ እንበል:: ከጓደኞችዎ አንዱ "በክስተቶቹ አማካኝነት ስለ እግዚአብሔር ከምናውቃቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ የትኞቹ ናቸው ብሎ ቢጠይቅዎ እንዴት ይመልሱለታል?______
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
________________________________________
_______

4. በዚህ ርዕስ ከጓደኞችዎ ጋር ሲጫዋወቱ ከበሃኦላህ ጽሁፎች ለመጥቀስ እንዲችሉ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ መያዝ ይፈልጉ ይሆናል፡፡

"የእርሱ የሁሉ ነገሮች ምንጭ የሆነው ዕውቀት ወደ እርሱም መድረስ በእነዚህ ከእውነቱ ፀሐይ በሚወጡት አንጸባራቂ ፍጡራን ዕውቀትና ወደ እነርሱም በመቅረብ አማካይነት በቀር በሌላ በምንም ዓይነት አይቻልም፡፡"[10]

"የመገንዘብ ችሎታው ምንም ያህል ጥልቅ ቢሆን መለኮታዊ ሐኪም ከደረሰበት ጥበበኝነትና የመገንዘብ ኃይል ከፍታ ላይ ለመድረስ ተስፋ የሚያደርግ ሰው እስከ መቼውም ሊገኝ ከቶ አይችልም፡፡"[11]

"የክስተቱ ሰብዓዊ አቋም ምንጊዜም የእግዚአብሔር አፈቀላጤ ወኪልና መነጋገሪያ ነው እርሱ በእርግጥ የእግዚአብሔር ፍጹም የላቁ ስያሜዎች የቀን ምንጭ የተከበሩ ባሕሪያቱም የንጋት ቦታ ነው፡፡"[12]

"ከዚህም በላይ የእነዚህ የአምላክ ክስተቶች የእያንዳንዳቸውና የሁላቸው ሥራዎችና ተግባራቸው እንዲያውም ማንኛውም ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም እነርሱ ወደፊት የሚገልጹት ሁሉ በአምላክ የታዘዘ የፈቃዱና የዓላማውም ነጸብራቅ ስለመሆኑ እርግጠኞች ሁኑ፡፡"[13]

## ምዕራፍ 6

በሌሎች ጊዜያት ደግሞ ስለ በሃኦላህ ተልእኮና ሕይወት ባጭሩ መናገር ይኖርብዎታል፡፡ የሚከተለው ምንባብ ለዚህ ይረዳዎታል፡፡

ከ150 ዓመታት በፊት በሃኦላህ ከፋርስ ተነስቶ ሕይወቱን ሰዎችን ለማነቃቃትና ለማስተማር ሰጠ፡፡ የሰው ልጅን አንድነት አወጀ፡፡ ሁሉንም የፈጠረውና የሚመግበው አንድ አፍቃሪና ሩኅሩህ አምላክ እንደሆነ አስተማረ፡፡ የሴቶችና የወንዶች እኩልነት አጉል ጥላቻን ማስወገድ የሳይንስና ሐይማኖት መስማማትና የዓለም አቀፍ መምህር አስፈላጊነት የመሳሰሉ መርሆዎችን አራመደ፡፡

የምስራቅ ነገሥታትና የፋርስ ቀሳውስት የበሃኦላህ ትምህርቶች የግል ጥቅሞቻቸውን የሚያራምዱላቸው ሆነው ስላላገኟቸው በእርሱ ላይ ተነሱበት፡፡ አሰቃዩት አሾፉበት በኋላም በሰንሰለት አሰሩት፡፡ ፋርስ ሳለ ኃብትና ንብረቱን ተገፈፈ፡፡ በግዞት በመጀመሪያ ወደ ባግዳድ በኋላም ወደ ቁስጥንጥንያ ቀጥሎም ወደ አድርያኖጵሎስ በመጨረሻም ወደ አቆር የእስር ከተማ ተወሰደ፡፡

በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ሁልጊዜ ደስተኛ ነበር፡፡ ክብሩን ለማሳነስ ጠላቶቹ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ቢያደርጉም ታዋቂነቱ በየቀኑ እያደገ ሄደ፡፡ በጠላቶቹ ቢከበብም ራሱን ለመከላከል ምንም እርምጃ አልወሰደም፡፡ በአንፃሩ ግን መንፈሳዊ ኃይሉ ለሰዎች ሁልጊዜ በግልጽ ይታይ ነበር፡፡

ሕይወቱን በሙሉ ያሳለፈው በስራ ነበር፡፡ ጉልበቱ ገደብ አልነበረውም፡፡ ተረጋግቶ የተኛባት አንዲትም ቀን አልነበረችም፡፡ ራስ ወዳድነት ጠፍቶ ማገልገል በሰው ልጆች ዘንድ እንዲታይ እጅግ ታላቁ ሰላም እንዲመሰረት የሰዎች እምነት እንዲጠነክር የሰው ልጅ አዕምሮ ሙሉ ችሎታ እንዲዳብርና ሰው የአምላክ ነፀብራቅና ምሳሌ እንዲሆን በሃኦላህ መከራን ተቀበለ፡፡ በእውነቱ በሃኦላህ የእግዚአብሔር ክስተትና የሰው ልጅ ዓለም አቀፍ መምህር ነው፡፡

***መልመጃዎች***

1. እንደተለመደው ምንባቡን በቡድን ተከፋፍላችሁ አንቀጽ በአንቀጽ ደጋግማችሁ ካነበባችሁና ይዘቱን በደንብ እስከምትረዱት ድረስ ጥያቄ እየተጠያየቃችሁ ካጠናችሁት በኋላ በራሳችሁ ቃላት ታሪኩን መናገርን ተለማመዱ::

2. ቀጥሎ ከተሰጡት የጭውውት ርዕሶች መካከል የበሃኦላህን ሕይወት ታሪክ በአጭሩ ለመናገር የሚመችዎትን ምልክት ያድርጉባቸው:: በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው እንዴት ታሪኩን ለመናገር እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ:: የተቀሩትም የቡድንዎ አሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይሰጡና ተወያዩባቸው::

_______ የሰው መብት
_______ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለ ፍትሕ አልበኝነት
_______ የመካከለኛው ምሥራቅ ሁኔታ
_______ የታሪክ የተመዘገቡ ታላላቅ ሰዎች

3. አንድ ሰው ከበሃኦላህ በፊት የመጡ ክስተቶች ትምህርቶች እያሉልን በሃኦላህ ለምን ያስፈልጋል ብሎ ቢጠይቅዎ እንዴት ይመልሱለታል? ______________________________
________________________________________________________________
________________________________________________________________
________________________________________________________________
________________________________________________________________
________________________________________________________________
________________________________________________________________
____________________

4. ስለ በሃኦላህ በሚናገሩበት ጊዜ መጥቀስ ይችሉ ዘንድ የሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዟቸው::

"ዘለዓለማዊው እውነት አሁን መጥቷል:: እርሱ የሥልጣንን ግርማ ሰንደቅ ዓላማ ሰቅሏል አሁን የግልጸቱን ያልተጋረደ ደማቅ ብርሃን በዓለም ላይ እያበራ ነው::"[14]

"ልትገነዘቡት ብትችሉ ኖሮ ለዚያ ሊታወቅ ለማይቻለው የሥውሮች ሥውር ለሆነው ክስተቱ እርሱ ነው::"[15]

"ይህ ቀን ፍጹም መሕረተኛው በዕውቀት ደመናዎች ውስጥ ሆኖ ግልጽ ሉዓላዊነትን ተጎናጽፎ የወረደበት ቀን ነው::"[16]

## ምዕራፍ 7

የሰው ልጅ ወደ ብስለት ደረጃ መሸጋገር ቀጥሎ በሚገኘው ምንባብ የሚያጠኑት ርዕስ ነው::

በዚህ ዓለም የሚገኝ ማንኛውም ሕይወት ያለው ነገር ከልደት እስከ ሞት ባለው ጊዜ የተለያዩ ደረጃዎችን ያልፋል:: እያንዳንዱ ደረጃ የራሱ ሁኔታዎች ሲኖሩት የራሱ የሆኑ ፍላጎቶችም አሉት:: በሰው ሕይወት ውስጥ የጨቅላነት÷ የህፃንነት÷ የልጅነት÷ የጉርምስና÷ የወጣትነትና የብስለት ዕድሜ ሁኔታዎች ፍላጎቶች አንድ አይነት አይደሉም:: እያንዳንዱ ደረጃ ኃይሎቻችንን እያነቃና አዕምሮዎቻችንን እያሰለጠነ ለሚቀጥለው ደረጃ ያዘጋጀናል::

በተመሳሳይ መንገድ የሰው ዘር በጅምላ ሕይወቱ የተለያዩ ዕድሜዎች አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ልጅነቱን ትቶ ለዘመናት ወደ ተጠበቀው የብስለት ደረጃው እየተሸጋገረ ነው፡፡ በቀዳሞ ጊዜ ፍላጎቱን ሲያሟሉለት የነበሩ ነገሮች የአሁኑን ጊዜ ችግሮቹን አይፈቱለትም፡፡ የጨቅላነትና የህጻንነት ጊዜ መጫወቻዎች የአዋቂን አዕምሮ አያረኩም፡፡

ከሁሉም አቅጣጫ ብንመለከት የሰው ልጅ በአስተዳደር ሆነ በሕግ በሳይንስ ሆነ በኢንዱስትሪ ስርነቀል ለውጦች ውስጥ እያለፈ ነው፡፡ ያረጁት የግብረ ገብነት መለኪያዎች የስነ ምግባር አንቀጾችና የቀድሞው የአኗኗር ስልቶች ለአሁኑ የዕድገትና ግስጋሴ ዘመን በቂ አልሆኑም፡፡

ለሃይማኖትም ቢሆን ይህ የብስለትና የማሻሻያ ዘመን ነው፡፡ አክራሪነትና ጥንታዊ እምነቶችን በጭፍን መውረስ የጥላቻ ምንጮች ሆነዋል፡፡ ለሰው ልጅ ዕድገት በዚህ ዘመን ለተገለጹ መንግሥተ ሰማያዊ ትምህርቶች ቦታቸውን መልቀቅ አለባቸው፡፡ መሠረታዊውን የሃይማኖት እውነታ ከዘመኑ ፍላጎት ጋር ማጣጣም የዘመናዊነት እውነተኛ መንፈስ የማያሳስት የዓለም ብርሃንና ለሰው ልጅ ህመሞች ሁሉ መለኮታዊ ፈውስ ነው፡፡

***መልመጃዎች***

1. በምንባቡ የተላለፉትን ሐሳቦች መረዳት እንዲችሉ እንደተለመደው በቡድን ተከፋፍለው ደጋግመው ያንብቡትና ከምንባቡ የሚያወጡትን ጥቃቄዎች ይጠያየቁ፡፡ ከዚያም በራስዎ ቃላት የምንባቡን ሐሳቦች ይግለጹ፡፡

2. ከዚህ በታች የጭውውት ርዕሶች ተዘርዝረዋል፡፡ የውይይቱን ሰንሰለት ሳይለቁ የምንባቡን ሐሳቦች ልናገርባቸው እችላለሁ የሚሉባቸው ርዕሶች ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡ በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው እንዴት ሐሳቦችን መናገር እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ፡- የተቀሩት የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና ተወያዩባቸው፡፡

_______ ታሪክ
_______ ዘመናዊ ሥነ ጽሁፍ
_______ የሰው ልጅ መጨረሻ
_______ በዘመናችን ያለ የኅብረተሰብ አለመረጋጋት

3. የሰው ልጅ የብስለት ደረጃ መድረሱን እንዴት እናውቃለን? ተብለው ቢጠየቁ ምን ይመልሳሉ? ______________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________

4. የሚከተሉትን የበሃኦላህ ቃላት በቃልዎ ለመያዝ ይፈልጉ ይሆናል?

“እያንዳንዱ ዘመን የራሱ ችግር እያንዳንዱ ነፍስ የተለየ የራሱ ፍላጎት አለው፡፡ ዓለም ለዛሬው ጊዜ መከራዎቿ የሚያስፈልጋት መድኃኒት ለሚቀጥለው ዘመን ከሚያስፈልገው ጋር አንድ ዓይነት ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡”[17]

“ለምትኖሩበት ዘመን ፍላጎቶች የኃላፊነት ስሜት የተመላበት ሃሳብ ይኑራችሁ ምክክሮቻችሁም በአጣዳፊና አስፈላጊ ጉደዮችዋ ላይ እንዲያተኩሩ አድርጉ።”[18]

“በዚህ ዘመን አዲስ ሕይወት በመላው የምድር ሕዝቦች መካከል እየተንቀሳቀሰ ነው ሆኖም ምክንያቱን የተገነዘበ ዓላማውንም የተረዳ ማንም የለም።”[29]

## ምዕራፍ 8

የሰላም መመሥረት ሁሉም አእምሮ ውስጥ የሚጉላላ ሃሳብ ነው። የሚቀጥለው ምንባብ በሰላም መመስረት ላይ ያለውን የባሃኢ አመለካከት በጭውውቶች ውስጥ ለመናገር ይረዳዎታል።

ዛሬ ሰላምን መመስረትን ያክል ለሰው ልጅ አስቸጋሪ ነገር የለም። ሰላም ብርሃን ነው ጦርነት ጨለማ ነው። ሰላም ሕይወት ነው ጦርነት ግን ሞት ነው። ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ዓለም አቀፍ ሰላም እንዴት መመሥረት እንደሚቻል በሃኦላህ አውጆአል። የሰላምን መመሥረት እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ብዙ ትምህርቶች አምጥቷል።

ከእነዚህ ትምህርቶች መካከል አንዱ እውነትን በግልና በነፃነት መመርመር ነው። ሰዎች እውነትን ለመመርመር ቢነሱ የሰው ልጅ አንድነትን ማምጣት ይቻላል። የሁሉም ዓይነት አጉል ጥላቻና ፍቅር ማለትም የዘር÷ የቀለም÷ የሐይማኖት÷ የሐገር÷ የጾታና የቁሳዊ ሥልጣኔ ደረጃ ግጭቶችን ያስከትላሉ። ያለፉ እምነቶችን በጭፍን ከመቅዳት ይልቅ እውነትን ለመመርመር ብንነሳ ሁሉንም ዓይነት አጉል ጥላቻና ፍቅር ለማጥፋት እንነሳለን።

ሃይማኖትን የተመለከቱ የበሃኦላህ ትምህርቶች በእውነተኛ ሃይማኖትና በአጉል አምልኮ መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ አድርገው ያሳያሉ። እውነትኛ ሃይማኖት ከሳይንስና ከምክንያታዊነት ጋር መስማማት አለበት። ሃይማኖት የወዳጅነትና የፍቅር ምክንያት ሊሆን ይገባል። የመለያየትና የጥላቻ ምክንያት ከሆነ ያለሃይማኖት መኖር ይሻላል። ከበሃኦላህ ትምህርቶች መካከል ሌላው የወንዶችና የሴቶች እኩልነት ነው። የሰውን ልጅ በወፍ ልንመስለው እንችላለን። የዚህ ወፍ አንዱ ክንፍ ሴቶች ሲሆኑ ሌላው ክንፉ ደግሞ ወንዶች ናቸው። ወፉ በሚገባ እንዲበር ከተፈለገ ሁለቱም ክንፎቹ እኩል መጠንከር ይገባቸዋል። ሌሎቹ የበሃኦላህ ትምህርቶች በዓለም አቀፍ ትምህርት አስፈላጊነት÷ የዓለም አቀፍ ቋንቋ ጠቀሜታ÷ ለኢኮኖሚ ችግሮች መንፈሳዊ መፍትሔ መፈለግ ላይ ብርሃን ይፈነጥቃሉ።

የሰው ልጅ ከሥጋው እስር ነፃ መሆን አለበት። የተፈጠረው ያለማቋረጥ የሚያድግ ሥልጣኔ ለማራመድ ነው። ይሁንና ሥልጣኔ ሁለት አይነት ነው ማለትም ቁሳዊና መንፈሳዊ ጎኖች አሉት። ሁለቱን ማጣመር ካልተቻለ የሰው ልጅ ደስታን አያገኝም። ፍትህ የሰውን ጉዳዮች እስካልመራ ድረስ ስርአተ አልበኝነት ይቀጥላል ክፋትም አይጠፋም።

***መልመጃዎች***

1. ከቡደንዎ ጋር በመሆን ምንባቡን እንደተለመደው ካጠኑ በኋላ ከዚህ በታች ከተሰጡት የጭውውት ርዕሶች ውስጥ የውይይቱን ሰንሰለት ሳይበጥሱ የምንባቡን ሐሳቦች በቀላሉ ለመናገር በሚችሉባቸው ላይ ምልክት ያድርጉ። በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጥረው እንዴት ሐሳቦቹን መናገር እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ። የተቀሩት የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና ተወያዩባቸው።

_______ የሕዝብ አውዳሚ መሳሪያዎች መታገድ
_______ የሽብር ፈጠራ በዓለም ላይ መስፋፋት
_______ የጦርነት አጥፊነት
_______ ደስታን የሚያመጡልን ነገሮች

2. "ጦርነት ጠፍቶ አያውቅም። ሰላምን ማስፈን ይቻላል ብለው እንዴት ያስባሉ?" ተብለው ቢጠየቁ እንዴት ይመልሳሉ?________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
________________________________________

3. የሚከተሉትን የበሃኦላህ ጥቅሶች በቃልዎ ቢይዙ መልካም ነው።

"የዓለም ዕድገት፥ የአገሮች መልማት፥ የሕዝቦች እርጋታና የእነዚያ በምድር ላይ የሚኖሩት ሁሉ ሰላም በአምላክ መሠረታዊ መመሪያዎችና ትእዛዛት መካከል ይገኛሉ።"[20]

"ሃይማኖት በእውነቱ፤ በዓለም ላይ ሥርዓትን፥ በሕዝቦቿም መካከል ሰላማዊ እርካታን ለመመሥረት ዋና መሣሪያ ነው።"[21]

"አንድነቱ በጥብቅ ካልተመሠረተና እስኪመሠረት የሰው ዘር ደህንነት ሰላሙና ዋስትናው ሊደረስባቸው አይችልም።"[22]

## ምዕራፍ 9

የሰው ልጅ አንድነት የባሃኢ ትምህርቶች ማዕከላዊ ጭብጥ በመሆኑ በጭውውትዎ ውስጥ በተደጋጋሚ ሊያነሱት ይሻሉ።

ተመሳሳይ ቅርጽና ቀለም ያላቸውን እጽዋት ብቻ ያዘለ መናፈሻ ውበት ይጎድለዋል። የማይማርክና አሰልቺም ነው። ሁሉም ዓይነት ቀለሞችና መዓዛዎች ያሏቸው አበቦች በመደዳ የተተከሉበት መናፈሻ ዓይንን ይስባል። አንድን መናፈሻ ውብና ማራኪ የሚያደርጉት የተለያዩ ቀለሞች ያሏቸው አበቦች አስደናቂ ስብጥር ነው። ምንም እንኳን የተለያዩ ዓይነት አበቦች ቢሆኑም ሁሉም ከአንድ ዝናብ ውሃ ይጠጣሉ ሙቀትንም ከአንድ ፀሐይ ያገኛሉ። የሰው ልጅም ቢሆን እንደዚህ ነው። በየተለያዩ ዘሮችና ቀለሞች የተገነባ ነው። ነገር ግን ሁሉም ከአምላክ የመጡ በመሆናቸው የሁሉም ምንጭ አንድ ነው። የተለያዩ የሙዚቃ ኖታዎች ተደባልቀው ለጆሮ ጥኡም የሆነ ድምጽ እንደሚያመነጩ ሁሉ በሰው ልጅ ቤተሰብ መካከል ያለው ስብጥር የፍቅርና የስምምነት ምንጭ መሆን አለበት።

አንድነት ለኑሮ አስፈላጊ ነው። የሕይወት መንስኤ ፍቅር ነው። በቁሳዊ ዓለም ሁሉም ነገሮች መኖር የቻሉት በአንድነት ኃይል ነው። ንጥረ ነገሮቻቸው በመሳሳብ ሕግ በአንድነት እንዲያያዙ ሆነ። ንጥረ ነገሮች በመሳሳብ ሕግ በአንድነት ሲያያዙ የሚያምር አበባ ይወጣቸዋል። መሳሳቡ በማይኖር ጊዜ አበባው ይደርቃል። ሕይወትም አይኖረውም። የሰው ልጅም ቢሆን እንደዚህ ነው። መሳሳብ ስምምነትና አንድነት የሰው ዘርን አቅፈው የሚይዙ ኃይሎች ናቸው።

በሃኦላህ በዓለም ሕዝቦች መካከል አንድነትን ለመመስረት የሚያስችል ንድፍ አምጥቷል። ሕዝቦችን ወደዚህ የአንድነት ቀለበት ለመሳብ የተቻለንን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለብን። የተለያዩ ዘሮች ዜግነቶች ሃይማኖቶችና አመለካከቶች ካሏቸው ሰዎች ጋር ስንገናኝ ልዩነቶች ለአንድነታችን እንቅፋት እንዲሆኑ መፍቀድ የለብንም። ይልቁንም እነዚህን ልዩነቶች በሰው ዘር መናፈሻ ውስጥ እንደበቀሉ የተለያዩ ቀለሞች እንዳሉዋቸው ጽጌረዳዎች አድርገን ማሰብና ከእነርሱም መካከል በመሆናችን መደሰት አለብን።

***መልመጃዎች***

**1.** ከላይ የተሰጠውን ምንባብ በቡድን ተከፋፍላችሁ በተለመደው መንገድ ካጠናችሁ በኋላ በታች ከተዘረዘሩት የጭውውት ርዕሶች ውስጥ የውይይቱን ሰንሰለት ሳይበጥሱ የምንባቡን ሐሳቦች በቀላሉ ለመናገር በሚችሉባቸው ላይ ምልክት ያድርጉ። በመረጡት ርዕስ ላይ በቡድንዎ ውስጥ ጭውውት ፈጠረው እንዴት ሐሳቦቹን መናገር እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ። የተቀሩት የቡድንዎ ተሳታፊዎች ተመልክተው አስተያየታቸውን ይስጡና ተወያዩባቸው።

_______ መናፈሻ
_______ ስብጠር
_______ የተፈጥሮ ውበት
_______ ከኑሮ ደረጃ ልዩነት የሚመነጭ አጉል ጥላቻ

**2.** “የዓለም ሕዝቦችን አንድ ለማድረግ ምን አስተወጽኦ ማድረግ እንችላለን?” ተብለው ቢጠየቁ እንዴት ይመልሳሉ? __________________________________________
______________________________________________________________
______________________________________________________________
______________________________________________________________
____________________________________

**3.** ከጓደኞችዎ ጋር በዚህ ርዕስ ጭውውት በሚያደርጉበት ጊዜ መጥቀስ ይችሉ ዘንድ ከዚህ በታች የሚገኙትን ጥቅሶች በቃልዎ መያዝ ይፈልጉ ይሆናል።

“የአንድነት ድንኳን ተተክሏል እርስ በርሳችሁ እንደ ባዕዳን አትተያዩ። እናንተ የአንድ ዛፍ ፍሬዎች የአንድ ቅርንጫፍም ቅጠሎች ናችሁ።”[23]

“የአንድነት ብርሃን በከፍተኛ ኃይል የተመላ ስለሆነ መላውን ምድር ለማብራት ይችላል።”[24]

“ፊቶቻችሁን ወደ አንድነት መልሱ የብርሃኑም ጨረር በእናንተ ላይ እንዲያበራ አድርጉ። በአንድ ላይ ተሰብሰቡ ለአምላክ ብላችሁም በመካከላችሁ የፍልሚያ ምንጭ የሆነውን ማንኛውንም ነገር ነቅላችሁ ለመጣል ወስኑ።”[25]

## *ምዕራፍ 10*

*ብዙ ሰዎች ትልቅ ትኩረት የሚሰጡት ርዕስ ፍትህ ነው:: ቀጣዩ ምንባብ በዚህ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ላይ ከሰዎች ጋር በሚወያዩበት ጊዜ የእምነቱን አመለካከት ለመግለጽ እንዲችሉ ይረዳዎታል::*

*በሰዎች መካከል የችሎታ መለያየት ለሰው ሕልውና መሰረት ነው:: ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ወይም እኩል ችሎታ ሊኖረው አይችልም:: ይሁንና የሰዎች ሁሉ ጉዳዮች በፍትህ መርህ መተዳደር ይኖርባቸዋል::*

*ፍትህ ውሱን ሳይሆን ሁለንተናዊ ባህርይ አለው:: በሁሉም የህብረተሰብ ደረጃዎች ውስጥ መስራት አለበት:: ፍትህ ቅዱስ ነገር ሆኖ ሊቆጠር ይገባል:: የሰዎች ሁሉ መብቶች መጠበቅ አለበት:: የኅብረተሰብ ህግጋት ጥቂት ሰዎች ሐብትን እያግበሰበሱ ሌሎቹ ጎስቋሎች እንዳይሆኑ ተደርጎ መቀረጽና ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል:: ከበሃኦላህ ትምህርቶች መካከል ፍጹም ኃብታምነትንና ፍጹም ድህነትን ማስወገድ አንዱ ነው::*

*እያንዳንዱ ግለሰብ የሰው ልጅ አካል ክፍል ስለሆነ እያንዳንዱ የህብረተሰብ አባል የሥልጣኔ ፍሬ ተቃማሽ መሆን ይገባዋል:: አንዱ የሰውነት ክፍል ካዘነና ከተከዘ ሌሎች መከራው ሊሰማቸው ይገባል:: አንዱ ክፍል እየተሰቃየ ሌሎቹ እንዴት ሊዝናኑ ይቻላቸዋል? ሆኖም ዛሬ በአንድነት የተሞላ ግንኙነት ባለመኖሩ አንዳንዶች በታላቅ ምቾትና መንደላቀቅ በእርካታ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ምግብና መጠለያ በማጣት ይሰቃያሉ:: ያለንበት ህብረተሰብ ተፈላጊው መተዛዘንና መቀናጀት ይጎድለዋል:: በሚገባ የተደራጀ አይደለም:: የመላውን የሰው ልጅ ቤተሰብን ደህንነትና ደስታ የሚያስከብሩ ህግጋትና መርሆዎች ያስፈልጉታል::*

*ፍትሕ የሚመሰረተው በሽልማትና በቅጣት ምሰሶዎች ላይ ነው:: ለሽልማት መጓጓትና ቅጣትን መፍራት ሰዎችን ፍትሐዊ እንዲሆኑ ያነሳሷቸዋል:: ጭቆና እንዲወገድ ከተፈለገ እነዚህ ሁለት ስሜቶች አስፈላጊ ናቸው:: የህግጋት አውጪዎችና አስፈጻሚዎች ውሳኔዎቻቸው የሚያስከትሉትን መንፈሳዊ ውጤት ማጤን ይገባቸዋል:: አንድ ባለሥልጣን በዚህ ምድር ለሚፈጽመው ነገር ከሞት በኋላ ባለው ዓለም ተጠቃቂ እንደሚሆን ካወቀ በፍትህ ለማስተዳደር ይነሳሳል:: የሚሰጣቸው ብያኔዎች በመለኮታዊ ፍትሕ እንደሚመዘኑ የሚያውቅ መሪ በእርግጥም ጭቆናን ያስወግዳል::*

### *መልመጃዎች*

**1.** *በቡድን ተከፋፍላችሁ እንደተለመደው ምንባቡን ካጠናችሁ በኋላ የምንባቡን ሃሳቦች በቀላሉ ለማስተዋወቅ በሚመቾት የጭውውት ርዕሶች ላይ ምልክት አድርጉ:: ከዚያም በመረጡት ርዕስ ላይ ጭውውት ፈጥረው ሃሳቦቹን እንዴት መናገር እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ:: በመጨረሻም ባቀረቡት ጭውውት ላይ ቡድንዎ አስተያየት ይስጥበትና ተወያዩበት::*

_______ *የሰው መብት*
_______ *ጭቆና*
_______ *ድህነትን ማጥፋት*
_______ *ሥራ አጥነት*

**2.** *በዚህ ርዕስ ላይ ሲናገሩ የሰማዎ አንድ ሰው "ፍጹም ሐብታምነትና ፍጹም ድህነትን እንዴት ማስወገድ ይቻላል?" ብሎ ቢጠይቅዎ እንዴት ይመልሱታል?* _______________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. የሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ እንዲይዙ ይጠየቃሉ፡፡

"የሰዎች ብርሃን ፍትሕ ነው በጭቆናና በግፍ ተጻራሪ ነፍሶች አታጥፉት የፍትሕ ዓላማ በሰዎች መካከል አንድነት ማከሰት ነው፡፡"[27]

"ከፍትሕ ብርሃን ጋር የሚወዳደር ምንም ብርሃን የለም፡፡ የዓለም መደራጀትና የሰው ዘር እርጋታ በዚህ ይወሰናል፡፡"[28]

"ዓለምን የሚያስለጠነው ፍትሕ ነው በሽልማትና በቅጣት ሁለቱ ምሰሶዎች ተደግፎ የቆመ ነውና፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምሰሶዎች ለዓለም የሕይወት ምንጮች ናቸው፡፡"[29]

## ምዕራፍ 11

የሴትና የወንድን እኩልነት አስመልክተው ከጓደኛዎ ጋር ሲጨዋወቱ ከዚህ በታች ባለው ምንባብ የተካተቱ ሃሳቦችን ያስተላልፉ ይሆናል፡፡

ቁሳዊዋ ፀሐይ በብርሃንዋና በሙቀቷ አማካኝነት በምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ እውነታ ትከሰታለች፡፡ ጨረሮቿ ባይኖሩ ኖሮ ሁሉም ነገሮች በጨለማ ተሸፍነው ይኖሩ ነበር፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የበሃኦላህ ፀሐይ በመንፈሳዊ ሰማይ በሙሉ ድምቀት እያበራች ባለፉት ጊዜያት ግልጽ ያልነበሩ እውነታዎችን ከስታለች፡፡ ከእነዚህ እውነታዎች አንዱ የሴቶችና የወንዶች እኩልነት ነው፡፡ በእውነት ፀሐይ ጨረሮች አማካኝነት የሴቶች ችሎታዎች ግልጽ ከመደረጉ የተነሳ የወንዶችና የሴቶች እኩልነት አሁን የተረጋገጠ እውነት ነው፡፡

በአምላክ ዘንድ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት እንደሌለ በሃኦላህ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ተናግሯል፡፡ ባለፉት ዘመናት ሁሉ እኩልነት ያልነበረበት ምክንያት ወንዶች የሚበልጡ ሆነው ሳይሆን ሴቶች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከወንዶች እኩል እድል ስላልተሰጣቸው ነው፡፡ ምንም እንኳን የጾታ ጭቆና ቢደርስባቸውም ከፍተኛ ተግባር የፈጸሙ ብዙ ሴቶች በታሪክ ተመዝግበዋል፡፡

የአምላክን እዲሱን ግልጸት እውነተኛነት ያመነችው የመጀመሪያዋ ሴት የፋርሷ ገጣሚ ጣሂሬ ናት፡፡ የአዲስ ቀንን ንጋት በተመለከተች ጊዜ ወንዶችና ሴቶች እኩል መሆናቸውን ተገንዝባ ሙሉ ኃይሏን ይህንን እውነት በማወጅ ላይ አዋለች፡፡ እውቀቷና አንደበተ ርቱዕነቷ በጊዜው የተማሩ የተባሉ ወንዶችን አወከ፡፡ የጨቋኙ ንጉሥና አላዋቂና በኩራት የተወጠሩ ቀሳውስት የተባበሩ ኃይሎች ተነስተውባት የነበሩ ቢሆንም እንኳን እውነቱን ከመናገር አንድም ጊዜ ወደኋላ አላለችም፡፡ በመጨረሻም አጥብቃ ለያዘችው አዲስ እምነት ተሰዋች፡፡ አምላክ ያልፈቀደውን ነገር ማመን ድንቁርናና አጉል አምልኮ ነው፡፡ ዛሬ ሴቶች እንዲማሩና ሰው በተሰማራባቸው መስኮች ሁሉ ከወንዶች እኩል ቦታ እንደያገኙ ተገቢው ዕድል ሁሉ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንደመንፈሳዊ ዓለም በዚህም ዓለም የወንዶችና የሴቶች እኩልነት እውን ካልሆነ የሰው ልጅ እውነተኛ እድገት ሊያደርግ አይችልም፡፡

***መልመጃዎች***

1. በቡድን ተከፋፍላችሁ እንደተለመደው ምንባቡን ካጠናችሁ በኋላ የምንባቡን ሃሳቦች በቀላሉ ለማስተዋወቅ በሚመቹዎት የጭውውት ርዕሶች ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡ ከዚያም በመረጡት ርዕስ ጭውውት ፈጥረው ሃሳቦቹን እንዴት ማስተላለፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡ በመጨረሻም ባቀረቡት ጭውውት ላይ ቡድንዎ አስተያየት ይስጥበትና ተወያዩበት፡፡

______ የቤተሰብ ሕይወት
______ የሰላም መመስረት
______ በታሪክ የተመዘገቡ ታላላቅ ሴቶች
______ የሰው ልጅ ዕድገት

2. "በሁሉም መስኮች ሴቶች ከወንዶች እኩል ቦታ ከያዙ ልጆችን ማን ያሳድጋል?" ተብለው ቢጠየቁ እንዴት ይመልሳሉ?________________________________________
______________________________________________________________
______________________________________________________________
______________________________________________________________
______________________________________________________________
__________________________________________

3. በዚህ ርዕስ ጋር ዝምድና ያላቸውን የሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ ቢይዙ ይጠቅምዎታል፡፡

"በእግዚአብሔር ፊት ሴቶችና ወንዶች እኩል ነበሩ ወደፊትም ሁል ጊዜ እኩል ይሆናሉ፡፡"[30]

"እኛ ለምን ከአንድ ዓይነት ትቢያ እንደፈጠርናችሁ አታውቁምን አንዱ ከሌላው ራሱን ከፍ እንዳያደርግ ነው፡፡"[31]

"በአሁኑ ጊዜ የመለኮታዊ ጸጋ እጅ መበላለጥን ሁሉ አስወግዷል፡፡ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና የእርሱ ሴት አገልጋዮች በአንድ ደረጃ ላይ ይታያሉ፡፡"[32]

# ምዕራፍ 12

በመጨረሻ እንድያጠኑ የሚጠየቁት ምንባብ ሁለንተናዊ ትምህርት በሚል ርዕስ ላይ የቀረበ ነው፡፡

በሃኦላህ በትምህርቶቹ አጽንኦት ከሰጠባቸው መርሖዎች አንዱ ሁለንተናዊ ትምህርት ነው፡፡ ከዘመናችን እጅግ አንገብጋቢ ነገሮች አንዱ ትምህርትን ማስራጫት ነው፡፡ ትምህርትን ከማዕከላዊ ጉደዮቹ መካከል አንዱ ያላደረገ ማንም ሃገር ሊበለጽግ አይችልም፡፡ ለሕዝቦች ውድቀት ተቀዳሚው ምክንያት ድንቁርና ነው፡፡ ትምህርት ለአንድ መንግሥትና ለሕዝቦቹ ክብርን ብልጽግናን ነፃነትን ያጎናጽፋል ከጥገኝነት ያላቅቃል፡፡

ትምህርት በጨቅላ ዕድሜ መጀመር አለበት፡፡ እናትና አባት ልጆቻቸውን የማስተማር ባሕሪያቸውን በመንፈሳዊና የሥነ ምግባር ሕጎች የማነጽና በሳይንስና በጥበብ የማሰልጠን ኃላፊነታቸውን ለመወጣት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡ እናቶች የሰው ልጅ የመጀመሪያ መምህራን ናቸው፡፡ በመታቀፊያ ያለን ህፃን ይንከባከቡታል ከእውቀትም ጡትም ያጠቡታል፡፡ ሁሉም ህፃን

*መማር አለበት፡፡ ይህ ጉዳይ ቸል ሊባል አይገባውም፡፡ ወላጆች የትምህርቱን ወጪ መሸፈን ከቻሉ መክፈል አለባቸው፡፡ የማይችሉ ከሆነ ማህበረሰቡ የትምህርቱን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡*

*ትምህርት ልቀትን የመቀዳጀት ፍላጎትን በሁሉም ሰው ውስጥ ማዳበር አለበት፡፡ ሰው ሰብአዊ ምሉዕነትን ማፍቀርና ይህንንም ለመቀዳጀት በስሜት መጣር አለበት፡፡ መንፈሳዊ ልቀትን ለማግኘት ሰውን ለማገልገል ለፍቅርና ለፍትህ ባለው ጉጉት ታዋቂ መሆን አለበት፡፡ ሰላምንና አንድነትን ለማራመድና ትምህርትን ለማዳረስ በሚያደርገው ጥረት ለየት ለማለት ማጣር አለበት፡፡*

***መልመጃዎች***

**1.** በቡድን ተከፋፍላችሁ እንደተለመደው ምንባቡን ካጠናችሁ በኋላ የምንባቡን ሃሳቦች በቀላሉ ለማስተዋወቅ በሚመችዎት የጭውውት ርዕሶች ላይ ምልክት ያድርጉ፡፡ ከዚያም በመረጡት ርዕስ ላይ ጭውውት ፈጥረው ሃሳቦቹን እንዴት ማስተላለፍ እንደሚችሉ ለማሳየት ይሞክሩ፡፡ ጭውውት ላይ ቡድንዎ አስተያየት ይስጡበትና ተወያዩበት፡፡

_______ ህፃናትን ማሳደግ
_______ የኅብረተሰብ ዕድገት
_______ የሳይንስ ኃይል
_______ የትምህርት ቤት አሰጣጥ

**2.** "በምድር ላይ ለሚኖሩ በቢሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሕዝቦች ትምህርትን ማዳረስ የሚቻለው እንዴት ነው ብለው ያስባሉ? ተብለው ቢጠየቁ እንዴት ይመልሳሉ? ____________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
______________________________________________________________________
________

**3.** ከበሃኦላህ ጽሑፎች የተወሰዱትን የሚከተሉትን ጥቅሶች በቃልዎ ቢይዙ?

"*አዕምዎቻችሁንና ፈቃዳችሁን የምድርን ሕዝቦችና ዘሮች ወደማስተማሩ ተግባር አዙሩ፡፡*"[34]

"*ኪነጥበብ የእጅ ሥራና የሳይንስ ዕውቀት የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ የሚያደርጉና ክብርም የሚሰጡ ናቸው፡፡ ዕውቀት ለሰው ልጅ ሕይወት ክንፍና ለዕድገቱም መሰላል ነው፡፡*"[35]

"*በእውነቱ ዕውቀት ለሰው ልጅ የማይጠፋና የማይባክን ሃብት ነው፡፡ የክብር፥ የደስታ፥ የቸርንት፥ የከፍተኛ ስሜት፥ የፍስሐና የተድላ ምንጭም ነው፡፡*"[36]

## *የጥቅሶች ማመሣከሪያ*


1. ከአብዶል በሃ በሾጊ ኤፌንዲ "የበሃኦላህ የዓለም ሥርዓት" በሚለው መጽሐፍ የተጠቀሰ የአሜሪካን እትም ገጽ 139

2. ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት የአሜሪካን እትም ቁጥር 119 ገጽ 215

3. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 132 ገጽ 287

4. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 34 ገጽ 79-80

5. ከኪ.ታብ. አቅደስ (እጅግ በጣም ቅዱስ መጽሐፍ) በኋላ ከተገለጹት የበሃኦላህ ጽላቶች የአሜሪካ እትም ገጽ 161

6. ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቁጥር 111 ገጽ 217

7. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 43 ገጽ 95

8. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 110 ገጽ 215

9. ከኪ.ታብ. አቅዳስ በኋላ ከተገለጹት የበሃኦላህ ጽላቶች ገጽ 220

10. ከበሃኦላህ ከኪ.ታብ. ኢ.ቃን (የእርግጠኝነት መጽሐፍ) የአሜሪካን እትም ገጽ 142

11. ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት ቁጥር 34 ገጽ 80

12. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 28 ገጽ 70

13. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 24 ገጽ 59

14. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 25 ገጽ 60

15. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 14 ገጽ 30

16. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 18 ገጽ 45

17. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 106 ገጽ 213

18. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 106 ገጽ 213

19. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 96 ገጽ 196

20. ከኪ.ታብ. አቅዳስ በኋላ ከተገለጹት የበሃኦላህ ጽላቶች ገጽ 29-30

21. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 63-64

22. ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት ቁጥር 131 ገጽ 186

23. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 112 ገጽ 218
24. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 132 ገጽ 288
25. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 111 ገጽ 217
26. ከኪ.ታብ. አቅዳስ በኋላ የተገለጹት የበሃኦላህ ጽላቶች ገጽ 90
27. ከላይ ከተጠቀሰው ቁጥር 66-67
28. ከበሃኦላህ የሾጊ ኤፌንዲ የመለኮታዊ ፍትሕ ምጽአት በሚለው መጽሐፍ የተጠቀሰ የአሜሪካን እትም ገጽ 28
29. ከኪ.ታብ. አቅዳስ በኋላ ከተገለጹት የበሃኦላህ ጽላቶች ገጽ 27
30. ከበሃኦላህ ሴቶች በተባለው ጥንቅር የካናዳ እትም ቁጥር 51 ገጽ 26
31. የበሃኦላህ ኅቡዓተ ቃላት ከአረብኛ ቁጥር 68
32. ከበሃኦላህ ሴቶች በተባለው ጥንቅር ቁጥር 3 ገጽ 3
33. ከበሃኦላህ እክስለንስ አን ኦል ትንግስ በተባለው

34. ከበሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት ቁጥር 156 ገጽ 333
35. ከበሃኦላህ ይድረስ ለተኩላው ልጅ በተባለው መጽሐፍ የአሜሪካ እትም ገጽ 26
36. ከላይ ከተጠቀሰው ገጽ 27